# ለንግድ ፡ ማኅበር ፡ ሕግ ፡ መግቢያ ።

በኤቨረት ፡ ኤፍ ፡ ጎልድበርግ ።

የ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አዲስና ፡ አጠቃላይ ፡ የሆነ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ሕግ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ፈጠረ ። የዚህም ፡ ጽሑፍ ፡ ዓላማ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ጠቅላላ ፡ ደንቦችንና ፡ መመሪያዎችን ፤ ከሌሎች ፡ ሕጎች ፡ ጋር ፡ ያላቸውን ፡ ግንኙነትና ፡ የሚፈጥሩትን ፡ አንዳንድ ፡ ችግሮች ፡ መተንተን ፡ ነው ። ከመግቢያው ፡ ማብራሪያ ፡ በኋላ ፡ የሚታዩት ፡ ጉዳዮች ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ አከፋፈል ፤ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ ስለመስጠት ፡ (የተወሰነ ፡ ኃላፊነትንና ፡ ዋና ፡ ገንዘብን ፡ ጨምሮ) ፤ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፤ ጠቅላላ ፡ የአመሠራረት ፡ ደንቦችና ፡ ስለ ፡ መፍረስ ፡ ናቸው ።[1] በሥራ ፡ አስኪያጅነትና ፡ በሂሳብ ፡ ቁጥጥር ፡ ላይ ፡ የሚሠሩት ፡ ዐይነት ፡ ደንቦች ፡ አልተመረመሩም ።

## ፩. በጠቅላላው ፡

ትርጓሜ ፡- የንግድ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪፻፲ ፡ የንግድ ፡ ማኅበርን ፡ እንደዚህ ፡ ይተረጉመዋል ፡ "ማናቸውም ፡ በሽርክና ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ የሚቋቋም ፡ ማኅበር ፡ ነው ።" የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ማለት ፡ "ሁለት ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ መዋጮ ፡ አዋጥተው ፡ በአንድነትና ፡ በኅብረት ፡ የኤኮኖሚ ፡ ተግባር ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ለመሥራትና ፡ ከሚገኘው ፡ ትርፍም ፡ ሆነ ፡ ከሚመጣው ፡ ዕዳ ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ የሚስማሙበት ፡ ውል ፡ ነው ።"[2]

ጽኑ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ በተደረገ ፡ ማንኛውም ፡ ጊዜና ፡ ሌላ ፡ ተፈላጊ ፡ ደንቦች ፡ ከአሉና ፡ እነዚህ ፡ ደንቦች ፡ ተሟልተው ፡ ከተገኙ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ይኖራል ። ስምምነቱ ፡ የማኅበሩ ፡ መሠረት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ማኅበሩ ፡ ከስምምነቱ ፡ በላይ ፡ ነው ። ሕጉ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮችን ፡ የሚመሩ ፡ ብዙ ፡ ድንጋጌዎች ፡ አሉት ። ከነዚህም ፡ ብዙዎቹ ፡ በስምምነቱ ፡ ሊለወጡ ፡ (ሊሻሻሉ) ፡ የማይችሉ ፡ ናቸው ። ከእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ በቀር ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ በሙሉ ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ አላቸው ። ስለዚህም ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ በሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ የተመረኰዘ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከእርሱ ፡ የተለየ ፡ የድርጅት ፡ ዓይነት ፡ አኗኗር ፡ አለው ።

እንደ ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ የሰዎች ፡ ስብሳቤ ፤ የንግድ ፡ ማኅበር ፤ ሰዎች ፡ ብቻቸውን ፡ ሊሠሩት ፡ የሚያዳግታቸውን ፡ ወይም ፡ የሚያቅታቸውን ፡

---

1. የሕጉ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ጽሑፉን ፡ በአዘጋጁበት ፡ ጊዜ ፡ ከብዙ ፡ ምንጮች ፡ የቀሰሙ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ድንጋጌዎች ፡ በብዛት ፡ የጣሊያንን ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ፭ ፤ አንቀጽ ፡ ፭ን ፡ ይመስላሉ ። የኢታሊያን ፡ ሎው ፡ ኦፍ ፡ ካምፓኒስን ፡ ተመልከት ። ሌበር ፡ ኤንተር ፡ ፕራይዝ ፡ ኤንድ ፡ ኢኮኖሚክ ፡ ኦርጋኒዜሽን ፡ (በቢ ፡ ቤንቶሩኢ ፤ ዲቢንተር ፤ ሆላንድ ፤ ክሉዌር ፤ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተተረጐመ) ።

2. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፩ ፡

ነገሮች ፡ እንዲሠሩ ፡ ያደርጋቸዋል ። የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ልዩ ፡ የሚሆነው ፡ አላማው ፡ ትርፍን ፡ የማግኘት ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። ትርፍም ፡ ሲባል ፡ የገንዘብ ፡ ትርፍ ፡ እንጂ ፡ መንፈሳዊ ፡ ወይም ፡ የአእምሮ ፡ ጥቅም ፡ አይደለም ። የማኅበሩ ፡ አባሎችን ፡ ጥቅም ፡ ለማበርከት ፡ "ቁጠባ ፡ (ኤኮኖሚ) ፡ እንዲያደርጉ ፡ በመፍቀድ ፡"[3] የገንዘብ ፡ ፍላጐታቸውን ፡ ማሟላትንም ፡ ይጨምራል ።

የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ በይበልጥ ፡ የሚመሩት ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ሁለተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ። ከቁጥር ፡ ፪፻፲ —፪፻፳፮ ፡ ያለው ፡ የሁለተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ክፍል ፡ በሁሉም ፡ የሚጸኑ ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ይዞአል ። ተከታዮቹ ፡ አንቀጾች ፡ የተለያዩ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮችን ፡ የሚመለከቱ ፤ ስለመለወጥና ፡ ስለመዋሐድ ፤ እንዲሁም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ የሆኑ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ይዘዋል ።

<u>የተለዩ ፡ ማኅበሮች ፡</u> ማኅበር ፡ ማለት ፤ "ትርፎችን ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለመከፋፈል ፡ ሳይሆን ፤ አንድ ፡ ውጤት ፡ ለማግኘት ፡ በሁለት ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የሚቋቋም ፡ ስብሰባ ፡ ነው ።"[4] ማኅበሮች ፡ ለብዙ ፡ ትርፍ ፡ ለማያስገኙ ፡ ጉዳዮች ፡ ሊቋቋሙ ፡ ይችላሉ ። የስፖርት ፡ ማኅበሮች ፤ የክርክር ፡ ክበብ ፤ የትምህርት ፡ ስብሳቤ ፤ የመረዳጃ ፡ ማኅበር ፤ እንዲሁም ፡ ሌሎች ፡ ምሳሌዎች ፡ ናቸው ። ከኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተክርስቲያን ፡ በቀር ፡ የሃይማኖት ፡ ስብሳቤዎች ፤ የአባሎቻቸውን ፡ የገንዘብ ፡ ጥቅም ፡ ለመከላከል ፡ ወይም ፡ ላንድ ፡ የተወሰነ ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ እንደራሴ ፡ ለመሆን ፡ የተቋቋሙ ፡ ስብሳቤዎች ፡ በልዩ ፡ ሕጎች ፡ ካልተመሩ ፡ በቀር ፡ እንደ ፡ ማኅበሮች ፡ ይቆጠራሉ ።[5]

ማኅበሮች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፬—፬፻፹፪ ፡ ይመራሉ ። እንዚህ ፡ ድንጋጌዎችና ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ሁለተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ የተለያዩና ፡ እራሳቸውን ፡ የቻሉ ፡ ናቸው ። ይኸም ፡ አባባል ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲ ፡ (፩) ፡ የንግድ ፡ ማኅበርን ፡ በሽርክና ፡ ስምምነት ፡ የሚቋቋም ፡ "ማኅበር" ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቢተረጉመውም ፡ እውነተኛ ፡ ሆኖ ፡ ይቀራል ። ይህም ፡ በመጀመሪያ ፡ ፈረንሣይኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ለተጠቀሙበት ፡ ቃል ፡ በይበልጥ ፡ ትክክለኛ ፡ በሆነው ፡ ትርጓሜ ፡ መሠረት ፡ "ስብሳቤ" ፡ ማለት ፡ ነው ።[6]

ማኅበሮች ፡ ትርፍ ፡ የማግኘት ፡ ዓላማ ፡ የሌላቸው ፡ ስለሆኑና ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ለትርፍ ፡ የሚሠሩ ፡ በመሆናቸው ፡ በተለያዩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይመራሉ ። ስለሆነም ፡ ማኅበሮች ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ በማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ቁጥጥር ፡

---

3. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፰ ፡ (፪) ፡
4. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፬ ፡
5. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፭ ፡
6. በፈረንሣይኛ ፡ ለተጻፈው ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ መመልከት ፡ የሚኖርብን ፡ ኮድ ፡ ደ ፡ <u>ኮሜርስ ፡ ደ ፡ ሌኤምፒሬ ፡ ደ ፡ ፲፱፻፷</u> ፡ (ፓሪስ ፡ ሌጂዲጂ ፤ ፲፱፻፷፬) ፤ ሲሆን ፡ ለፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ደግሞ ፡ ኮድ ፡ <u>ሲቪል ፡ ደ ፡ ሌኤምፒሬ ፡ ደ ፡ ኢቲዮፒ ፡ ደ ፡ ፲፱፻፷</u> ፡ (ፓሪስ ፡ ሌጂዲጂ ፤ ፲፱፻፷፪) ነው ። ለአማርኛ ፡ ጽሑፎች ፡ የምንመለከተው ፡ በአቶ ፡ ከበደ ፡ ካሣና ፡ በአቶ ፡ ኸብሩ ፡ ሰይፉ ፡ በተደረጉት ፡ እርዳታዎች ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ።

ሥር ፡ ናቸው ፡፡[7] በጠቅላላው ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ በንግድና ፡ እንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ናቸው ፡፡[8]

አንድ ፡ ትርፍ ፡ ለማያስገኝ ፡ ጉዳይ ፡ የተቋቋመ ፡ ስብሳቢ ፡ ትርፍ ፡ የሚያስገኙ ፡ ሥራዎችን ፡ ሁልጊዜ ፡ ቢሠራስ ? በዚሀ ፡ የተመረከዘ ፡ ማመልከቻ ፡ በሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ቦርድ ፤ ወይም ፡ ከአባሎቹ ፡ በአንድ ፡ አምስተኛው ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ በማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ ለማኅበሩ ፡ በፍርድ ፡ መፍረስ ፡ ምክንያት ፡ ይሆናል ፡፡[9] የንግድ ፡ ሕግ ፡ ማኅበሮች ፡ ንግድ ፡ እንዳያካሄዱ ፡ በግልጽ ፡ ይከለክላል ፡፡ ይህም ፡ ማለት ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ትርፍ ፡ የሚያስገኙ ፡ ሥራዎችን ፡ እንዳያካሄዱ ፡ ይከለክላሉ ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡ አንድ ፡ ማኅበር ፡ ንግድ ፡ ሲያካሄድ ፡ ቢገኝ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፷፮ ፡ መሠረት ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡፡[10]

ምንም ፡ እንኳ ፡ አንድ ፡ ማኅበር ፡ ትርፍ ፡ የሚያስገኝ ፡ ሥራ ፡ ቢሠራም ፡ ያገኘውን ፡ ትርፍ ፡ ለአባሎቹ ፡ ለመስጠት ፡ የሕግ ፡ ችግር ፡ ይገጥመዋል ፡፡ ገንዘብና ፡ ሌላም ፡ የማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ማኅበሩ ፡ በፈረሰበት ፡ ጊዜ ፡ ለአባሎቹ ፡ ሊከፋፈል ፡ አይችልም ፡፡[11] ማኅበሩ ፡ ከመፍረሱ ፡ በፊት ፡ የማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ ለአባሎቹ ፡ ሊከፋፈል ፡ ይችላል ፡ የሚል ፡ ድንጋጌ ፡ የለም ፡፡ የሚል ፡ ቢኖር ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፬ ፤ ፬፻፷፯ ፡ እንዲሁም ፡ ሌሎች ፡ ተመሳሳይ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከሚፈልጉት ፡ ሁኔታ ፡ ጋር ፡ ተቃራኒ ፡ ይሆናል ፡፡ አንድ ፡ ማኅበር ፡ የተወሰኑ ፡ ሥራዎችን ፡ በየጊዜው ፡ በመሥራት ፡ ትርፍ ፡ የማያስገኙ ፡ ዓላማዎቹን ፡ ለማሟላት ፡ የሚያስችለውን ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ይችላል ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ትርፍ ፡ በሚያስገኝ ፡ ሥራ ፡ ለሁልጊዜ ፡ ሊሠማራ ፡ አይችልም ፡፡

ኅብረቶች ፡ የ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለኅበረት ፡ ሥራ ፡ ማኅበር ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡[12] አንቀጽ ፡ ፩ ፡ የኅብረት ፡ ሥራን ፡ ሲተረጉም ፡ "ዋና ፡ ዓላማና ፡ ግባቸው ፡" የሚከተሉትን ፡ የሆነ ፡ ነው ፡ ይላል ፡፡

፩/ ለብድር ፡ ገንዘብ ፡ የሚከፈለውን ፡ ወለድና ፡ ሌላም ፡ ወጭ ፡ በመቀነስ ፤

፪/ ለሥራ ፡ ውጤትና ፡ (ፕሮዳክሽን) ፡ አላቂ ፡ ነገሮችን ፡ ለማግኘት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ የመሣሪያዎችንና ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋን ፡ በመቀነስ ፤

፫/ አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻውን ፡ ቢሠራ ፡ ሊደርስበት ፡ የሚችለውን ፡ ጉዳትና ፡ ኪሣራ ፡ በኅብረት ፡ በመካፈል ፡ የያንዳንዱን ፡ ሰው ፡ ጉዳትና ፡ ኪሣራን ፡ በመቀነስ ፤

---

7. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፷፰ ፡፡ በተጨማሪም ፡ የማኅበሮች ፡ ምዝገባ ፡ ደንብ ፤ ፲፱፻፶፰ ፤ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፳፩ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፭ኛ ፡ ዓመት ፤ ቁጥር ፡ ፩ን ፡ ተመልከት ፡፡

8. የሁለቱ ፡ ሚኒስቴሮች ፡ ሥልጣኖች ፡ ይለያያሉ ፡፡ ለምሳሌም ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባዎች ፡ በሚደረጉበት ፡ ጊዜ ፡ ለማኅበሩ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ማስታወቂያ ፡ መላክን ፡ ግዳጅ ፡ የሚያደርገውን ፤ የስብሰባውን ፡ "የሥራ ፡ መልክም ፡ አፈጻጸም ፡" ለማረጋገጥ ፡ ጠቃሚዎች ፡ የሚመስሉትን ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ለማዘዝ ፡ የሚያስችለውንና ፡ ታዛቢ ፡ ሊወክል ፡ የሚያስችለውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፷፫ን ፡ ተመልከት ፡፡

9. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፷፭ ፡ (ሐ) ፡፡

10. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፲ ፡፡

11. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፷፯ ፡፡

12. የአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፵፩ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፭ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፳፱ ፡፡ በተጨማሪም ፡ የ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለ ፡ ኅብረት ፡ ሥራ ፡ ማኅበር ፡ የወጣ ፡ ደንብ ፤ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፤ ቁጥር ፡ ፫፻፳፯ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፭ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲፩ን ፡ ተመልከት ፡፡

፬/ የቴክኒክን ፡ ዕውቀት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የሚያስችሉ ፡ ዘዴዎችን ፡ እንዲስፋፉ ፡ በማድረግ ፤ ወይም ፡

፭/ ሌሎችም ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ዘዴዎች ፡ ሁሉ ፡ በመከተል ፤ በኅብረት ፡ ሥራ ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳብና ፡ ለኅብረተ ፡ ሰብ ፡ ትክክለኛ ፡ ፍትሕ ፡ ሆኖ ፡ በሚታይ ፡ ሁኔታ ፡ የኑሮ ፡ ደረጃንና ፡ ሥራን ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፤ እንዲሁም ፡ በተሻለ ፡ ዘዴ ፡ የሥራን ፡ ውጤት ፡ (ፕሮዳክሽን) ፡ ለማግኘት ፡ እንዲቻል ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

የኅብረት ፡ ሥራ ፡ ማኅበር ፡ አዋጅ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ከመዋሉ ፡ በፊት ፡ ኅብረት ፡ ሊቋቋም ፡ የሚችለው ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ዐይነት ፡ (መሠረት) ፡ እንደ ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ማኅበር ፡ ነበር ። በንግድ ፡ ማኅበር ፡ ዓይነት ፡ ሊቋቋም ፡ የሚችለው ፡ "የአባሎቹን ፡ የገንዘብ ፡ ጥቅም ፡ ለማበርከት ፡ ቁጠባ ፡ (ኢኮኖሚ) ፡ እንዲያደርጉ ፡ የፈቀደ ፡" እንደሆነ ፡ ነበር ።[13] ይኸም ፡ በይበልጥ ፡ የሚመጣው ፡ በኅብረት ፡ ሥራ ፡ ማኅበር ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፬ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፩ና ፡ ፪ ፡ ከተጠቀሱት ፡ ሥራዎች ፡ ጋር ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ለብድር ፡ ገንዘብ ፡ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብና ፡ ሌላም ፡ ወጭ ፡ መቀነስና ፡ ለሥራ ፡ ውጤትና ፡ (ፕሮዳክሽን) ፡ አላቂ ፡ ነገሮችን ፡ ለማግኘት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋን ፡ መቀነስ ፡ ናቸው ።

የኅብረት ፡ ማኅበርተኞች ፡ ወጪ ፡ ቀንሰው ፡ ገንዘብ ፡ ለማበርከት ፡ (ለመቆጠብ) ፡ የሚችሉበት ፡ አንዱ ፡ መንገድ ፡ ለማኅበሩ ፡ በመሥራት ፡ ወይም ፡ ዕቃዎቹን ፡ ከማኅበሩ ፡ በመግዛት ፡ ወይም ፡ ለማኅበሩ ፡ በመሸጥ ፡ ነው ። ይኸም ፡ በማገርና ፡ በሽያጭ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የተለየ ፡ ቀጣሪና ፡ "ገዥና ፡ ሻጭ ፡" ያጠፋዋል ።

ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ኪሎ ፡ ባቄላ ፡ በአምሳ ፡ ሣንቲም ፡ ከማንኛውም ፡ አትክልት ፡ ሱቅ ፡ ይገዛል ፡ እንበል ። የአትክልት ፡ ሱቁ ፡ ባለቤት ፡ አንዱን ፡ ኪሎ ፡ ባቄላ ፡ ከገበሬው ፡ ላይ ፡ በሰላሳ ፡ ሳንቲም ፡ ገዛ ፡ እንበል ። ከሚቀረው ፡ ሃያ ፡ ሳንቲም ፡ ውስጥ ፡ አስሩ ፡ ሳንቲም ፡ ሰውየው ፡ በሱቁ ፡ በመሥራቱ ፡ የሰውየው ፡ ወጪ ፡ ሆኖ ፡ አሥሩን ፡ ሣንቲም ፡ እንደ ፡ ትርፍ ፡ ያቆየዋል ፡ እንበል ። በዚህም ፡ መሠረት ፡ ብዙ ፡ ባቄላ ፡ በይዎች ፡ (ገዥዎች) ፡ ተስማምተው ፡ ባቄላ ፡ የሚሸጥና ፡ የሚገዛ ፡ አንድ ፡ የኅብረት ፡ ማኅበር ፡ ቢያቋቁሙ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ከአንዱ ፡ ኪሎ ፡ ባቄላ ፡ ላይ ፡ አሥር ፡ ሳንቲም ፡ ሊያተርፉ ፡ ይችላሉ ። ማኅበሩ ፡ ከገበሬው ፡ ላይ ፡ አንዱን ፡ ኪሎ ፡ በሰላሳ ፡ ሳንቲም ፡ ሂሳብ ፡ ይገዛል ። የማኅበሩም ፡ ወጪ ፡ ከአትክልት ፡ ሱቁ ፡ ባለቤት ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ነው ፡ እንበል ፡ ይኸውም ፡ በአንድ ፡ ኪሎ ፡ አሥር ፡ ሳንቲም ፡ ማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ትርፍ ፡ የሚወስድ ፡ የሱቅ ፡ ባለቤት ፡ (ገዥና ፡ ሻጭ) ፡ ስለሌለ ፡ የኅብረቱ ፡ ማኅበርተኞች ፡ አንዱን ፡ ኪሎ ፡ ባቄላ ፡ በአምሳ ፡ ሣንቲም ፡ ከመግዛት ፡ ይልቅ ፡ በአርባ ፡ ሳንቲም ፡ ሊያገኙ ፡ ይችላሉ ። ወይም ፡ ኅብረቱ ፡ አንዱን ፡ ኪሎ ፡ ባቄላ ፡ በአምሳ ፡ ሳንቲም ፡ ሸጦ ፡ ትርፉን ፡ (ከእያንዳንዱ ፡ ኪሎ ፡ ላይ ፡ አሥር ፡ ሣንቲም ፡ የሚሆነውን) ፡ በዓመቱ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ለአባሎቹ ፡ ሊያከፋፍል ፡ ይችላል ። ተጣሪ ፡ ውጤቱ ፡ አንድ ፡ ነው ። እንደሌላ ፡ ምሳሌ ፡ አንድ ፡ የብድር ፡ ኅብረትን ፡ እንመልከት ። የብድር ፡ ኅብረት ፡ ዓላማ ፡ ለማኅበርተኞቹ ፡ ባንክ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ አበዳሪ ፡ ድርጅት ፡ ከሚሰጠው ፡ ወለድ ፡ በማሳነስ ፡ የገንዘብ ፡ ብድር ፡ መስጠት ፡ ነው ። (የሚጠይቀውም ፡ ዋስትና ፡ አነስተኛ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።) ባንክ ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ተበዳሪ ፡ ዘጠኝ ፡ ከመቶ ፡ ወለድ ፡ ያስከፍላል ፡ እንበል ። የብድር ፡ ኅብረቱ ፡ ከባ

13. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፰ ፡ (፪) ።

ንኩ ፡ በአንስተኛ ፡ ወለድ ፡ ሊበደር ፡ ይችላል ፡ ምክንያቱም ፡ የሚበደረው ፡ ገንዘብ ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ስለሚሆንና ፡ (እያንዳንዱ ፡ ማኅበርተኛ ፡ ሊበደር ፡ የሚችለው ፡ ተደ ምሮ) ፡ የተሻለ ፡ ዋስትና ፡ ስለሚሰጥ ፡ ነው ። አነስተኛው ፡ ወለድ ፡ ሰባት ፡ ከመቶ ፡ ነው ፡ እንበል ። የብድር ፡ ኅብረቱም ፡ በስምንት ፡ ከመቶ ፡ ወለድ ፡ ለማኅበርተኞቹ ፡ ሊያበድር ፡ ይችላል ። ኅብረቱ ፡ ከማኅበርተኞቹ ፡ ከሚያገኘው ፡ ስምንት ፡ በመቶና ፡ እሱ ፡ ለባንክ ፡ ከሚከፍለው ፡ ሰባት ፡ ከመቶ ፡ መሐል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ወጪውን፡ ይሸፍንበታል ። ተበዳሪው ፡ ማኅበርተኛ ፡ አንድ ፡ ከመቶ ፡ ለእራሱ ፡ አትርፏል ፡ ማለት ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ከባንክ ፡ ተበድሮ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ለተበደረው ፡ ገንዘብ ፡ መክፈል ፡ የሚኖርበት ፡ ዘጠኝ ፡ ከመቶ ፡ ወለድ ፡ ሲሆን ፡ አሁን ፡ የሚከፍለው ፡ ስምንት ፡ በመቶ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

ማንኛውም ፡ በኅብረት ፡ ሥራ ፡ ማኅበር ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፬ ፡ ላይ ፡ የሠፈሩ ትን ፡ አላማዎችና ፡ ግቦች ፡ ያሉት ፡ ኅብረት ፡ በዚሁ ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ ሊቋቋም ፡ ይችላል ። በዚህም ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ የተቋቋመ ፡ ኅብረት ፡ በሕዝባዊ ፡ ኑሮ ፡ እድ ገትና ፡ የማኅበራዊ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ በኅብረት ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮች ፡ መዝገብ ፡ ቤት ተመዝግቦ ፡ በአዋጁና ፡ በሚኒስቴሩ ፡ አመራር ፡ ዕቅድ ፡ መሠረት ፡ ይመራል ። በአ ዋጁ ፡ አንቀጽ ፡ ፵፱ ፡ መሠረት ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በእንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ የኅብረት ፡ ሥራ ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚነት ፡ የላቸውም ፡-

> በተለይ ፡ ከዚህ ፡ አዋጅ ፡ ዓላማና ፡ ድንጋጌዎች ፡ ጋር ፡ የሚስማማ ፡ ካል ሆነ ፡ በቀር ፡ በኅብረት ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆኑም ። በተለይም ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ስለንግድ ፡ ሥራ ፡ ድርጅቶች ፡ አቋም ፡ አመዘጋገብና ፡ የሥራ ፡ አካሄድ ፡ የተደነገገው ፡ በኅብረት ፡ ሥራ ፡ ማኅበ ሮች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

ነገር ፡ ግን ፡ በኅብረት ፡ ሥራ ፡ ማኅበር ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ ምዝገባ ፡ ግዳጅ ፡ ያለመ ሆኑ ፡ መታወቅ ፡ አለበት ። ማኅበርተኞች ፡ ገንዘብ ፡ እንዲቆጥቡ ፡ የሚያደርግ ፡ (የሚ ያስችል) ፡ ኅብረትን ፡ ለማቋቋም ፡ የሚፈልጉ ፡ ሰዎች ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ በተሰጠው ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ዐይነት ፡ ሊያቋቁሙት ፡ ይችላሉ ።

<u>ሌሎች ፡ ማኅበሮች</u> ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ከሁለት ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ትርፍ ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለመካፈል ፡ በመፈለግ ፡ አንድ ፡ ስብሳቤ ፡ ቢያቋቁሙ ፡ ስብሳቤ አቸው ፡ የንግድ ፡ ማኅበርን ፡ በሚመለከቱ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይመራል ። ስብሳቤአቸው ፡ በሌላ ፡ ዓላማ ፡ ተንሳስቶ ፡ የተቋቋመ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ማኅበሮችን ፡ በሚመለከቱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይመራል ።[15] ነገር ፡ ግን ፡ ልዩ ፡ ሕጎች ፡ ከማኅበሮችና ፡ ከንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ የተለዩ ፡ ስብሳቤዎችን ፡ ሊፈጥሩ ፡ ይች ላሉ ። ከነዚህም ፡ አንዳንድ ፡ ሕጎች ፡ እንዳንድ ፡ የተለዩ ፡ ስብሳቤዎች ፡ የሚመሠ ረቱበትን ፡ ደንቦች ፡ ይሰጣሉ ። ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ ለተወሰኑ ፡ ማኅበሮች ፡ ቻርተሮች ፡ ናቸው ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ውስጥም ፡ የጋራ ፡ ባለኃብቶችን ፡ የሚያስተዳድሩ ፡ ደን ቦች ፡ አሉ ፤ የአንድ ፡ ሕንፃ ፡ ክፍያ ፡ የእያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ሲሆን ፡ ሌላው ፡ ደግሞ ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ የሚሆንበትን ፡ ሁኔታ ፡ (በቁጥር ፡ ፲፪፻፶፯—፲፪፻፸፯) ፤ የኅብረት ፡ ስለ ሆኑ ፡ የእርሻ ፡ መሬቶች ፡ (በቁጥር ፡ ፲፩፻፺፱-፲፭፻፷፪) ፤ እና ፡ በመንግሥት ፡ የታወቁ ፡

14. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፪ ፡ (፪)።

15. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፺፯ ፡ ፬፻፭ ።

የመሬት ፡ ባለሀብቶች ፡ ማኅበር ፡ (በቁጥር ፡ ፲፪፻፶፯-፲፪፻፸፯) ፡[16] ተሰጥተዋል ። ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሌላም ፡ የኅብረት ፡ ሥራ ፡ ማኅበር ፡ አዋጅና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የገንዘብ ፡ ቁጠባና ፡ የመኖሪያ ፡ ቤት ፡ ማኅበር ፡ አዋጅ፡ አሉ ።[17] በተጨማሪም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ከመዋሉ ፡ በፊት ፡ በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ፈቃድ ፡ በቻርተር ፡ የተቋቋሙ ፡ ብዙ ፡ ለትርፍ፡ የማይሠሩ ፡ ማኅበሮች ፡ አሉ ።[18]

የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ እንደ ፡ እቁብ ፡ ዐይነት ፡ ለሆኑ ፡ የተለምዶ ፡ የኅብረት ፡ ማኅበሮች ፡ ምንም ፡ የማይሉ ፡ መሆናቸውንና ፡ እነዚህም ፡ ማኅበሮች ፡ ከሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ ቁጥጥር ፡ ውጪ ፡ መሆናቸውን ፡ አንዳንድ ፡ ደራሲያን ፡ ይናገራሉ ።[19] በዚህ ፡ ደራሲ ፡ መሠረት ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አባባል ፡ እውነተኛ ፡ አይደለም ፡ እላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፬ ና ፡ ፬፻፭ ፡ ማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ "ስብሳቢዎችን ፡" የሚመሩ ፡ ደንቦችን ፡ ይሠጣሉ ። የኅብረት ፡ ማኅበር ፡ የተለምዶ ፡ ቢሆንም ፡ ባይሆንም ፡ ስብሰባ ፡ ነው ። በቁጥር ፡ ፴፫፻፵፯ ፡ (፩) ፡ መሠረት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ በቁጥር ፡ ፴፫፻፵፯ — ፴፫፻፵፰ ፡ ለተፈጠሩ ፡ መብቶችና ፡ ሁኔታዎች ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ማንኛውም ፡ በንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ማኅበር ፡ የሚሠራ ፡ የተለምዶ ፡ ደንብ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ተተክቶአል ። በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኅብረት ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮች ፡ አዋጅ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የተቋቋመ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በሕጉ ፡ አስተሳሰብ ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ማኅበር ፡ በቁጥር ፡ ፬፻፬ ፡ ወይም ፡ ፬፻፭ ፡ መሠረት ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ የተለምዶ ፡ ኅብረት ፡ እንደ ፡ ውል ፡ ባይቆጠርም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የውል ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንጂ ፡ በተለምዶ ፡ ሕግ ፡ አይመራም ።

## ፪. የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ አከፋፈል ።

የንግድ ፡ ሕግ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮችን ፡ በሁለት ፡ በተለያዩ ፡ መንገዶች ፡ ይከፋፍላቸዋል ። ፩) እንደ ፡ ማኅበሩ ፡ የተለየ ፡ ዓይነት ፡ ፪) የንግድ ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ በመሆኑና ፡ ባለመሆኑ ። ማኅበሮች ፡ ከተለያዩ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ በሚፈልጉት ፡ የሥራ ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፡ መከፋፈልም ፡ ጠቃሚ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

16. በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደበ ፡ ንብረት ፤ ስለ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅቶችና ፡ ለልዩ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ የሚውሉ ፡ የአደራ ፡ ንብረቶች ፤ የሚናገሩትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ አወዳድሩ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፡ ምዕራፍ ፡ ፫ ።

17. ፲፱፻፶፬ ፤ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፹፰ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፩ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲፭ ።

18. ለምሳሌ ፡ የነጋዴዎች ፡ ምክር ፡ ቤት ፤ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፺ ፤ ፲፱፻፴፱ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፯ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፰ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ቀይ ፡ መስቀል ፡ ማኅበር ፤ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ፲፱፻፴፱ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፯ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ፈረስ ፡ እሽቅድምድም ፡ ክበብ ፤ የማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፴ ፤ ፲፱፻፶ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፲፯ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፯ ።

19. ጂ ፡ ክርዜቹኖቪች ፡ "ኤ ፡ ኒው ፡ ሌጂስሌቲቭ ፡ አፕሮች ፡ ቱ ፡ ከስተማሪ ፡ ሎው ፡ ዘ ፡ ሪፒልስ ፡ ፕሮቪዥን ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሲቪል ፡ ኮድ ፡ ኦፍ ፡ ፲፱፻፷" ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጥናትና ፡ ምርመራ ፡ መጽሔት ፡ ፩ኛ ፡ ቮልዩም ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ ፲፱፻፷፫ ፤ ጄ ፡ ቫንደርሊንደን ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ምንጮች ፡ መግቢያ" ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፤ ፫ኛ ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፷፮) ፤ ገጽ ፡ ፪፻፶፩ ። ስለ ፡ እቁብ ፡ መግለጫ ፡ የአስፋው ፡ ዳምጤን ፡ ተመልከት ፤ "እቁብ" ፡ ቡሌቲን ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ኤትኖሎጂካል ፡ ሶሳይቲ ።

ሁ<u>የማኅበሩ ፡ ዓይነት</u> ፡ ሕጉ ፡ ስድስት ፡ ዓይነት ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ መኖራቸውን ፡ ያረጋግጣል ። ተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፤ የእሽሙር ፡ ማኅበር ፤ የኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፤ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ኃላፊነት ፡ የአለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፤ የአክሲዮን ፡ ማኅበርና ፤ ኃላፊነቱ ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበር ። የሚከተሉት ፡ ጽሑፎች ፡ የእያንዳንዱን ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ጠባይ ፡ በአጭሩ ፡ ይገልጻሉ ።

፩/ ተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ (ቁጥር ፡ ፪፻፳፯—፪፻፸) ፡ ቁጥራቸው ፡ አነስ ፡ ባለ ፡ ሰዎች ፡ የሚቋቋም ፡ ማኅበር ፡ ነው ። የንግድ ፡ ሥራ ፡ ድርጅት ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። ይኸም ፡ ማለት ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭ ፡ ከተጻፉት ፡ ሥራዎች ፡ ማናቸውንም ፡ ሊያካሄድ ፡ አይችልም ። ቁጥር ፡ ፭ ፡ ብዙ ፡ ትርፍ ፡ የሚያስገኙ ፡ ሥራዎችን ፡ የሚተነትን ፡ ስለሆን ፡ የተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ዓይነት ፡ ጥቅም ፡ በጣም ፡ የተወሰነ ፡ ነው ። የማኅበርተኞቹ ፡ አላፊነት ፡ የተወሰነ ፡ አይደለም ። በአባልነት ፡ (በማኅበርተኝነት) ፡ የሚገኙ ፡ ጥቆሞች ፡ እንደተፈለገው ፡ የሚተላለፉ ፡ አይደሉም ።

፪/ የእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ (ቁጥር ፡ ፪፻፸፩-፪፻፸፱) ፡ ይህ ፡ ማኅበር ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የሚቋቋመው ፡ ቁጥራቸው ፡ አነስ ፡ ባለ ፡ ሰዎች ፡ ሆኖ ፡ ለተወሰነ ፡ ዓላማ ፡ (ዕቅድ) ፡ ወይም ፡ ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ከሌሎች ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ዓይነቶች ፡ በሙሉ ፡ ተለይቶ ፡ የእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የለውም ፤ መኖሩንም ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ እንዲያውቁት ፡ ማድረግ ፡ አይቻልም ። ማኅበርተኝነት (አባልነት ፡) እንደተፈለገው ፡ ተላላፊ ፡ አይደለም ። የማኅበርተኞቹ ፡ ኃላፊነት ፡ በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ እንደሚወሰነው ፡ ነው ።

፫/ የኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ (ቁጥር ፡ ፪፻፹-፪፻፺፭) ፡ ይህ ፡ ማኅበር ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ቁጥራቸው ፡ አነስተኛ ፡ በሆኑ ፡ ሰዎች ፡ የሚቋቋም ፡ ማኅበር ፡ ነው ። ማኅበርተኝነት ፡ እንደተፈለገው ፡ ሊተላለፍ ፡ አይችልም ። የማኅበርተኞቹ ፡ ኃላፊነት ፡ የተወሰነ ፡ አይደለም ። የተወሰነ ፡ ኃላፊነት ፡ የሌለበት ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ነው ። ተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበርን ፡ በሚመለከቱ ፡ ብዙ ፡ ድንጋጌዎችና ፡ በቁጥር ፡ ፪፻፹-፪፻፺፭ ፡ ይመራል ።

፬/ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ኃላፊነት ፡ የአለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ (ቁጥር ፡ ፪፻፺፮-፫፻፫) ። በመሠረቱ ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ኃላፊነት ፡ የአለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ከአንድ ፡ ልዩነት ፡ በቀር ፡ ከኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ (አንድ ፡ ዓይነት) ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ልዩነት ፡ ሁሉም ፡ ሳይሆኑ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ የሆኑት ፡ አባሎች ፡ ኃላፊነት ፡ የተወሰነ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። ማኅበርተኝነት ፡ እንደተፈለገው ፡ ተላላፊ ፡ አይደለም ። በብዙ ፡ ተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበርንና ፡ የኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበርን ፡ በሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይመራል ። ኃላፊነታቸው ፡ የተወሰነ ፡ አባሎች ፡ በመኖራቸው ፡ መጨመር ፡ የሚኖርባቸው ፡ ደንቦች ፡ በቁጥር ፡ ፪፻፺፮-፫፻፫ ፡ ተጨምረዋል ።

፭/ የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ (ቁጥር ፡ ፫፻፬-፭፻፱) ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ከተዘረዘሩት ፡ የማኅበሮች ፡ ዓይነት ፡ በሚገባ ፡ ይለያል ። ይኸውም ፡ የማኅበርተኞች ፡ በሙሉ ፡ ኃላፊነት ፡ የተወሰነ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። ግዴታ ፡ ባይሆንም ፡ ብዙ ፡ ማኅበርተኞች ፡ (አባሎች) ፡ ሊኖሩት ፡ ይችላል ። የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ የሚፈልጉ ፡ ድርጅቶችን ፡ (ኤንተርፕራይዝስ) ፡ ለማካሄድ ፡ በሚፈለግበት ፡ ጊዜ ፡ የሚመረጥ ፡ ማኅበር ፡ ነው ።

፮/ ኃላፊነታቸው ፡ ስለተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበሮች ፡ (ቁጥር ፡ ፭፻፲-፭፻፵፫) ፡ ይህ ፡ ማኅበር ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበርና ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ድብልቅ ፡ ነው ። ከአክ

ሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ጋር ፡ የሚመሳሰለው ፡ የማህበርተኞች ፡ (የአባሎቹ) ፡ በሙሉ ፡ ኃላ ፊነት ፡ የተወሰነ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። የሽርክና ፡ ማኅበርን ፡ የሚመስለው ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በቁጥር ፡ አነስ ፡ ያሉ ፡ ሰዎችን ፡ የሚይዝና ፡ የማኅበርተኝነት ፡ ጥቅም ፡ በሚፈ ለግበት ፡ ዓይነት ፡ ተላላፊ ፡ ባለመሆኑ ፡ ነው ።

በግልጽ ፡ ባልተደረገ ፡ ጥናት ፡ መሠረት ፡ ፫፻፷፬ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ በ፲፱፻፶፯ ዓ ፡ ም ፡ በንግድ ና ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ ተመዝግበው ፡ ነበር ። ከነዚህም ፡ ፻፷ ፡ ያህል ፡ የኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ የኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮችና ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ኃላፊነት ፡ ያለባቸው ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ ነበሩ ። (ሁለት ፡ ዓይ ነት ፡ ኃላፊነት ፡ ያለባቸው ፡ ማኅበሮች ፡ ስለ ፡ መጨመራቸው ፡ ወይም ፡ የተመዘገቡ ፡ ምንም ፡ ስለአለመኖራቸው ፡ በግልጽ ፡ አይታወቅም) ። የነዚህም ፡ ማኅበሮች ፡ የተገ ለጸ ፡ ጠቅላላ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ፯ ፡ ሚሊዮን ፡ ፫፻፰፩ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ነበር ። ከተመዘገ ቡት ፡ ማኅበሮች ፡ ፩፻ቱ ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበሮች ፡ ነበሩ ። የነዚህም ፡ የተገለጸ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ፩፻፲፰ ፡ ሚሊዮን ፡ ፮፻፹፩ሺ ፡ ነበር ። ፪፻ቱ ፡ ደግሞ ፡ የተገለጸ ፡ ጠቅላላ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ፴፩ ፡ ሚሊዮን ፡ ፯፻፹፫ሺ ፡[20] ያላቸው ፡ ኃላፊነታቸው ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበ ሮች ፡ ነበሩ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፹ና ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፩ ፡ ከሚ ጠቀሙበት ፡ በተለየ ፡ መንገድ ፡ "የሽርክና ፡ ማኅበርን" ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፪ ፡ (፩) ፡ በንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ስም ፡ የተጠቀመበት ፡ መሆኑ ፡ መታወቅ ፡ አለበት ። በንግድ ፡ ማኅበር ፡ ምትክ ፡ የሚጠቀሙበት ፡ የተሻለ ፡ ቃልን ፡ በመፈለግ ፡ ወይም ፡ የሚገለጠው ፡ የን ግድ ፡ ማኅበር ፡ በዓይነቱ ፤ በእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ በኮመን ፡ ሎው ፡ ውስጥ ፡ በዚያ ፡ ስም ፡ የሚጠራውን ፤ የንግድ ፡ ማኅበርን ፡ ስለሚመስል ፡ ይሆናል ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፹ና ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፩ ፡ ሲጠቀሙበት ፡ "የንግድ ፡ ማኅበር ፡"[21] ከሚለው ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ትርጉም ፡ ይኖረዋል ።

<u>የንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበር</u> ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲ 1 የንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበርን "በመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ በተግባር ፡ ማናቸውንም ፡ በዚሁ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፭ ፡ የተገለጹትን ፡ ሥራዎች ፡ የሚሠሩ ፡" በማለት ፡ ይገልጸ ዋል ፡ (ይተረጉመዋል) ። ባለአክሲዮን ፡ ማኅበሮችና ፡ ኃላፊነታቸው ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበሮች ፡ "ዓላማቸው ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ቢሆን ፡" የንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮች ፡ ናቸው ። በዚህም ፡ ትርጓሜ ፡ ላይ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፫ ፡ በቁጥር ፡ ፪፻፲፪ ፡ የተዘረዘሩት ፡ ስድስት ፡ የማኅበር ፡ ዓይነቶች ፡ ከተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ በቀር ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮች ፡ መሆን ፡ ይችላሉ ፡ በማለት ፡ ያክልበታል ። የቁጥር ፡ ፲ና ፡ ፪፻፲፫ ፡ ውጤት ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ። ተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበር ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፡ (ስለዚህም ፡ በቁጥር ፡ ፭ ፡ ከተዘረዘሩት ፡ ሥራዎች ፡ አንዳቸውንም ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም) ፤ ባለአክሲዮን ፡ ማኅበሮችና ፡ ኃላፊነታቸው ፡ የተሰወነ ፡ የግል ፡ ማኅበሮች ፡ ዓላማቸው ፡ በቁጥር ፡ ፭ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ነገሮች ፡ ቢጨምርም ፡ ባይጨ ምርም ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮች ፡ ናቸው ፤ የኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፤ ሁለት፡

20. ሰላሙ ፡ በቀለ ፤ <u>ፕራይቬት ፡ ከሜርሺያል ፡ ካምፓኒስ ፡ አንደር ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሎው ፡</u> <u>ዘር ፡ ሊጋል ፡ ኤንድ ፡ ፕራክቲካል ፡ ሲግኒፊከንስ</u> ፡ (፲፱፻፷፯ ፤ ያልታተመ ፤ በአርካይብስ ፤ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፤ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒበርሲቲ) ።

21. በፈረንሳይኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ለንግድ ፡ ማኅበር ፡ የቆመው ፡ ቃል ፡ ሶሲዬቴ ፡ (Société) ፡ ነው ።

ዓይነት ፣ ኃላፊነት ፡ ያለባቸው ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፤ የእሽሙር ፡ ማኅበሮች ፤ ዓላማ ቸው ፡ በመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በተግባር ፡ በቁጥር ፡ ፭ ፡ የተገለጹትን ፡ ሥራ ዎች ፡ ለመሥራት ፡ ከሆነ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ይሆናሉ ። ይህን ፡ ዓይነት ፡ ዓላማ ፡ ከሌላቸው ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ አይባሉም ።

የንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበር ፡ በተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ዓይነት ፡ የተቋቋመ ፡ እን ደሆነ ፡ ወይም ፡ ዓይነቱ ፡ ሳይገለጽ ፡ የተቋቋመ ፡ እንደሆነ ፡ ማኅበሩ ፡ እንደ ፡ የኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ይቆጠራል ።[22]

የንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮች ፡ በሆኑና ፡ ባልሆኑ ፡ መሐከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ በፈረንሣይኛው ፡ ንግድ ፡ ሕግ ፡ በጣም ፡ ከፍተኛ ፡ ነው ። በእንግሊዝኛው ፡ ንግድ ፡ ሕግ ፡ ልዩነቱ ፡ አነስ ፡ ይላል ። በአማርኛው ፡ ንግድ ፡ ሕግ ፡ ደግሞ ፡ ልዩነቱ ፡ በጣም ፡ ያንሳል ።

በፈረንሣይኛው ፡ ንግድ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሂሳብ ፡ መዝገብ ፡ እንዲኖራቸው ፡ የሚገደዱና ፡ መመዝገብና ፡ መታወቅ ፡ የሚኖርባቸው ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። መክሰር ፡ የሚችሉና ፡ ነጋዴዎችን ፡ በሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚመሩ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።[23]

በእንግሊዝኛው ፡ ንግድ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሂሳብ ፡ መዝገብ ፡ እንዲኖራቸው ፡ የሚገደዱና ፡ መክሰር ፡ የሚችሉ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮች ፡ ናቸው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከእሽሙር ፡ ማኅበሮች ፡ ሌላ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ በሙሉ ፡ ሊመዘገቡና ፡ ሊታወቁ ፡ ይችላሉ ። እንዲሁም ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ በሙሉ ፡ ነጋዴዎችን ፡ በሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይመራሉ ።

በአማርኛው ፡ ንግድ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሂሳብ ፡ መዝገብ ፡ እንዲኖራቸው ፡ የሚገደዱ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ከእሽሙር ፡ ማኅ በር ፡ በቀር ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ በሙሉ ፡ መመዝገብ ፡ አለባቸው ። ከእሽሙር ፡ ማኅ በር ፡ በቀር ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ በሙሉ ፡ መክሰር ፡ ይችላሉ ። የንግድ ፡ ማኅበሮች በሙሉም ፡ ነጋዴዎችን ፡ በሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይመራሉ ።

<u>የእያንዳንዱ ፡ ማኅበርተኛ ፡ ሥራ ፡ (አላፊነት)</u> ፡ ከሌሎች ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች በይበልጥ ፡ በአንዳንድ ፡ ማኅበሮች ፡ አንድ ፡ ማኅበርተኛ ፡ በሥራ ፡ የሚካፈልበት ፡ ሁኔታና ፡ የሰውየውም ፡ ምንነት ፡ ለሌሎች ፡ ማኅበርተኞች ፡ ጠቃሚዎች ፡ ናቸው ። ይኸም ፡ የአንዳንድ ፡ የንግድ ፡ ማህበሮችን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለመግለጫ ፡ ይጠቅማል ።

በተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፤ በኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፤ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ኃላፊነት ፡ በአለበት ፡ ማኅበርና ፤ በእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ የሚገኙ ፡ ሰዎች ፡ ቁጥር ፡ ብዙ ውን ፡ ጊዜ ፡ አነስተኛ ፡ ነው ። ስለሆነም ፡ የእያንዳንዱ ፡ ማኅበርተኛ ፡ አገልግሎት ፡ ከፍተኛ ፡ ነው ። የተወሰነ ፡ ኃላፊነት ፡ ከአለባቸው ፡ የሁለት ፡ ዓይነት ፡ ኃላፊነት ፡ ከአለ በት ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኞች ፡ በቀር ፡ ማኅበርተኞቹ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የሚሠሩት ፡

---

22. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፫ ፡ (፪) ። የፈረንሳይኛው ፡ ትርጉም ፡ "ተግልጿል" ፡ ከሚለው ፡ ቃል ፡ በፊት ፡ "በግልጽ ፡ ወይም ፡ በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡" የሚለውን ፡ ሐረግ ፡ ይዞአል ። የአማርኛና ፡ የእ ንግሊዝኛ ፡ ትርጓሚዎች ፡ ይተውታል ። ምክንያታዊ ፡ የሆነ ፡ አተረጓጐም ፡ ግን ፡ አብሮ ፡ ያነብበዋል ።

23. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፷፫ ፤ ፸፫ ፡ (ሒሳቦች ፡) ፪ ፤ ፪፻፴፬ ፤ ፪፻፸፫ ፤ (በመዝገብ ፡ ስለመግባትና ፡ በማ ስታወቂያ ፡ ስለመውጣት) ፤ ፲፻፶፰ ፡ (ስለመክሰር) ፤ (፷ ፤ ነጋዴዎችን ፡ የሚመሩ ፡ ድንጋጌዎች) ። በመዝ ገብ ፡ ስለመግባት ፡ ከታች ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፪፷፪ ፡ ያለውን ፡ ተመልከት ።

ለማኅበሩ ፡ ወይም ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ማኅበሩ ፡ በደንብ ፡ እንዲሠራ ፡ ከተፈ ለገ ፡ ማኅበርተኞቹ ፡ መስማማት ፡ ይኖርባቸዋል ። በነዚህም ፡ በእያንዳንዱ ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ ያልተወሰነ ፡ ኃላፊነት ፡ ያለባቸው ፡ ሰዎች ፡ አሉ ። ከባድ ፡ ውሳኔ ፡ በጠቅላላ ፡ ድምፅ ፡ መፅደቅ ፡ የአለበት ፡ መሆኑን ፡ በማመንና ፡ አንድ ፡ አባል ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፤ የማይ ችል ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፤ ወይም ፡ በሚከስርበት ፡ ጊዜ ፡ ማኅበሩ ፡ ፈራሽ ፡ የሚሆን ፡ መሆ ኑን ፡ በማመን ፡ የማኅበርተኝነት ፡ ጥቅምንም ፡ ማስተላለፍ ፡ አስቸጋሪ ፡ የሚያደርጉት ፡ ዓይ ነት ፡ ደንቦች ፡ የእያንዳንዱ ፡ ማኅበርተኛ ፡ አስፈላጊነት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያሳያሉ ።[24]

የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ጥቂት ፡ አባሎች ፡ (ማኅበርተኞች) ፡ ብቻ ፡ ሊኖሩት ፡ ይች ላል ። በሌላ ፡ አቅጣጫ ፡ ደግሞ ፡ አክሲዮኖችን ፡ ለሕዝቡ ፡ በመሸጥ ፡ ብዙ ፡ ማኅበር ተኞች ፡ እንዲኖሩት ፡ ማድረግ ፡ ይችላል ። በሁለተኛው ፡ ሁኔታ ፡ የማንኛውም ፡ ማኅ በርተኛ ፡ ምንነት ፡ ለሌሎች ፡ አባሎች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ጠቃሚ ፡ አይደለም ። ብዙ ፡ አባሎች ፡ ማኅበርተኛ ፡ የሚሆኑት ፡ ገንዘባቸውን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የማዋያ ፡ መን ገድ ፡ ስለሚያደርጉት ፡ ነው ። እነዚህም ፡ በማኅበሩ ፡ የሥራ ፡ እንቅስቃሴ ፡ ላይ ፡ በትንሹ ፡ ይካፈላሉ ፡ ወይም ፡ ምንም ፡ አይካፈሉም ፤ ለማኅበሩ ፡ ዕዳ ፡ የማኅበርተኞች ፡ በሙሉ ፡ ኣላፊነት ፡ የተወሰነ ፡ ነው ። በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ብዙ ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይህን ፡ ሁኔታ ፡ ያሳያሉ ። ስለዚህም ፡ የአንድ ፡ አባል ፡ መሞት ፡ አለመቻል ፤ ወይም ፡ መክሰር ፡ ማኅበሩን ፡ አያፈርሰውም ። የማኅበርተኝነት ፡ ጥቅም ችም ፡ እንደተፈለገው ፡ ሊተላለፉ ፡ ይችላሉ ።[25]

ኃላፊነቱ ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ እያንዳንዱን ፡ ማኅበር ፡ የሚመስል ፡ አንዳንድ ፡ ጠባይ ፡ አለው ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በቁጥር ፡ አነስ ፡ ያሉ ፡ ማኅበርተኞች ፡ ይኖሩታል ። የማኅበርተኝነት ፡ ጥቅሞች ፡ እንደተፈለገው ፡ ሊተላለፉ ፡ አይችሉም ። ነገር ፡ ግን ፡ የእያንዳንዱ ፡ አባል ፡ ኃላፊነት ፡ የተወሰነ ፡ ስለሆነ ፡ የአንዱ ፡ አባል ፡ መሞት ፤ አለመቻል ፤ ወይም ፡ መክሰር ፡ ማኅበሩን ፡ ያፈርሰዋል ፡ ተብሎ ፡ አይታመንም ።[26]

የእያንዳንዱ ፡ አባል ፡ ሥራ ፡ (አገልግሎት) ፡ የሚታየው ፡ የንግድ ፡ ማሕበሮችን ፡ ከሚመሩ ፡ ደንቦች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሩም ፡ በእያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ከሚሠራውም ፡ ጭምር ፡ ነው ። የኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበርን ፡ ዓይነት ፡ ማኅ በሮች ፡ የውስጥ ፡ ደንብ ፡ ለመወሰን ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሩ ፡ ውል ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ አነስተኛ ፡ ናቸው ። ከእሉትም ፡ ድንጋ ጌዎች ፡ ብዙዎቹ ፡ በተለያዩ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሊሻሩ ፡ ይች ላሉ ። ይህም ፡ የሚሆነው ፡ እያንዳንዱ ፡ አባል ፡ በጣም ፡ አስፈላጊና ፡ የራሱን ፡ ጥቅም ፡ ለመከላከል ፡ ይችላል ፡ ተብሎ ፡ ስለሚታመንበት ፡ ነው ። ማኅበሩ ፡ ዕዳውን ፡ አልከፍልም ፡ ቢል ፡ በባለገንዘቦች ፡ ሊከሰሱ ፡ የሚችሉ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ የማኅበሩ ፡ ማኅበርተኞች ፡ ስለአሉ ፡ በማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ያላ ቸው ፡ ሰዎች ፡ ጥብቅ ፡ የሆነ ፡ ዋስትና ፡ (መከላከያ) ፡ አይፈልጉም ። በሌላ ፡ አቅጣጫ ፡ ደግሞ ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበርን ፡ የሚመሩ ፡ ብዙ ፡ ደንቦች ፡ በሕጉ ፡ ተሰጥተዋል ። ከነዚህም ፡ በሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ሊለወጡ ፡ ወይም ፡ ሊሻሻሉ ፡ የሚችሉት ፡ ጥቂቶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ብዙ ፡ ማኅበርተኞች ፡ ባሉበት ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ እያንዳን

24. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፵፫ ፥ ፪፻፺ ፤ ፪፻፶ ፤ ፪፻፹፪ ፡ ተመልከት ።

25. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፵፫ ፡ (፫) ፤ ፬፻፺፰ ።

26. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፲ ፡ (፪) ፤ ፩፻፹፫ ፤ ፩፻፺፪ ፡ (፫) ።

ዱ፡ ማኅበርተኛ፡ ሊቆጣጠር፡ አይችልም። የአባሎቹ፡ በሙሉ፡ አላፊነት፡ የተወሰነ፡ በመሆኑ፡ ባለገንዘቦችን፡ የሚከላከሉ፡ ብዙ፡ ድንጋጌዎች፡ ያስፈልጋሉ። በመጨረሻም፡ ባለአክሲዮን፡ ማኅበሮች፡ ከፍተኛ፡ የሆነ፡ ዋና፡ ገንዘብ፡ ሊኖራቸው፡ ስለሚችሉ፡ በሰዎች፡ ማኅበር፡ ላይ፡ ከሚኖራቸው፡ ውጤት፡ በላይ፡ በኤኮኖሚው፡ ላይ፡ ሊኖራቸው፡ ይችላል፤ ለሕጉም፡ ማኅበሩ፡ በትክክል፡ እንዲሠራ፡ ማድረግ፡ በይበልጥ፡ ጠቃሚው፡ ነው።

## ፫· በሕግ፡ የሰው፡ መብት፡ ስለመሰጠት።

ትርጓሜ፤ ሰዎች፡ መብቶችና፡ ግዴታዎች፡ አሏቸው። የመብትና፡ ግዴታዎች፡ ዕቃዎች፡ ከሆኑት፡ ንብረቶች፡ ጋር፡ ሊነፃፀሩ፡ ይችላሉ። ለምሳሌ፡ አንድ፡ ወንበር፡ የአንድ፡ ሰው፡ ሀብት፡ ሊሆን፡ ወይም፡ ሊሸጥ፡ ይችላል። እሱ፡ እራሱ፡ የሌላ፡ ነገር፡ ባለሀብት፡ ሊሆን፡ አይችልም። ባለሀብትነት፡ የሰዎች፡ ብቻ፡ የሆነ፡ መብት፡ ነው። በሰዎች፡ ብቻ፡ ሊገባ፡ የሚቻለውን፡ የውል፡ ግዴታ፡ ሊገባ፡ አይችልም።

የፍትሐ፡ ብሔር፡ ሕግ፡ ቁጥር፡ ፩፡ "ሰው፡ ከተወለደበት፡ ቀን፡ አንስቶ፡ እስከሞተበት፡ ቀን፡ ድረስ፡ የሕግ፡ መብት፡ አለው"፡ ይላል። ሕጉ፡ በብዙ፡ ሁኔታዎች፡ የሕግ፡ ሰውነትን፡ ለዕቃ፡ ወይም፡ ለስብሳቤ፡ (ግሩፕ)፡ ይሰጣል። ስለዚህም፡ የንግድ፡ ሕግ፡ ቁጥር፡ ፪፻፲(፪)፡ "ከእሽሙር፡ ማኅበር፡ በቀር፡ ማንኛውም፡ የንግድ፡ ማኅበር፡ በሕግ፡ የሰው፡ መብት፡ እንዳለው፡ ሆኖ፡ ይቆጠራል።" ይላል። ይህም፡ ማኅበሩ፡ መብቶችና፡ ግዴታዎች፡ እንዲኖሩት፡ የማድረጊያ፡ መንገድ፡ ነው።[27]

የንግድ፡ ማኅበር፡ ብዙውን፡ ጊዜ፡ የሰዎችና፡ የንብረት፡ ስብሳቤ፡ ነው። ማኅበር፡ እንደሰው፡ ያልተቆጠረ፡ እንደሆነ፡ ሰዎቹ፡ በአንድነት፡ የንብረቱ፡ ባለቤቶች፡ ይሆናሉ፡ ማለት፡ ነው። የማኅበሩ፡ ሥራ፡ በሚካሄድበት፡ ጊዜ፡ የሚገባው፡ ግዴታ፡ በአንድ፡ ወይም፡ ከዚያ፡ በላይ፡ በሆኑ፡ ማኅበርተኞች፡ ስም፡ ይገባል። እነዚህም፡ ማኅበርተኞች፡ ለእንደዚህ፡ ዓይነት፡ ግዴታዎች፡ ተጠሪዎች፡ ይሆናሉ። ማኅበሩ፡ በሕግ፡ የሰው፡ መብት፡ አለው፡ ተብሎ፡ በሕጉ፡ ከተሰጠ፡ ማኅበሩ፡ ባለሀብት፡ መሆን፡ ይችላል፤ በማኅበሩም፡ ስም፡ ግዴታዎች፡ መግባት፡ ይቻላል። በሕጉ፡ ፊት፡ ከማኅበርተኞቹ፡ ተለይቶ፡ ልክ፡ እንደ፡ ሰው፡ ይታያል። ለምሳሌ፡ ያህል፡ ሀ፤ ለ፤ ሐ፤ ሰዎች፡ ናቸው፡ እንበል። 'ሀ'፤ 'ለ' ና 'ሐ'፡ ምንም፡ ለማያገባቸው፡ (መብት፡ ለሌላቸው)፡ መሬት፡ ባለሀብት፡ ነው፡ እንበል። ሁኔታው፡ ተቀይሮ፡ 'ሀ' በሕግ፡ የሰው፡ መብት፡ የተሰጠው፡ የንግድ፡ ማኅበር፡ ቢሆንና፡ 'ለ' ና፡ 'ሐ'፡ ማኅበርተኞች፡ ቢሆኑ፡ ውጤቱ፡ አንድ፡ ነው። ይኸውም፡ 'ሀ'፡ በሕግ፡ የሰው፡ መብት፡ ስለአለው፡ የመሬቱ፡ ባለሀብት፡ ነው። 'ለ' ና፡ 'ሐ'፡ አይደሉም። 'ለ' ና 'ሐ'፡ የ'ሀ'፡ ወኪሎች፡ ሆነው፡ መሬቱን፡ የሚመለከቱ፡ ጉዳዮችን፡ ሊወስኑ፡ ይችሉ፡ ይሆናል። ቢወስኑም፡ ስለመሬቱ፡ የሚያደርጉትን፡ ማንኛውንም፡ ነገር፡ የሚያደርጉት፡ በ'ሀ'፡ ስም፡ ነው። በአባልነታቸው፡ 'ለ' ና፡ 'ሐ'፡ መሬቱን፡ በሚመለከት፡ ውሳኔ፡ ላይ፡ ሊካፈሉ፡ ይችላሉ። እንደዚህም፡ ከሆነ፡ የእነሱ፡ መብት፡ በማኅበሩ፡ የመካፈል፡ እንጂ፡ የመሬቱ፡ ባለሀብት፡ የመሆን፡ አይደለም። የሚከፈል፡ ቀረጥ፡ ቢኖር፡ ማኅበሩ፡ ይከፍላል። ተመሳሳይ፡ የሆነ፡ ማብራሪያ፡ በውሎችና፡ በጥ

---

27. ስለ፡ በሕግ፡ የሰው፡ መብት፡ መስጠት፡ ብዙ፡ ክርክሮች፡ ከብዙ፡ ጊዜ፡ ጀምሮ፡ ተደርገዋል። ስለ፡ ተለያዩ፡ አባባሎች፡ መግለጫ፡ የአር፡ ፓውንድን፤ ጁሪስ፡ ፕሩደንስ፡ (ሴይንት፡ ፖል፤ ሚን፤ ዌስት፤ ፲፱፻፶፱)፡ ቮልዩም፡ ፬፡ ገጽ፡ ፻፺፩—፪፻፳፭፡ ተመልከት።

ፋት ፡ ላይ ፡ በሚመሠረቱ ፡ አላፊነቶች ፤ በጠቅላላውም ፡ ክስ ፡ ሊቀርብባቸው ፡ በሚ ቻልባቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ሊጸና ፡ ይችላል ።

ይህን ፡ መምሪያ ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በዴልቡርጎና ፡ በአ ገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ መሐል ፡ በነበረው ፡ ክስ ፡ ተጠቅሞበታል ።[28] አመልካቾች ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበሩና ፡ የማኅበሩ ፡ ሦስት ፡ አባሎች ፡ ነበሩ ። የአገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የማኅበሩን ፡ የገቢ ፡ ቀረጥ ፡ በሚገምትበት ፡ (በሚያ ሰብበት) ፡ ጊዜ ፡ ሦስቱን ፡ አባሎች ፡ የግል ፡ ባንክ ፡ ሂሳባቸውን ፡ የሚያሳይ ፡ መግ ለጫ ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ጠየቃቸው ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ የአገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መሥ ሪያ ፡ ቤት ፡ የሚገምተው ፡ የማኅበሩን ፡ ቀረጥ ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ የአገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ እንደዚህ ፡ ዐይነት ፡ ትእዛዝ ፡ ሊሰጥ ፡ አይችልም ፡ ብሎ ፡ ወሰነ ። "ማኅበሩ ፡ ከአባሎቹ ፡ ወይም ፡ ከባለአክሲዮኖቹ ፡ በግልጽ ፡ የተለየ ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ዓለው ፡ የሚለው ፡ ይጸናል ።"[29]

በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የሚባለው ፡ ዘይቤ ፡ ከንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ሌላ ፡ በብ ዙ ፡ ቦታዎች ፡ ይጠቅማል ። ለምሳሌም ፡ በመንግሥቱና ፡ በክፍሎቹ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተክርስቲያንና ፡ በማኅበሮች ፡ ላይ ፡ ይጸናል ።[30]

<u>በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የመሰጠት ፡ ጠባዮች</u> ። የሚከተሉት ፡ ጽሑፎች ፡ የን ግድ ፡ ማኅበሮችን ፡ የሚመለከቱ ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የመሰጠት ፡ ጠባዮችን ፡ ይተነትናሉ ። የንግድ ፡ ማኅበሮችን ፡ የሚመለከት ፡ ማንኛውም ፡ ጉዳይ ፡ የእሽሙር ፡ ማኅበሮችን ፡ አይመለከትም ፡ ምክንያቱም ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ ስለሌላቸው ፡ ነው ።

<u>ችሎታ</u> ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሊኖረውና ፡ ሊሠራበት ፡ ይችላል ፡ ተብሎ ፡ በሕጉ ፡ የሚሠጠው ፡ መብት ፡ የሰውየው ፡ ችሎታ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ("መብት ፡" በዚህ ፡ አግ ባብ ፡ መሠረት ፡ ተቃራኒው ፡ የሆነውን ፡ ግዴታንም ፡ ይጨምራል) ። ሕጉ ፡ መብቶ ችን ፡ ሲከለክለው ፡ ወይም ፡ በመብቶቹ ፡ ራሱ ፡ እንዳይጠቀምባቸው ፡ ሲያደርግ ፡ ችሎታ ፡ የለውም ፡ ይባላል ።

በመብቶች ፡ መኖርና ፡ በመብቶች ፡ መጠቀም ፡ መሐከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ መታወቅ ፡ አለበት ። በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ ስለአለው ፡ ነገር ፡ በምንናገርበት ፡ ጊዜ ፡ የምንመለከተው ፡ ስለመብቶች ፡ መኖር ፡ ብቻ ፡ ነው ። በተፈጥሮው ፡ ከሚኖ ረው ፡ አቋም ፡ የተነሣ ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ድርጅት ፡ መብቶቹን ፡ እራሱ ፡ ሊጠቀምባቸው ፡ አይችልም ፤ ሊሠራባቸው ፡ የሚችለው ፡ በእንደራሴዎቹ ፡ አማካኝነት ፡ ነው ።

---

28. የአዲስ ፡ አበባ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ ፭፻፷፮/፶፫ ፡ (ያል ታተመ) ። ክሱ ፡ የተነሣው ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ከመዋሉ ፡ በፊት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፤ የፍ ርድ ፡ ቤቱ ፡ ምክንያቶች ፡ በሕጉ ፤ መሠረት ፡ በተቋቋሙ ፡ ድርጅቶችም ፡ ላይ ፡ ይጸናል ።

29. በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ መስጠት ፡ በሕግ ፡ የተፈጠረ ፡ ነገር ፡ ስለሆነ ፡ በአንዳንድ ፡ ሁኔታዎች ፤ በተ ለይም ፡ ተንኰልን ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ሕጋዊ ፡ ያልሆኑ ፡ ሥራዎችን ፡ ለመሥሪያ ፡ በሚጠቀሙበት ፡ ጊዜ ፤ ሕጉ ፡ ሊረሳው ፡ ወይም ፡ ሊገሰው ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ማስታወስ ፡ ይገባል ።

30. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፺፬—፬፻፫ ፤ ፬፻፶፩—፬፻፶፰ ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የተለያዩ ፡ ስሞችን ፡ ይጠቀማል ። ለምሳሌም ። "Body corporate" "Juridical person" "aritificial person" or "Corporation" በጠቅላላው ፡ እነዚህን ፡ ቃላት ፡ በሚጠቀምበት ፡ ጊዜ ፡ አጠቃቀሙ ፡ የሚመለከተው ፡ ቡድን ፡ (ስብ ሳቢ) ፤ በሕጉ ፤ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ እንዳሉት ፡ ሰው ፡ ይቆጠራል ።

ችሎታ ፡ ማጣት ፡ ጉዳይ ፡ የሚሆነው ፡ ከሚከተሉት ፡ ሁለት ፡ ምክንያቶች ፡ ለአንዱ ፡ ነው ። እንደ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ልጆች ፤ እንደ ፡ አእምሮአቸው ፡ የጐደለ ፡ ሰዎችና ፤ እንደ ፡ ድውዮች ፡ ያሉትን ፡ ከራሳቸው ፡ ስህተት ፡ ለመከላከልና ፡ ማሕበራዊ ፡ ኑሮን ፡ በአካባቢው ፡ ከሚጠረጠሩ ፡ ወይም ፡ ከማይታመኑ ፡ ወንጀለኞች ፤ በሕግ ፡ ከተከለከሉና ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋዎች ፡ ለመከላከል ፡ ነው ።[31]

በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፻፺፪ ፡ መሠረት ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ "ችሎታ ፡ የሌለው ፡ መሆኑ ፡ በሕግ ፡ ተወስኖ ፡ ካልተገለጸ ፡ በቀር ፡ ማንኛውንም ፡ ዓይነት ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮን ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ ችሎታ ፡ አለው ።" ቁጥር ፡ ፻፺፫ ትም ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ድርጅት ፡ ችሎታ ፡ የሚመራው ፡ በዚሁ ድርጅት ፡ ላይ ፡ ሊጸኑ ፡ በሚችሉ ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ያክልበታል ።

የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፳፪ ፡ የንግድ ፡ ማኅበርን ፡ በሕግ ፡ ተለይተው ፡ የተከለከሉ ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ መወዳደር ፡ እንዳይደረጉ ፡ የተደረጉ ፡ የስምምነት ፡ ውሎች ፡ እንደተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ስለንግድ ፡ በወጡ ፡ ሕጋዊ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ያሉበትን ፡ ግዴታዎች ፡ እየፈጸመ ፡ "ማናቸውንም ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት" ፡ ያስችለዋል።[32] ነገር ግን ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ በጠቅላላ ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ የመሰማራት ፡ ችሎታ (ንግድ ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭ ፡ ከተዘረዘሩት ፡ ሥራዎች ፡ አንዱ ፡ ብቻ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን) ፤ ስለ ፡ ውል ፡ መፈጸምና ፡ ስለ ፡ ሌላም ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ተግባሮችን ፡ የመሥራት ፡ ችሎታ ፡ የሚናገር ፡ ሕግ ፡ የለም ።

በእንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ሁኔታ ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ የሚሠራው ፡ (የሚጸናው) ፡ አጠቃላይ ፡ ደንብ ፡ በንግድ ፡ ማኅበሮችም ፡ ላይ ፡ እንዲሠራ ፡ መደረግ ፡ አለበት ። የንግድ ፡ ማኅበር ፡ በሕግ ፡ እስከአልተከለከለ ፡ ድረስ ፡ ማናቸውንም ፡ ከተፈጥሮ ፡ ጋር ፡ የማይቃረኑ ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ተግባሮችን ፡ የመሥራት ፡ ችሎታ ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ። ተሰሚ ፡ (ምክንያታዊ) ፡ ደንብ ፡ ነው ፡ ምክንያቱም ፡ የችሎታ ፡ መኖር ፡ ከዚህ ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነው ፡ በልዩ ፡ ሕጎች ፡ ወይም ፡ ማኅበሩን ፡ በመመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ በተጸፈው ፡ መሠረት ፡ እንዲወሰን ፡ ከተደረገ ፡ አጠራጣሪ ፡ ሁኔታዎችን ፡ በመፍጠር ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንዲቀር ፡ ያደርጋል ። ልዩ ፡ የሆኑ ፡ የችሎታዎች ፡ አለመኖር ፡ እንዲኖሩ ፡ ከተፈለገ ፡ ለሰዎች ፡ እንደሚደረገው ፡ በሕግ ፡ ሊፈጠሩ ፡ ይችላሉ ። "ማኅበሩ ፡ ከዐይነቱ ፡ ጋር ፡ የሚስማሙትን ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ተግባሮችን ፡ ሁሉ ፡ መፈጸም ፡ ይችላል ።"[33]

---

31. በጠቅላላው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፻፺፪—፫፻፸፫ ፡ ተመልከት ።

32. በእንግሊዝኛው ፡ ቁጥር ፡ ፳፪ ፡ የሚገኘው ፡ "በሕግ ፡ ተለይተው ፡ የተከለከሉ ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ መወዳደር ፡ እንዳይደረግ ፡ የተደረጉ ፡ የስምምነት ፡ ውሎች ፡" የሚለው ፡ ሐረግ ፡ ትክክለኛ ፡ አይደለም ። የፈረንሳይኛውና ፡ የአማርኛው ፡ በሕግ ፡ ስለሚከለከሉና ፡ የንግድ ፡ ውድድርን ፡ ስለሚከለክሉ ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑ ፡ ስምምነቶች ፡ ይናገራሉ ። እንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ተገቢ ፡ ያልሆኑ ፡ የንግድ ፡ ውድድሮች ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩—፻፺፰ ፤ ፻፺፱ና ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፰፻፸፭—፩ሺ፰፻፺፯ ፡ ይመራሉ ።

33. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፶፬ ፡ (፩) ። ይህም ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ለንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ አጠቃላይ ፡ ደንብ ፡ ነው ። ፺ ፡ ሪፐርት ፡ ትሬይት ፡ ኤለመንታይሬ ፡ ደ ፡ ድሮዋ ፡ ኮሜርሺያል ፡ (፭ኛ ፡ እትም ፡ በአር ፡ ሮብሎት ፤ ፓሪስ ፤ ሊብሬሪ ፤ ፲፱፻፷፫—፲፱፻፷፬) ፡ ፩ኛ ፡ ቮልዩም ፤ ቁጥር ፡ ፭፻፩ ። ስለተወሰኑ ፡ ደንብና ፡ ስለሚፈጥራቸው ፡ ችግሮች ፡ የ ፡ ፺ ፡ ኤስካራን ፡ "ሳም ፡ ኮምፓሪዝን ፡ ቢትዊን ፡ ዘ ፡ ኮምፓኒስ ፡ አክት ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ኤንድ ፡ ዘ ፡ ፍሬንች ፡ ሎው ፡ ኦፍ ፡ ኮምፓኒስ ፤" ካምብሪጅ ፡ ሎው ፡ ጆርናል ። ፲፩ኛ ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፶፫) ፡ ገጽ ፡ ፩፻፲ ፤ ትልቋ ፡ ብሪታንያ ፤ ቦርድ ፡ ኦፍ ፡ ትሬድ ፤ ሪፖርት ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ካምፓኒ ፡ ሎው ፡ ኮሚቴ ፡ (Comnd 1749) ፡ (ሎንዶን ፤ ኤች ፡ ኤም ፡ ኤስ ፡ ኦ ፡ (Hmso) ፤ ፲፱፻፷፪) ፤ ገጽ ፡ ፲—፲፫ ፡ ተመልከት ። የጋናን ፡ ኮሚሽን ፡ ኦፍ ፡ ኤንኳየሪ ፡ ኢንቱ ፡ ዘ ፡ ወርኪንግ ፡ አድሚኒስትሬሽን ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ፕረዘንት ፡ ካምፓኒ ፡ ሎው ፡ ኦፍ ፡ ጋና ፤ ፋይናል ፡ ሪፖርት ፡ (አክራ ፤ የመንግሥት ፡ ማተሚያ ፤ ፲፱፻፷፩) ፤ ገጽ ፡ ፴፮ ፤ ፵፩ ፤ ፶፱ ።

ይህ ፡ አጠቃላይ ፡ ደንብ ፡ ነው ፡ ከተባለ ፡ የማኅበሩ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሁኔታ፡ ከሚያግደው ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ከሚከለከለው ፡ ሁኔታ ፡ ካልሆን ፡ በቀር ፡ የንግድ ፡ ማኅበር፡ ውሎችን ፡ ለመፈጸም ፤ ለመክሰስ ፡ ወይም ፡ ለመከሰስ ፤ ስጦታዎችን ፡ ለመቀበልና ፡ ማናቸውንም ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ተግባሮችን ፡ ለማከናወን ፡ ችሎታ ፡ አለው ፡ ማለት፡ ነው ።

የንግድ ፡ ማኅበር ፡ እንደማንኛውም ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ድርጅት ፤ ሰው ፤ ሰብአዊ ፡ ፍጡር ፡ በመሆኑ ፤ ሊያደርጋቸው ፡ የሚችላቸውን ፡ ነገሮች ፡ ሊያደርግ ፡ አይችልም ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ አለመድረስ ፤ የአእምሮ ፡ ጉድለትና ፤ ድውይነት ፡ በመሳሰሉ ፡ ሰዎችን ፡ የማይችሉ ፡ በሚያደርጓቸው ፡ በሰዎች ፡ ጠባዮች ፡ አይመራም ።

**<u>መብቶችና ፡ ግዴታዎች</u>** ፡ ብዙዎቹ ፡ ጠባዮች ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ድርጅት ፡ ከአለው ፡ መብቶች ፡ ጋር ፡ በቀጥታ ፡ የተያያዙ ፡ ናቸው ። እነዚህም ፤ በተለይ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮችን ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የሚከተሉትን ፡ ይጨምራሉ ።[34]

ሀ፣ ማኅበሩ ፡ መክሰስ ፡ ወይም ፡ መከሰስ ፡ ይችላል ።

ለ/ አባሎች ፡ የግል ፡ ዕዳቸውን ፡ እንዲከፍሉ ፡ የሚሰጡ ፡ ፍርዶች ፡ የማኅበሩን ንብረት ፡ አይመለከቱም ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ንብረቱ ፡ በማኅበርተኛው ፡ ለማኅበሩ ፡ በመዋጮ ፡ መልክ ፡ ቢገባም ፡ ማኅበርተኛ ፡ በሆነ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ የሚያገኝ ፡ ባለገንዘብ ፡ ፍርዱን ፡ በማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ሊያስፈጽመው ፡ አይችልም ። ማኅበርተኛው ፡ በእንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የግልም ፡ ሆነ ፡ ያልተከፋፈለ ፡ የባለቤትነት ፡ መብት ፡ የለውም ። ነገር ፡ ግን ፡ የግል ፡ ባለገንዘብ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ማኅበርተኛው ፡ በማኅበርተኛነቱ ፡ በሚያገኘው ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ ክሱን ፡ ሊመሠርት ፡ ይችላል ። ባለገንዘብ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ቢያገኝ ፡ የማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ በሆነ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ፍርዱን ፡ ሊያስፈጽም ፡ ይችላል ። ከእያንዳንዱ ፡ ማኅበርተኛ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ሊጠይቅ ፡ የሚችለው ፡ ማኅበርተኛው ፡ ለማኅበሩ ፡ ዕዳዎች ፡ ያለበት ፡ አላፊነት ፡ ያልተወሰነ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ባለገንዘቡም ፡ ፍርዱን ፡ ከማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ እንዲያስፈጽም ፡ ሊገደድ ፡ ይችላል ።

ሐ) ማኅበሩ ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ዕዳና ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በእያንዳንዱ ፡ ማኅበርተኛ ፡ ላይ ፡ ባላቸው ፡ ዕዳ ፡ (ወይም ፡ በተዘዋዋሪው ፡ መንገድ) ፡ መሐከል ፡ ማቻቻል ፡ አይደረግም ።

መ) ማኅበርተኛ ፡ በሚሞትበት ፡ ጊዜ ፡ ወራሾቹ ፡ የማኅበሩ ፡ በሆነው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የባለቤትነት ፡ መብትን ፡ ሊወርሱ ፡ አይችሉም ። የወራሾቹ ፡ መብቶች ፡ ሟቹ ፡ በማኅበርተኝነቱ ፡ ያገኘው ፡ በነበረው ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ። በማኅበሩ ፡ ዓይነት ፡ ወይም ፡ በመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ በተደነገጉት ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ የማኅበርተኝነት ፡ ጥቅሙን ፡ ወይም ፡ ዋጋውን ፡ ለመውረስ ፡ ይችላሉ ። በማኅበርተኛው ፡ መሞት ፡ ምክንያት ፡ ማኅበሩ ፡ ቢፈርስ ፡ እንኳ ፡ ወራሾቹ ፡ ንብረቱን ፡ ሊወርሱ ፡ አይችሉም ። ማኅበሩ ፡ የፈረሰው ፡ ሟቹ ፡ በሕይወት ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ እንደሆነ ፡ ተቆጥሮ ፡ የሟቹን ፡ ድርሻ ፡ ዋጋ ፡ ይከፈላቸዋል ። የዚህም ፡ መደበኛ ፡ ውጤት ፡ በሕጉ፡ ወይም ፡ በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ከተሰጠ ፡ ማኅበርተኞቹ ፡ ቢሞቱ ፡ እንኳ ፡ ማኅበሩ ፡ "በሕይወት ፡" ሊኖር ፡ ይችላል ።

---

34. በማስታወሻ ፡ ፴፫ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ፲ ፡ ሬፐርቶን ፡ ቁጥር ፡ ፺፫፻፸፱ን ፡ ተመልከት ።

ሠ) የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ሊከስር ፡ ወይም ፡ የመጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ እንዲኖረው ፡ ማድረግ ፡ ይችላል ።[35]

ረ) የንግድ ፡ ማኅበር ፡ በንብረቱ ፤ በገቢውና ፡ ቀረጥ ፡ በሚከፈልባቸው ፡ ሥራዎቹ ፡ በሙሉ ፡ ቀረጥ ፡ የመክፈል ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

ስለ ፡ እንደራሴነትና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ግዴታዎች ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ድርጅት ፡ ሥራዎችን ፡ እራሱ ፡ ለማከናወን ፡ ስለማይችል ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፪ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ "ማኅበር ፡ ስለ ፡ እንደራሴነት ፡ በተወሰነው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ እንደራሴ ፡ ያደረጋቸው ፡ ሰዎች ፡ ስለማኅበሩ ፡ ሆነው ፡ ለሠሩት ፡ ሥራ ፡ ባለመብትና ፡ ባለዕዳ ፡ ይሆናል ።" የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፱ ፡ አጠቃላይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ እንደራሴነት ፡ ደንቦችን ፡ ይዞአል ። የንግድ ፡ ማኅበሮችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ልዩ ፡ ደንቦች ፤ ስለእየአንዳንዱ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ በሚተነትነው ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ተሰጥተዋል ። እነዚህ ፡ ደንቦች ፡ በይበልጥ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ። እያንዳንዱ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ አጠቃላይ ፡ የሆነ ፡ ማኅበሩን ፡ የመወከል ፡ ሥልጣን ፡ ያሉዋቸው ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ የበለጡ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ አሉት ። በአክሲዮን ፡ ማኅበሮች ፡ የአስተዳደሩ ፡ ሥራ ፡ በአስተዳደር ፡ ምክር ፡ ቤቱና ፡ በዋናው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ የተከፋፈለ ፡ ነው ። የንግድ ፡ ማኅበሮችን ፡ በሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በግልጽ ፡ ወይም ፡ በሥውር ፡ ካልተለወጡ ፡ በተቀር ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፴፭—፷፱ ፡ ስለንግድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ፤ ስለነጋዴዎች ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፤ ስለንግድ ፡ ተላላኪዎችና ፡ እንደራሴዎች ፤ ስለ ፡ ንግድ ፡ ወኪሎች ፤ ስለደላሎችና ፡ ስለኮሚሲዮኖች ፡ የተዘረዘሩት ፡ ልዩ ፡ ደንቦች ፡ በንግድ ፡ ማኅበሮችም ፡ ላይ ፡ ይጸናሉ ።[36]

በጠቅላላው ፡ በእንደራሴነት ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ እንደራሴው ፡ ከወኪልነት ፡ ሥልጣኑ ፡ ሳያልፍ በንግድ ፡ ማህበሩ ፡ ስም ፡ ለሚፈጽማቸው ፡ ውሎች ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ተግባሮች ፡ ማኅበሩ ፡ ተጠያቂ ፡ ይሆናል ።[37] በአንዳንድ ፡ ሌሎች ፡ ሁኔታዎችም ፡ ተጠያቂ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ለምሳሌ ፡ የተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ማኅበሩን ፡ የሚጠቅም ፡ ሥራ ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ ቢሠራ ፡ ለተሠራው ሥራ ፡ ማኅበሩ ፡ ተጠያቂ ፡ ይሆናል ።[38]

ከማኅበሩ ፡ እንደራሴዎች ፡ ወይም ፡ ሠራተኞች ፡ አንዱ ፡ ሥራውን ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ አላፊነት ፡ የሚያስከትል ፡ ጥፋት ፡ የሠራ ፡ እንደሆን ፡ ማኅበሩ ፡ ከውል፡ ውጭ ፡ በሚደርሱ ፡ አላፊነቶች ፡ ይመራል ። በእንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ሁኔታ ፡ ማኅበሩና ፡ እንደራሴው ፡ ወይም ፡ ሠራተኛው ፡ ያልተከፋፈለና ፡ በአንድነት ፡ የሚወስዱት ፡ አላፊነት ፡ ይኖርባቸዋል ።[39] ጥፋት ፡ ሠሪው ፡ በማኅበሩ ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ያልሆነ ፡ እን

35. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፰ ፡ (፩) ። ነገር ፡ ግን ፡ ከላይ ፡ በቁጥር ፡ ፳፫ ፡ የተሰጠውን ፡ ማስታወሻና ፡ አብሮት ፡ ያለውን ፡ ጽሑፍ ፡ ተመልከት ።

36. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ።

37. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፯ ፡ (፩) ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፳፪፻፹፱ ፡ (፩) ። የደ.ብሊው ፡ ቾርችን ፡ "ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንደራሴነት ፡ ሕግ ፡ ማብራሪያ ፡" የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፫ኛ ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፶፰) ፤ ገጽ ፡ ፫፻፫ ፡ ተመልከት ።

38. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፯ ፡ (፪) ።

39. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፳፻፲፫ ፡ (፪) ፡ "ያልተከፋፈለ ፡ አላፊነት" ፡ ይላል ። የፈረንሣይኛውና ፡ የአማርኛው ፡ "ያልተከፋፈለና ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ የእርስ ፡ በርስ ፡ አላፊነት" ፡ በማለት ፡ በይበልጥ ፡ ትክክለኛ ፡ የሆነ ፡ ትርጉም ፡ ይሰጠዋል ። ልዩነቱና ፡ ጥቅሙ ፡ በማስታወሻ ፡ ፴፮ ፡ በተጠቀሰው ፡ ደብሊው ፡ ቾርች ፡ ገጽ ፡ ፫፻፲፫ ፡ ተገልጧል ።

ዶሆን ፡ ወይም ፡ እራሱን ፣ የቻለ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ የሚገመት ፣ ከሆነ ፣ ማኅበሩ ፣ አላፊ፣ አይሆንም ። አላፊነት ፣ የሚያስከትለው ፡ ጥፋት ፡ የተሠራው ፡ ሥራ ፡ በሚሠራበት ፡ በታ ፡ ወይም ፣ ጊዜ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፣ ሊታመን ፡ (ሊገመት) ፣ የሚቻለው ፡ እንደራሲው ፡ ወይም ፡ ሠራተኛው ፡ እንደደንቡ ፡ በሚሠራበት ፡ ቦታና ፡ ጊዜ ፣ የተሠራ ፣ እንደሆነ ፡ ነው ። ይህ ፡ ግምት ፡ ወይም ፡ እምነት ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ማስረጃ ፣ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ሊሻር ፣ የሚቻል ፡ ነው ።[40]

<u>የወንጀል ፡ አላፊነት</u> ፣ በሕግ ፣ የሰው ፣ መብት ፣ የተሰጠው ፡ ድርጅትን ፡ በወንጀል፡ አላፊ ፡ የሚያደርገው ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ድንጋጌ ፣ ባለመኖሩ ፣ በሕግ ፡ የሰው ፣ መብት ፣ የተ ሰጠው ፡ ድርጅት ፡ በወንጀል ፡ አላፊ ፡ መሆን ፡ ወይም ፣ አለመሆኑ ፡ በግልጽ ፣ የታወቀ ፣ አይደለም ።[41] የአላፊነት ፡ ጥርጣሬ ፡ ቢያንስ ፡ ከአራት ፡ ምንጮች ፡ ሊመጣ ፡ ይችላል ። ፩) አእምሮ ፤ እግርና ፣ እጅ ፣ ስለሌለው ፣ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ድርጅት ፡ እንድን ፡ ድርጊት ፡ በሚፈጽምበት ፣ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሰው ፣ ወንጀል ፣ ሰርቶአል ፡ ለማለት ፡ የሚያበቁትን ፡ ዐውቆ ፡ ወይም ፡ በቸልተኝነት ፡ የማጥፋት ፡ ችሎታዎች ፡ ሊኖ ሩት ፣ አይችልም ።[42] ፪) እንደራሴዎቹ ፣ ወይም ፡ ሠራተኞቹ ፡ ለሚሠሩት ፡ ጥፋት ፡ በሕግ ፣ የሰው ፡ መብት ፣ የተሰጠውን ፡ ድርጅት ፣ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ አላፊ ፡ የሚያደር ገውን ፡ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ ቁጥር ፣ ፳፩፻፹፱ ፣ ዓይነት ፡ ድንጋጌ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የለም ። ፫) የወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፣ ፫፻፺፱ ፤ በቁጥር ፡ ፫፻፸፩-፫፻፺፰ ፡ የተጠቀሱት ፡ የኢኮኖሚ ፡ ወይም ፣ የንግድ ፡ ወንጀል ፡ በአ ንድ ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ላይ ፡ ከተፈጸመ ፡ ቅጣቱ ፣ የሚወሰነው ፡ ጥፋቱን ፡ (ወንጀሉን) ፣ በሠሩት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፤ እንደራሴዎች ፤ አባሎች ፤ አስተዳዳሪዎች፤ ተቆጣጣሪዎች ፤ ወይም ፣ የሂሳብ ፣ አጣሪዎች ፣ ላይ ፡ ነው ፡ ይላል ።[43] ፬) የሞት ፣ ወይም ነፃነትን ፡ የመገፈፍ ፡ (የሚያሳጣ) ፡ ዓይነት ፡ ቅጣት ፣ በሕግ ፣ የሰው ፣ መብት ፡ በተሰ ጣቸው ፣ ድርጅቶች ፡ ላይ ፡ ሊወሰን ፣ አይችልም ። ነገር ፡ ግን ፡ የገንዘብ ፣ ቅጣት ፡ በሕግ ፣ የሰው ፣ መብት ፣ በተሰጠው ፣ ድርጅት ፡ ላይ ፡ ሊወሰን ፣ <u>ይቻላል ።</u> አላፊነትን በሰዎች ፡ ብቻ ፡ መወሰን ፡ በግልጽ ፡ የሚታየውን ፤ የማኅበሩ ፣ መሣሪያዎች ፣ ወንጀል ፡ ለመፈጸሚያ ፡ የሚያገለግሉ ፡ መሆናቸውን ፣ ወይም ፣ ወንጀል ፣ በመሠራቱ ፣ የሚያገ ኙትን ፡ ጥቅም ፡ መዘንጋት ፡ ይሆናል ። ማኅበሩን ፡ መቅጣት ፣ ወንጀል ፣ እንዳይሠራ ፡ የማድረጊያ ፡ ጥሩ ፡ መንገድ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

ፍርድ ፣ ቤት ፣ ማንኛውንም ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮን ፡ ጸጥታ ፡ የሚያደፈርስ ፡ ወን ጀልን ፣ የፈጸመ ፣ ወይም ፣ እንዲፈጸም ፡ ያደረገ ፣ "መሥሪያ ፡ ቤትን ፣ ወይም ፡ ድር ጅትን" ፡ የመዝጊያ ፡ ወይም ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ እንዳይሠራ ፡ የማድረጊያ ፡ ትዕዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ይናገራል ።[44] ወንጀ

---

40. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፣ ፳፩፻፹፱—፳፩፻፺፱ ፤ ፳፩፻፺፮ ።

41. ፒ ፣ ግራቨን ፡ <u>ለኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፣ ሕግ ፣ መግቢያ</u> ፣ (አዲስ ፣ አበባ ፤ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፤ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፣ ፲፱፻፷፩) ፤ ገጽ ፡ ፶፰ ፣ ።

42. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ ቁጥር ፡ ፳፫ ፤ ፶፰ ፡

43. ይህ ፡ ደንብ ፡ በመተላለፍ ፣ ወንጀሎች ፡ ላይ ፣ ይጸናል ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ ቁጥር ፣ ፭፻፰ ።

44. የወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፡ ቁጥር ፣ ፻፷፯ ። በቁጥር ፡ ፻፷፰ ፣ ትዕዛዝ ፡ ሊሰጥባቸው ፣ የሚችሉ ፣ ወንጀ ሎች ፡ ወሰን ፡ ግልጽ ፣ አይደለም ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ቁጥር ፣ ፬፻፺፱ ፣ ዓይነት ፣ አንዳንድ ፣ ድንጋጌ ዎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፣ የሚውልበትን ፣ መንገድ ፡ በግልጽ ፣ ይናገራሉ ። እንደ ፣ ቁጥር ፣ ፫፻፷፬ ፣ ያሉ ፡ ሌሎች ፣ ደግሞ ፡ ቁጥር ፡ ፻፷፯ን ፣ ሳይጠቅስ ፡ የመዝጋትን ፡ ወይም ፣ ላልተወሰነ ፣ ጊዜ ፣ የመጻረዋን ፣ ቅጣት ፡ ይሰጣሉ ።

ለኛው ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በበለጠ ፡ ጽኑ ፡ እሥራት ፡ የተቀጣ ፡ እንደሆነ ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስና ፡ ንብረቱም ፡ እንዲጣራ ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።[45] በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፡ በተግባር ፡ ላይ ፡ ስለሚሰማሩና ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችም ፡ ስለአሉዋቸው ፡ እነዚህ ፡ ውሳኔዎች ፡ አላፊነትን ፡ ይጥሉባቸዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፡ ስለአለባቸው ፡ አላፊነት ፡ ያለውን ፡ ችግር ፡ በሙሉ ፡ አያቃልሉም ። አንደኛ ፡ ነገር ፡ እነዚህ ፡ ውሳኔዎች ፡ የሚያስቡት ፡ ሰውም ፡ አላፊ ፡ የሚሆንባቸውን ፡ ወንጀሎችን ፡ ነው ። ቁጥር ፡ ፩፻፶፯ ፡ በአጥፊው ፡ (በወንጀለኛው) ፡ ከተወሰነበት ፡ ቅጣት ፡ ጋራ ፡ በተጨማሪ ፡ አብሮ ፡ የሚጸና ፡ መሆኑን ፡ በግልጽ ፡ ይናገራል ። ሁለተኛ ፡ ድርጅቱን ፡ የሚያዘጋ ፡ ትዕዛዝ ፡ የሚሰጠው ፡ የሕዝቡን ፡ ጸጥታ ፡ የሚያደፈርስ ፡ ወንጀል ፡ የተፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ። በመጨረሻም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በጊዜና ፡ በቦታ ፡ የተወሰነ ፡ ቢሆንም ፡ በቁጥር ፡ ፩፻፶፯ ፡ የተሰጠው ፡ መፍትሔ ፡ ኃይለኛ ፡ (አደገኛ) ፡ ነው ። በብዙ ፡ ሁኔታዎች ፡ ገንዘብ ፡ በይበልጥ ፡ ጥሩ ፡ ቅጣት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

ጉዳዩ ፡ በአጠቃላይ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፤ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ድርጅት ፡ ወንጀል ፡ ፈጽሞአል ፡ የሚባለው ፡ ወንጀል ፡ መፈጸሙ ፡ በግልጽ ፡ የተሰጠ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ የሚያደርግ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌ ፡ ብቻ ፡ ነው ።[46] የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፳፯ ፡ የሰውን ፡ ክብር ፡ ወይም ፡ መልካም ፡ ዝና ፡ በማጥፋት ፡ ወንጀልን ፡ ቢፈጽም ፡ በገንዘብ ፡ እንዲቀጣ ፡ ያዛል ። የድርጅቱ ፡ መዘጋት ፡ ወይም ፡ መፍረስ ፡ በቁጥር ፡ ፩፻፶፯ ፡ መሠረት ፡ ሊታዘዝ ፡ ይቻላል ። ወንጀሉን ፡ የፈጸሙ ፡ ሹማምንት ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ የተፈጥሮ ፡ ሰዎች ፡ በተጨማሪ፡ ሊቀጡ ፡ ይችላሉ ።

ስም ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ድርጅት ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ስም ፡ ይኖረዋል ። በሕግ ፡ የሚገደዱ ፡ ነገሮች ፡ ከሌሉ ፡ በስተቀር ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ስም ፡ በአባሎች ፡ ይመረጣል ። የተራ ፡ ሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሊኖረው ፡ የሚገባ ፡ የተለየ ፡ ተፈላጊ ፡ ስም ፡ የለም ። የሌሎች ፡ የማናቸውም ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ስም ፡ እንደ ፡ "የኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር" ፤ "የአክሲዮን ፡ ማኅበር" ፡ወዘተ ፡ የመሳሰሉ ፡ የማኅበሩን ፡ ዓይነት ፡ የሚገልጹ ፡ ምልክቶች ፡ መኖር ፡ አለባቸው ። በተጨማሪም የሕብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ስም ፡ ቢያንስ ፡ የሁለት ፡ አባሎችን ፡ ስም ፡ መጨመር ፡ አለበት ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ኃላፊነት ፡ ያለበት ፡ ማኅበር ፡ ስም ፡ ሊጨምር ፡ የሚችለው ፡ ኃላፊነታቸው ፡ ያልተወሰነ ፡ አባሎችን ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ነው ። የአክሲዮን ፡ ማኅበርና ፡ ኃላፊነቱ ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ ስሞች ፡ እንደተፈለገው ፡ ሊመረጡ ፡ ይችላሉ ። ለምሳሌ ፡ ያህልም ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ የማኅበርተኞችን ፡ ስም ፡ ጨምሮ ፡ አንድ ፡ ማንኛውንም ፡ በሕሊና ፡ የሚታሰብ ፡ ቃል ፤ የማኅበሩን ፡ ዓላማ ፡ የሚያሳይ ፤ ወይም ፡ ከነዚህ ፡ ተውጣጥተው ፡ የተጣመሩ ፡ ስሞች ፡ ሊኖራቸው ፡ ይችላል ።[47]

ጠቅላላ ፡ ሁኖታን ፡ የሚቃረን ፡ ወይም ፡ የሦሥተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መብት ፡ የሚነካ ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ስም ፡ እንዳይመረጥ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፭ ፡ ይከለክላል ። እንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ልዩ ፡ ግዳጅ ፡ የተደነገገው ፡ እዚህ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

45. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፶፮—፩፻፶፰ ፡

46. ፒ ፡ ግራቨን ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ፶፭ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ገጽ ፡ ፶፰ ፡ ተመልከት ።

47. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፩ ፡ (፩) ፤ ፪፻፲፪ ፡ (፪) ፤ ፫፻፲፩ ፤ ፭፻፲፱ ።

ነገር ፡ ግን ፡ መመሪያው ፡ በእያንዳንዱ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፡ የሚጸና ፡ ይመስላል ። ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሕሊናን ፡ ወይም ፡ መልካም ፡ ጠባይን ፡ የሚቃወም ፡ ሥራ ፡ እን ዳይሠራ ፡ የሚከለክለው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፴ ፡ ስለ ፡ ጠቅላላ ፡ ፀጥ ታም ፡ ይናገራል ።

ልዩ ፡ ስለሆኑ ፡ የሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መብቶች ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ስም ፡ በመ ጠቀም ፡ ስለሚደረጉ ፡ ጥፋቶች ፡ የሚናገሩ ፡ ብዙ ፡ ድንጋጌዎች ፡ አሉ ። በጠቅላላው ፡ ደንበኞችን ፡ ለማወናበድ ፡ የሚችል ፡ የአንድ ፡ ተወዳዳሪ ፡ ንግድ ፡ ማኅበርን ፡ ወይም፡ ነጋዴን ፡ ስም ፡ ለሌላ ፡ ንግድ ፡ ማኅበር ፡ መምረጥ ፡ አይቻልም ። እንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ስም ፡ ከተመረጠ ፡ ያላግባብ ፡ መወዳደርን ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ ይጸናሉ ።[48] በዚህ ፡ አባባል ፡ መሠረት ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ስም ፤ "ነጋዴ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የንግድ ፡ መደብ ሩን ፡ ጥቅም ፡ የሚያስገኝበት ፡ ስምና ፡ የንግድ ፡ መደብሩንም ፡ ዓይነት ፡ ለይቶ ፡ ከሚ ያስረዳው ፡"[49] ነጋዴ ፡ ከሚነግድበት ፡ ስም ፡ ጋር ፡ ይመሳሰላል ።

አንድ ፡ ሰው ፡ "በይመስላል ፡ ከሚደርሰው ፡ መዘባረቅ ፡ የተነሣ ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ክብርና ፡ ገናናነት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርስ ፡ ግብ ፡ ወይም ፡ ውጤት ፡ የሚያስ ከትል ፡" ከሆነ ፡ የገዛ ፡ ስሙን ፡ ከሥራው ፡ ጋር ፡ ለተያያዘ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ሊጠ ቀምበት ፡ አይችልም ። ጥፋተኛው ፡ (ወንጀለኛው) ፡ ያለአግባብ ፡ በመወዳደር ፡ ወይም ፡ በስም ፡ አጥፊነት ፡ ሊከሰስ ፡ ይችላል ።[50] የንግድ ፡ ማኅበር ፡ የአንድን ፡ ሰው ፡ ስም ፡ መጠሪያ ፡ በማድረግ ፡ ሰውዬውን ፡ ሊጐዳው ፡ የሚችል ፡ ከሆነ ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነ ቱን ፡ ስም ፡ ሊገለገልበት ፡ (ሊወስድ) ፡ አይችልም ።

ዋና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ — የአንድ ፡ ሰው ፡ መደበኛ ፡ ቦታ ፡ በዚያ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ሊያስከትላቸው ፡ የሚችላቸው ፡ ዓይነት ፡ ውጤቶች ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰ ጠው ፡ ድርጅት ፡ ዋና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ያለበት ፡ ቦታም ፡ በድርጅቱ ፡ ላይ ፡ ያስከት ላቸዋል ። "ዋና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት" ፡ በሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ አልተተረጐ መም ። በፈረንሣይ ፡ ሕግ ፤ የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ የአስተዳደርና ፡ የሥራ ፡ ማካሄጃ ፡ ክፍሎች ፡ (ቅርንጫፎች) ፡ ያሉበት ፡ ቦታ ፡ ማለት ፡ ነው ።[52]

ዋና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ያለበት ፡ ቦታ ፤ በተለይም ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣንና ፡ መጥሪያን ፡ በሚመለከቱ ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፤ ጠቃሚ ፡ ይሆናል ።[53] ዜግነትንም ፡ በሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ።

ዜግነት ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፤ በተለይም ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፤ «የኢትዮጵያ ፡» ወይም ፡ "የውጭ" ፡ እየተባለ ፡ ሲጠራ ፡ ይሰማል ። በእንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡

---

48. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፻፴፫ ፡ (፪) ፡ (ሀ) ።
49. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፻፴፭ ፤ ፻፴፯(፪) ፤ ፻፴፰(፪) ። በተጨማሪም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርንና ፡ የወን ጀልን ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ ውድድርን ፡ የሚመለከቱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፶፰ና፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፹፫ን ፡ ተመልከት ።
50. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፺፩ ።
51. የፍትሐ - ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፵፯ ።
52. በማስታወሻ ፡ ፴፫ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ፯ ፡ ሪፖርት ፡ ቁጥር ፡ ፲፱፻፷፮ ፤ ሊ ፡ በክለር ፡ "ዘ ፡ ሶስዬቴ ፡ አኖኒም ፡ ኤንድ ፡ ዘ ፡ ሶሲዬቴ ፡ ሪስፖንሲቢሊቴ ፡ ሊሚቴ ፡ እን ፡ ፍራንስ ፡" ነው ፡ የርክ ፤ ዩኒቨርሳል ፡ ሎው ፡ ጆርናል ፡ ፴፰ ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፷፫) ፡ ገጽ ፡ ፩፻፶፱ ።
53. ለምሳሌ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፳፪ ፤ ፺፯ ፤ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፻፶፯ ፡ (፫) ፡ ተመልከት ፡ ።

ስለዜግነት ፡ ማውራት ፡ ትክክል ፡ አይደለም ፡ ምክንያቱም ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ድርጅት ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ከዜግነት ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ የታዛ ዥነት ፡ ስሜት ፡ ሊኖረው ፡ ስለማይችልና ፡ እንደ ፡ ድምፅ ፡ መስጠት ፡ ዓይነት ፡ የተ ወላጅነት ፡ መብቶች ፡ ስለሌለው ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ አንዳንድ ፡ ሕጎች ፡ "የውጭ ፡" ስለሆኑ ፡ ወይም ፡ "ዜግነት" ፡ ስለአላቸው ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ስለተሰጣ ቸው ፡ ድርጅቶች ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ይናገራሉ ። አንድ ፡ ማኅበር ፡ በአ ንድ ፡ መንገድ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ ከሆነ ፡ መብትና ፡ ግዴታ ዎቹ ፡ የተለዩ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ። የንግድ ፡ ማኅበርን ፡ አመሠራረትና ፡ ሥራውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሥራዎችን ፡ ለመሥራት ፡ ያለው ፡ መብትና ፡ ለኢትዮጵያው ያን ፡ ተወላጆች ፡ ብቻ ፡ የተሰጡ ፡ መብቶችን ፤ የሚመሩ ፡ (የሚመለከቱ) ፡ ሕጎች ፡ በተለይ ፡ ጠቃሚዎች ፡ ናቸው ።[54]

በመሠረቱ ፡ ዋና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የሆነ ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ድርጅት ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ ሕጎች ፡ የሚሰጠውን ፡ ዓይነት ፡ ዜግ ነት ፡ ይኖረዋል ።[55] ምንም ፡ እንኳ ፡ በግልጽ ፡ የሚናገር ፡ ሕግ ፡ ባይኖርም ፡ አንድ ፡ ዋና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሆነ ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰ ጠው ፡ ድርጅት ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የሆነ ፡ ዜግነት ፡ አለው ፡ የሚለው ፡ ይከተላል ። ይህ፡ አጠቃላይ ፡ የሆነ ፡ መመሪያ ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፡ በአጠቃላይ ፡ ሊኖራቸው ፡ በሚችሉ ፡ መብቶችና ፡ በተለይ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮችን ፡ አመሠራረትና ፡ የሥራ ፡ ሁኔታ በሚመለከቱ ፡ በሚጨበጡ ፡ ደንቦች ፡ ይወሰናል ።[56] ለማሳጠርም ፡ ያህል ፡ የንግድ ፡ ማኅበርን ፡ አመሠራረትና ፡ ሥራን ፤ በኢትዮጵያ ፡ ሊጠቀምባቸው ፡ ወይም ፡ ሊኖረው ፡ የሚገባው ፡ መብቶችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ሦስት ፡ ነገሮች ፡ ተወስደዋል ። እነዚህም ፡ ዋና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ ያለበት ፡ ሥፍራ ፤ የሥ ራው ፡ ዋና ፡ ጉዳይ ፡ ያለበት ፡ ቦታና ፤ በማን ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ እንደተቋቋመ ፡ ናቸው ። ዋና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሆነ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ አመ ሠራረቱና ፡ ሥራው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ነው ። ዋና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የሆነ ፡ ማኅበር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ሊመራ ፡ የሚችለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የተቋቋመ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ የሥራው ፡ ዋና ፡ ጉዳይ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።[57] ዋና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱና ፡ የሥራው ፡ ዋና ፡ ጉዳይ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የሆነ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ማኅበር ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በመዝገብ ፡ ገብቶ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቶቹን ፡ የሚመለከቱ ፡

54. ስለ ፡ ዜግነት ፡ አጭር ፡ ማብራሪያ ፡ ኤች ፡ ኤል ፡ ና ፡ ጂ ፡ ማዝኢዱ ፤ ሌሶንስ ፡ ደ ፡ ድሮዋ ፡ ሲቪል ፡ (፫ኛ ፡ እትም ፤ ፓሪስ ፤ ኤዲሽንስ ፡ ሞንቻሽሬስቲየን ፤ ፲፱፻፷፫) ፡ ፭ኛ ፡ ቮልዩም ፤ ቁጥር ፡ ፲፻፲፪ና ፤ ኢቸ ርቫ ፤ ቢዝነስ ፡ አሶስዬሽንስ ፡ አንደር ፡ ፍሬንች ፡ ሎው ፤ (ሎንዶን ፤ ስዊት ፡ ኤንድ ፡ ማክስዌል ፤ ፲፱፻፷፰) ፤ ቁጥር ፡ ፲፻፸፮ን ፡ ተመልከት ። ስለ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋዎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ አባል ፡ የመሆን ፡ ችሎታ ፡ ከታች ፡ የተጠቀሰውን ፡ ከ፩፻—፩፻፯ ፡ ያሉትን ፡ ማስታወሻዎችንና ፡ አብሮት ፡ ያለ ውን ፡ ጽሑፍ ፡ ተመልከት ።

55. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፸፯ ፡ (፪) ።

56. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፺፭—፩፻፺፱ ፤ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፶፩—፭፻፶፫ ። እነዚሁ ፡ አንቀጾች ፡ በጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ከሚገኙ ፡ አጭር ፡ መግለጫዎች ፡ ይበልጥ ፡ የተብራሩ ፡ ናቸው ።

57. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፻፲፩ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ትርጉሜ ፡ በውጭ ፡ የሚገኙ ፡ ድርጅቶች ፡ ዋና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤታቸው ፡ ወይም ፡ ዋና ፡ የንግድ ፡ ሥፍራዎች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ከሆነ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ይመ ራሉ ፡ ይላል ። የአማርኛውና ፡ የፈረንሣይኛው ፡ ንግድ ፡ ሕግ ፡ ስለዋና ፡ የንግድ ፡ ዓላማ ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ቦታ ፡ (ሥፍራ) ፡ አያወሩም ። የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋዎች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኙት ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ማኅበርተኛ ፡ ለመሆን ፡ ስለአላቸው ፡ ችሎታ ፡ ከታች ፡ የተገለፀውን ፡ ከ፩፻—፩፻፯ ፡ ያለ ውን ፡ ማስታወሻና ፡ አብሮት ፡ ያለውን ፡ ጽሑፍ ፡ ተመልከት ።

ጉዳዮች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ይመራሉ ።[58] የንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሥራዎችን ፡ ስለማስመዝገብ ፡ በወጣ ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ "የተቋቋመ ፡ ወይም ፡ የሚኖር ፡ ከሆነ ፡" ዋና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ የትም ፡ ቢሆን ፡ "የውጭ ፡ ይባላል ።" እንደነዚህ ፡ ዓይነት ፡ ማኅበሮች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሥራ ፡ ከመጀመራቸው ፡ በፊት ፡ "ከአገር ፡ ውስጥ" ፡ ማኅበሮች ፡ ለየት ፡ ባለ ፡ መንገድ ፡ (ደንብ) ፡ በመዝገብ ፡ እንዲገቡ ፡ ይገደዳሉ ።[59] እላይ ፡ ከተጠቀሱት ፡ ነገሮች ፡ በተጨማሪ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ጥቅሞች ፡ መኖር ፤ (ለምሳሌ ፡ በአባልነት ፡ ወይም ፡ በሥራ ፡ አካሄድ) ፡ በተለዩ ፡ ሕጎች ፡ ሊወሰኑ ፡ ይችላሉ ።

<u>የተወሰነ ፡ ኃላፊነት</u> ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ በውል ፡ ወይም ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ለሚመጣ ፡ ግዴታ ፡ (ጥፋት) ፡ አላፊ ፡ ቢሆንና ፡ ማኅበሩ ፡ ግዴታውን ፡ ለመፈጸሚያ ፡ በቂ ፡ ገንዘብ ፡ ባይኖረውስ ፡ አባሎቹ ፡ እንዲፈጽሙት ፡ ማድረግ ፡ ይቻላልን?

በአንዳንድ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ማኅበሩ ፡ ያለበትን ፡ ዕዳ ፡ ሊከፍል ፡ የማይችል ፡ ከሆነ ፡ አባሎቹ ፡ የማኅበሩን ፡ ዕዳ ፡ እንዲከፍሉ ፡ ተጠያቂ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ። ይህም ፡ ለኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ አባሎች ፤ አላፊነታቸው ፡የተወሰነ ፡የሁለት ፡ ዓይነት ፡ አላፊነት ፡ የአለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ አባሎችና ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ (ሁልጊዜ ፡ ሳይሆን) ፡ በተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ በሙሉ ፡ በርግጥ ፡ ይሠራል ። በሌሎች ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ማኅበርተኞች ፡ አላፊ ፡ አይደሉም ። ባለገንዘቦች ፡ ማኅበሩን ፡ ሊከሱና ፡ ከማኅበሩ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ቋሚ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ እንዲከፈላቸው ፡ መጠየቅ ፡ ይችላሉ ። በማኅበርተኞች ፡ ሳይከፈል ፡ የቀረ ፡ መዋጮ ፡ ቢኖር ፡ እንዲከፍሉ ፡ ሊገደዱ ፡ ይችላሉ ። ከዚያ ፡ በላይ ፡ ግን ፡ ሊጠየቁ ፡ አይችሉም ። ለማኅበሩ ፡ ዕዳ ፡ የማኅበርተኞቹ ፡ አላፊነት ፡ ለማኅበሩ ፡ ባገቡት ፡ መዋጮ ፡ መጠን ፡ የተወሰነ ፡ ነው ። የነዚህም ፡ አላፊነት ፡ የተወሰነ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ይህም ፡ ለጠቅላላ ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኞች ፤ ኃላፊነቱ ፡ ለተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኞችና ፡ አላፊነታቸው ፡ ለተወሰነ ፡ የሁለት ፡ ዓይነት ፡ አላፊነት ፡ የአለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኞች ፡ በርግጥ ፡ ይሠራል ።

የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ለነጋዴ ፡ ጥሩ ፡ ጥቅም ፡ ነው ፡ (አለው) ። ማኅበሩ ፡ ቢከስር ፡ የግል ፡ ንብረቱን ፡ በሙሉ ፡ አጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ሳይሰጋ ፡ ሥራውን ፡ ሊሠራ ፡ ይችላል ። በእንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ሁኔታ ፡ ሰውየው ፡ የሚያጣው ፡ ለማኅበሩ ፡ ያደረገውን ፡ መዋጮ ፡

---

58. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፲፱፻፵፭—፲፱፻፵፱ ፡ ዋና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤታቸው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የሆኑ ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ማናቸውንም ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ከመጀመራቸው ፡ በፊት ፡ ከአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ፈቃድ ፡ እንዲኖራቸው ፡ ያስገድዳል ። እንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ፈቃድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከተገኘ ፡ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ድርጅቱ ፡ ለሚሠራቸው ፡ ሥራዎች ፡ ሊወስን ፡ ከመቻሉና ፡ በመንግሥት ፡ ትዕዛዝ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ ለመሆን ፡ ካለመቻሉ ፡ በቀር ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ዜጋ ፡ ተቆጥሮ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ (የማኅበራዊ ፡ ኑሮ) ፡ መብቶች ፡ በሙሉ ፡ ይኖሩታል ። እነዚህ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ መጽናታቸውና ፡ አለመጽናታቸው ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ። የንግድ ፡ ማኅበሮችም ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፡ ናቸው ። በንግድ ፡ ሕግም ፡ ውስጥ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብት ፡ ስለመሆናቸው ፡ የሚናገር ፡ ምንም ፡ ድንጋጌ ፡ የለም ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፱፻፭ ፡ (፩) ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ በጠቅላላው ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ይመራሉ ፡ ይላል ። ይህም ፡ ስለእንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ መጽደቅ ፡ አይናገርም ። በተጨማሪም ፡ በንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሥራዎችን ፡ ስለማስመዝገብ ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፤ (ከታች ፡ ያለውን ፡ ማስታወሻ ፡ ፶፱ ፡ ተመልከት) ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱፻፶፪ ፤ ፲፱፻፶፱ ፡ መሠረት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ የሆኑ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ በንግድና ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ እንዲመዘገቡ ፡ (በመዝገብ ፡ እንዲገቡ) ፡ ይገደዳሉ ።

59. ቁጥር ፡ ፲ ፡ (፩) ፤ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፻፹፬ ፤ ፲፱፻፶፬ ፤ <u>ነጋሪት ፡ ጋዜጣ</u> ፡ ፳፩ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፫ ።

ብቻ ፡ ነው ። መዋጮ ፡ የሚያደርጉ ፡ አዲስ ፡ አባሎችንም ፡ በማግኘት ፡ ሥራውን ፡ ለማካሄጃ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲያገኝ ፡ ያደርገዋል ። እንደነዚህ ፡ ዐይነት ፡ አዲስ ፡ ማኅበርተኞች ፡ ለማኅበሩ ፡ ዕዳ ፡ ኃላፊ ፡ ይሆናሉ ፡ ከተባለ ፡ ገንዘባቸውን ፡ በእንደዚህ ፡ ዐይነት ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ፈቃደኛ ፡ ላይሆኑ ፡ ይችላሉ ።

የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ከሽርክና ፡ ማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ለሆኑ ፡ ሰዎች ፡ (ባለገንዘቦች) ፡ ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ አደገኛ ፡ ሁኔታዎችን ፡ ይይዛል ። እነዚህን ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ለመከላከል ፡ ሕጉ ፡ ብዙ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ይሰጣል ። አላፊነታቸው ፡ የተወሰነ ፡ ማኅበርተኞች ፡ የአሉዋቸው ፡ ማኅበሮች ፡ የተወሰነ ፡ አነስተኛ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ እንዲኖራቸው ፡ (የአክሲዮን ፡ ማኅበሮችና ፡ አላፊነታቸው ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበሮች) ፡ ወይም ፡ ቢያንስ ፡ የአንዱ ፡ ማኅበርተኛ ፡ አላፊነት ፡ ያልተወሰነ ፡ እንዲሆን ፡ ያስፈልጋል ፡ (ሁለት ፡ ዓይነት ፡ አላፊነት ፡ ያለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር) ፡ እንደ ፡ የማኅበሩን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ዋና ፡ ሀብት ፡ ለባለ ፡ አክሲዮኖች ፡ ሊከፋፈል ፡ የሚችልበትን ፡ መንገድ ፡ በሚወስኑ ፡ ከማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ሊጠይቁ ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎችን ፡ (ባለገንዘቦችን) ፡ በሚከላከሉ ፡ ዓይነት ፡ ብዙ ፡ ድንጋጌዎች ፤ የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ይመራል ። አላፊነቱ ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ አነስ ፡ ያሉ ፤ እንደዚህ ፡ ዓይነት ፤ ደንቦች ፡ አሉት ። ነገር ፡ ግን ፡ በአንድ ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ በሆኑ ፡ ማኅበርተኞች ፡ የግል ፡ ዋስትና ፡ ካልተሰጠ ፡ በስተቀር ፡ ዱቤ ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ።

ዋና ፡ ገንዘብ ፡ የሚባለው ፡ ዘይቤ ፡ በንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ በተለይም ፡ የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ በአለባቸው ፡ ማኅበሮች ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ። ክፍልፋዮቹ ፡ ውስብስብና ፡ ብዙ ፡ ገለጻ ፡ የሚያስፈልጋቸው ፡ ናቸው ። ቢሆንም ፡ አጭር ፡ መግለጫ ፡ ከዚህ ፡ ላይ ፡ መስጠት ፡ ተገቢ ፡ ነው ።[60]

የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፹፰ ፡ ዋና ፡ ገንዘብን ፡ (ካፒታልን) ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ይተረጉመዋል ። "ከባለቤቱ ፡ ወይም ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ በየድርሻቸው ፡ በገንዘብ ፡ ወይም ፡ በዐይነት ፡ ለጥቅም ፡ ማስገኛ ፡ ለንግድ ፡ ቤቱ ፡ የተሰጠው ፡ መሠረታዊ ፡ ሀብቱ ፡ ነው ።" እያንዳንዱ ፡ ማኅበርተኛ ፡ አንድ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ለማኅበሩ ፡ ማግባት ፡ አለበት ። ይህም ፡ ገንዘብ ፤ መሬት ፤ ግዙፍነት ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ የሌለው ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ለምሳሌም ፡ አምስት ፡ ሰዎች ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብን ፡ አዋጥተው ፡ የንግድ ፡ ማኅበርን ፡ ለማቋቋም ፡ ይፈልጋሉ ፡ እንበል ። አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ሰነዶች ፡ አውጥተው ፡ ተፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ምዝገባ ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ ገንዘቡን ፡ አገቡ ፡ (አስተላለፉ) ፡ እንበል ። ገንዘቡ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በማኅበሩ ፡ ስም ፡ በባንክ ፡ ሂሳብ ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣል ። እያንዳንዱ ፡ ማኅበርተኛ ፡ የአዋጣው ፡ ፲ሺ ፡ ብር ፡ ነው ፡ እንበል ። ማኅበሩ ፡ በተቋቋመበት ፡ ጊዜ ፡ በባንክ ፡ ውስጥ ፡ ፶ሺ ፡ ብር ፡ ይኖረዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ማለት ፡ ይህ ፡ ነው ።

አራት ፡ ሰዎች ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ቢያዋጡና ፡ አንዱ ፡ ፲ሺ ፡ ብር ፡ የሚያወጣ ፡ መሬት ፡ ቢያወጣስ ? ውጤቱ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ይሆናል ። የአባሎቹ ፡ ጠቅላላ ፡ መዋጮ ፡ ዋጋ ፡ ፶ሺ ፡ ብር ፡ ነው ። የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ፶ሺ ፡ ብር ፡ ነው ።

የዋና ፡ ገንዘብን ፡ ትርጓሜ ፡ አንዳንድ ፡ ክፍሎች ፡ መመልከት ፡ ያስፈልጋል ። አንደኛ ፡ ስለዋና ፡ ገንዘብ ፡ በምንናገርበት ፡ ጊዜ ፡ የምንናገረው ፡ ስለጥሬ ፡ ገንዘብ ፡

60. የዋና ፡ ገንዘብን ፡ ትርጓሜ ፡ ስለሚመለከተው ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ፵፫ ፡ የተጠቀሰውን ፤ ቁጥር ፡ ፷፻፲፰ ፡ ተመልከት ፤ ፯ ፡ ኤስካራ ፤ ኩር ፡ ደ ፡ ድሮዋ ፡ ኮሜርሺያል ፡ (ኑቬል ፡ ኤዲሽን ፤ ፓሪስ ፤ ሲሬይ ፤ ፲፱፻፶፱ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፲፬ ።

ወይም ፡ ንብረት ፡ ሳይሆን ፡ ስለዋጋው ፡ ነው ። የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ፶ሺ ፡ ብር ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ፶ሺ ፡ ብር ፡ የሚያወጣ ፡ መሬት ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ከብዙ ፡ ነገሮች ፡ የተውጣጡ ፡ ፶ሺ ፡ ብር ፡ ቢሆን ፡ አንድ ፡ ነው ። በተመሳሳይም ፡ መንገድ ፡ መጀመሪያ ፡ በማኅበርተኛ ፡ የተዋጣ ፡ ንብረት ፡ በማኅበሩ ፡ ቢሸጥ ፡ ምንም ፡ ልዩነት ፡ የለውም ። ዋና ፡ ገንዘቡ ፡ አንድ ፡ እንደሆነ ፡ ይቀራል ። ከላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ምሳሌ ፡ መሠረት ፶ሺ ፡ ብር ፡ ማለት ፡ ነው ። ሁለተኛ ፡ የዕቃው ፡ ወይም ፡ የንብረቱ ፡ ዋጋ ፡ ከፍና ፡ ዝቅ ፡ ሊል ፡ የሚችል ፡ ከሆነ ፡ የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ መዋጮው ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ በነበረው ፡ ዋጋ ፡ ይታሰባል ፡ (ታስቦ ፡ ይወሰናል) ። ይህም ፡ "የመጀመሪያ ፡ ዋጋ ፡" ይባላል ። ለምሳሌ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የተቋቋመ ፡ ማኅበርን ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ለማሰብ ፡ እንፈልጋለን ፡ እንበል ። ማኅበሩ ፡ በተቋቋመበት ፡ ጊዜ ፡ የመሬቱ ፡ ዋጋ ፡ ፲ሺ ፡ ብር ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ፲፪ሺ ፡ ብር ፡ ያወጣል ። የዋና ፡ ገንዘቡ ፡ ሂሳብ ፡ የሚደረገው ፡ በተዋጣበት ፡ ጊዜ ፡ በነበረው ፡ ዋጋ ፡ ፲ሺ ፡ ብር ፡ መሠረት ፡ ነው ። ሦስተኛ ፤ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ በሚታሰብበት ፡ ጊዜ ፡ የጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ የዓይነት ፡ መዋጮዎች ፡ (ንብረትና ፡ የገንዘብ ፡ መብት) ፡ (ዕዳዎች) ፡ የመሳሰሉት ፡ ብቻ ፡ ይወሰዳሉ ። በተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፤ በኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮችና ፡ በሁለት ፡ ዓይነት ፡ ኃላፊነት ፡ በአለባቸው ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፤ መዋጮዎች ፡ ለማኅበሩ ፡ በሚደረጉ ፡ የሙያ ፡ ሥራዎች ፡ ዓይነት ፡ ሊዋጡ ፡ ይችላሉ ።[61] ነገር ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነቶቹ ፡ የዋና ፡ ገንዘቡ ፡ ክፍል ፡ ሊሆኑ ፡ አይችሉም ። የዋና ፡ ገንዘቡ ፡ ክፍሎች ፡ የሚሆኑት ፡ የጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ የዓይነት ፡ መዋጮዎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው።

ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ከማኅበሩ ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ቋሚ ፡ ሀብቶች ፡ መለየት ፡ አለበት ። "ቋሚ ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ሀብቶች ፡" ማለት ፡ የጠቅላላው ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፤ ግዙፍነት ፡ ያላቸውና ፡ የሌላቸው ፡ ንብረቶችና ፡ ማኅበሩም ፡ በጠቅላላው ፡ "የአሉት ፡" መብቶች ፡ ዋጋ ፡ ነው ። (ቃሉ ፡ በይበልጥ ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፳፮–፩፻፳፱ ፡ በአሉት ፡ ተተርጉሟል) ። ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ከቋሚ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ሀብት ፡ ሊበልጥ ፡ ወይም ፡ ሊያንስ ፡ ይችላል ። አንድ ፡ ማኅበር ፡ በ፶ሺ ፡ ብር ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ይጀምራል ፡ እንበል ። የመጀመሪያው ፡ የማኅበሩ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ሀብት ፡ ይኸው ፡ ነው ፡ እንበል ። ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የማኅበሩ ፡ የተጣራ ፡ ትርፍ ፡ ፪ሺ ፡ ብር ፡ ነው ፡ እንበል ። ይህ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ ገንዘብ ፡ የተገዛው ፡ ንብረት ፡ የማኅበሩ ፡ ቋሚ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ሀብት ፡ ክፍል ፡ ይሆናል ። ይኸውም ፡ አሁን ፡ ፶፪ሺ ፡ ብር ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ገንዘብ ፡ የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ክፍል ፡ አይሆንም ። ምክንያቱም ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ የማኅበርተኞችን ፡ መዋጮ ፡ ዋጋ ፡ ብቻ ፡ የሚያሳይ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። ዋና ፡ ገንዘቡ ፶ሺ ፡ ብር ፡ እንደሆነ ፡ ይቀራል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የተጣራ ፡ ኪሣራ ፡ ፪ሺ ፡ ብር ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ቋሚ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ሀብቱ ፡ ፵፰ሺ ፡ ብር ፡ ብቻ ፡ ይሆን ፡ ነበር ። እንደገና ፡ ዋና ፡ ገንዘቡ ፡ ፶ሺ ፡ ብር ፡ እንደሆነ ፡ ይቀራል ።

የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ማኅበሩ ፡ በሚኖርበት ፡ ጊዜ ፡ በማኅበርተኞች ፡ ተጨማሪ ፡ መዋጮ ፡ ከፍ ፡ ሊል ፡ ይችላል ። በሌሎቹ ፡ ሁኔታዎች ፡ ደግሞ ፡ በተለያዩ ፡ መንገዶች ፡ ከፍ ፡ ወይም ፡ ዝቅ ፡ ሊል ፡ ይችላል ። ይህም ፡ በተለይ ፡ በዚሁ ፡ መስመር ፡ ልዩ ፡ ደንቦች ፡ ለተደነገጉላቸው ፡ ለአክሲዮን ፡ ማኅበሮች ፡ ጠቃሚ ፡ ይሆናል ።

የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ የማኅበሩ ፡ ዕዳዎች ፡ የሚከፈሉ ፡ ለመሆናቸው ፡ ዋስትና ፡ የሚሰጥ ፡ ሰነድ ፡ (መያዣ) ፡ እንደሆነ ፡ ይቆጠራል ። ይህን ፡ በግልጽ ፡ የሚናገር ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌ ፡ የለም ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ ከሁለት ፡ ዓይ

61. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፱ ፡ (፩) ፤ ፪፻፶፩ ፤ ፫፻፫ ።

ነት ፡ ደንቦች ፡ ላይ ፡ ይታያል ። አንደኛው ፡ ማኅበርተኞቹ ፡ ትርፍ ፡ ሳይኖር ፡ እንደ ፡
ትርፍ ፡ የሚቀበሉትን ፡ ድርሻ ፡ የሚከለክለው ፡ ነው ። በጠቅላላው ፡ አነጋገር ፡ ትርፍ
ሳይኖር ፡ እንደ ፡ ትርፍ ፡ የሚካፈል ፡ ድርሻ ፡ ማለት ፡ በማኅበሩ ፡ ለማኅበርተኞቹ ፡
የሚደረግ ፡ ከማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ የተገኘ ፡ ትርፍን ፡ የማይመለከት ፡ የገንዘብ ፡ ወይም ፡
የንብረት ፡ ክፍያ ፡ ማለት ፡ ነው ። ትርፍ ፡ ሳይገኝ ፡ እንደትርፍ ፡ የሚካፈል ፡ ድርሻ ፡
የተባለበትም ፡ ምክንያት ፡ የሚደረጉ ፡ ክፍያዎች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ከትርፍ ፡ ላይ ፡
ብቻ ፡ መከፈል ፡ ስለአለባቸው ፡ ነው ። ሁለተኛው ፡ ዓይነት ፡ ደንብ ፡ ደግሞ ፡ የማኅበሩ ፡
ባለገንዘቦችን ፡ ወይም ፡ ሂሳብ ፡ አጣሪዎችን ፡ በማኅበርተኞች ፡ ሳይከፈል ፡ የቀረ ፡
ማንኛውም ፡ መዋጮ ፡ እንዲከፈል ፡ የማስገደጃ ፡ ችሎታን ፡ የሚሰጥ ፡ ነው ።

ማንኛውም ፡ ለማኅበርተኞች ፡ የሚከፋፈል ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ ለባለ
ገንዘቦች ፡ የሚከፈለውን ፡ የማኅበሩን ፡ ቋሚ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ሀብት ፡ ይቀንስ
ዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሕጉ ፡ ማኅበሩ ፡ ያለውን ፡ ቋሚ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ሀብት ፡ በሙሉ ፡
ለባለገንዘቦች ፡ እንዲቆይ ፡ ማስገደድ ፡ አይችልም ። ሰዎች ፡ ማኅበርን ፡ የሚያቋቁሙ
በት ፡ ምክንያት ፡ ትርፍን ፡ ለማግኘት ፡ ነው ። በማኅበሩ ፡ የሚገኘውን ፡ ትርፍ ፡ ተከ
ፋፍለው ፡ ትርፉን ፡ ካልተቀበሉ ፡ ማኅበሩን ፡ አያቋቁሙም ። ስለዚህም ፡ እርግጠኛ ፡
የሆነውን ፡ ትርፍ ፡ መከፋፈል ፡ ይቻላል ፡ በሚለው ፡ ወደ ፡ ስምምነት ፡ ተደርሷል ።
ነገር ፡ ግን ፡ ማኅበሩ ፡ በሚኖርበት ፡ ጊዜ ፡ ዋና ፡ ገንዘቡን ፡ የሚያክል ፡ ገንዘብ ፡
ወይም ፡ ንብረት ፡ ሊኖር ፡ ይገባል ። ለማኅበርተኞችም ፡ መከፋፈል ፡ የለበትም ።
(ማኅበሩ ፡ በሥራ ፡ ምክንያት ፡ በሚያደርገው ፡ ጉዳይ ፡ የተነሳ ፡ ዋና ፡ ገንዘቡን ፡ የሚ
ያክል ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ ሊከስር ፡ ይችላል ። ይህ ፡ ከንግድ ፡ ማኅበሩ ፡ ሊመ
ጣ ፡ የሚችል ፡ አደጋ ፡ ስለሆነ ፡ በማኅበሩ ፡ ማኅበርተኞችና ፡ በባለገንዘቦች ፡ ተቀባ
ይነትን ፡ የሚያገኝ ፡ መሆን ፡ አለበት) ።

መመሪያው ፡ የማኅበርተኞቹ ፡ በሙሉ ፡ አላፊነት ፡ የተወሰነ ፡ ለሆኑ ፡ ማኅበሮች ፡
በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ለአክሲዮን ፡ ማኅበርና ፡ ኃላፊነቱ ፡ ለተወሰነ ፡
የግል ፡ ማኅበር ፡ ማለት ፡ ነው ። በማኅበሩ ፡ ያልተከፈለን ፡ ዕዳ ፡ ለማግኘት ፡ ባለገንዘቡ ፡
ሊመለከት ፡ የሚችለው ፡ የማኅበሩን ፡ ንብረት ፡ ብቻ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ማኅበሮች ፡
ትርፎችን ፡ ለማኅበርተኞች ፡ የሚያከፋፍሉበትን ፡ መንገድ ፡ የሚወስኑ ፡ የተወሳ
ሰቡ ፡ ደንቦች ፡ ተሰጥተዋል ። በተጨማሪም ፡ ባለገንዘቦችና ፡ የሂሳብ ፡ አጣሪዎች ፡
ለማኅበሩ ፡ ሊያዋጣ ፡ የሚገባውን ፡ መዋጮ ፡ በሙሉ ፡ ያልከፈለ ፡ ማኅበርተኛ ፡ እን
ዲከፍል ፡ ሊያስገድዱባቸው ፡ የሚያስችሏቸው ፡ ሌሎች ፡ ደንቦች ፡ ተሰጥተዋል ።[62]

የማኅበርተኞቹ ፡ አላፊነት ፡ ያልተወሰነ ፡ ከሆነ ፡ መመሪያው ፡ ብዙ ፡ ጠቃሚ ፡
አይደለም ፡ ምክንያቱም ፡ ገንዘቡን ፡ ያልተከፈለ ፡ ባለገንዘብ ፡ ማኅበርተኞችን ፡ በማን
ኛውም ፡ ጊዜ ፡ መክሰስ ፡ ስለሚችል ፡ ነው ። ይህም ፡ በኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡
ማኅበርተኞችና ፡ አላፊነታቸው ፡ ባልተወሰነ ፡ የሁለት ፡ ዓይነት ፡ አላፊነት ፡ የአለ
በት ፡ ማኅበር ፡ አባሎች ፡ ላይ ፡ ይሠራል ። ማኅበርተኞቹ ፡ ትርፍ ፡ ሳይኖር ፡ እንደ ፡
ትርፍ ፡ የተቀበሉትን ፡ ድርሻዎች ፡ ለማኅበሩ ፡ እንዲመልሱ ፡ የሚያስገድድ ፡ ክስ ፡
በባለገንዘብ ፡ የተመሠረተ ፡ እንደሆነ ፡ ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ማኅበሩን ፡ መጠየቅ ፡ ሳያስፈ
ልግ ፡ በቀጥታ ፡ በማኅበርተኞች ፡ ላይ ፡ ሊመሠረት ፡ በሚያስችለው ፡ በቁጥር ፡ ፪፻፺፩፡
እንኳ ፡ ቢሆን ፡ መመሪያው ፡ ተቀባይነትን ፡ አግኝቷል ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ባለ

62. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፶፪ ፣ ፬፻፶፯—፬፻፶፱ ፣ ፬፻፺፱ ፣ (፩) ፣ ፭፻፩ ፣ ፭፻፫ ፣ ፭፻፲፩ ፣ ፭፻፶፫—፭፻፶፬ ፡ ተመል
ከት ።

ገንዘቡ ፡ ስለአልተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ (ዕዳ) ፡ በማኅበርተኛው ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ከመመሥ ረቱ ፡ በፊት ፡ ማኅበሩን ፡ መጠየቅ ፡ ይኖርበታል ።

መመሪያው ፡ አላፊነታቸው ፡ ለተወሰነ ፡ የሁለት ፡ ዓይነት ፡ ኃላፊነት ፡ የአለበት ፡ ማኅ በር ፡ ማኅበርተኞችም ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ማኅበርተኞች ፡ ያላገቡት ፡ መዋጮ ፡ ቢኖር ፡ እንዲያገቡ ፡ በባለገንዘቡ ፡ ሊገደዱ ፡ ይችላሉ ። በማኅበሩ ፡ የሂሳብ ፡ ማመዛ ዘኛ ፡ ባለው ፡ ሂሳብ ፡ ከጸደቀ ፡ በኋላ ፡ በቅን ፡ ልቦና ፡ የተቀበሉት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ማኅበርተኞች ፡ ትርፍ ፡ ሳይኖር ፡ እንደትርፍ ፡ የተቀበሉትን ፡ እንዲመልሱ ፡ ሊገ ደዱ ፡ ይችላሉ ።[63]

## ፬. የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፦

ውል ፡ የሆነው ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ስምምነት ፡ ለማንኛውም ፡ የንግድ ፡ ማኅ በር ፡ መሠረት ፡ ነው ።[64] ይህም ፡ ማለት ፦

፩/ በቁጥር ፡ ፪፻፲፩ ፡ ለሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ በተሰጠው ፡ ትርጓሜ ፡ የሚፈ ለጉትን ፡ ነገሮች ፡ የሚያሟላ ፡ በማኅበርተኞቹ ፡ የተፈጸመ ፡ ውል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ሊቋቋም ፡ አይችልም ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፺ ፡ መሠረት ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮችን ፡ በሚመለከቱ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፤ ድንጋጌዎች ፡ (ውሳኔ ዎች) ፡ ቢመራም ፡ እንኳ ፡ "ትርፎችን ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለመካፈል ፡ የተቋቋመ" ፡ ስብሳቤ ፡ በሚጸና ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ካልተቋቋመ ፡ በቀር ፡ የንግድ ፡ ማኅ በር ፡ አይደለም ።[65]

፪/ የሽርክና ፡ ማኅበርን ፡ የሚመለከቱ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ደንቦች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፪ ፡ ከተሰጡት ፡ ውሎችን ፡ ከሚመለከቱ ፡ ጠቅላላ ፡ ደንቦች ፡ በተለይ ፡ እንዲሠሩ ፡ የተደረጉ ፡ ናቸው ።

ከላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ የውል ፡ ደንቦች ፡ ከአክሲዮን ፡ ማኅበሮች ፡ ይበልጥ ፡ በተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፤ በእሽሙር ፡ ማኅበሮችና ፤ በሁለት ፡ ዓይነት ፡ አላፊነት ፡ በአለባቸው ፡ ማኅበሮች ፡ ላይ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ይሆናሉ ። የአክሲዮን ፡ ማኅበርን ፡ በተለይም ፡ ብዙ ፡ ማኅበርተኞች ፡ የአሉት ፡ ማኅበርን ፡ አመሠራረት ፤ ሥራ ፡ አካሄ ድና ፤ አፈራረስን ፡ ከሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ ይልቅ ፡ የኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበርን ፡ አመሠራረት ፤ ሥራ ፡ አካሄድና ፤ አፈራረስ ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ ውሎችን ፡ ከሚ መለከቱ ፡ አጠቃላይ ፡ ደንቦች ፡ ጋራ ፡ ይቀራረባሉ ። ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ማኅበር ተኞች ፡ በአሉት ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ እያንዳንዱ ፡ ባለአክሲዮን ፡ ለማኅ በሩ ፡ ዋና ፡ ውል ፡ የውሉ ፡ ተዋዋይ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ማሰብ ፡ በጣም ፡ ያስቸግራል ። ማኅበርተኛ ፡ ሊሆን ፡ የቻለው ፡ በማኅበሩ ፡ መሥራቾች ፡ በቀረቡ ፡ የአክሲዮኖች ፡ ሽያጭ ፡ መሠረት ፡ ለመግዛት ፡ በመፈረም ፡ ወይም ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ አክሲዮኖች ፡ በመግዛት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ስለዚህም ፡ የሰውየው ፡ መብቶች ፡ የሚመሩት ፡ ከዋ ናው ፡ ውል ፡ ይበልጥ ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበሮችን ፡ በሚመለከቱ ፡ የሕግ ፡ ውሳኔዎ

63. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፶፬ ፤ ፪፻፶፭ ፤ ፪፻፶፪ ።
64. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲ ፡ (፩) ፤ ፪፻፲፩ ።
65. ነገር ፡ ግን ፡ የፒ. ማክአርቲን ፡ "በሕግ ፡ ሳይታወቁ ፡ የሚሠሩ ፡ ("ዲ ፡ ፋክቶ") ፡ እና ፡ ልማዳዊ ፡ የሽ ርክና ፡ ማኅበሮች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡" የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፤ ፭ኛ ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም) ፡ ገጽ ፡ ፪፻፳፫ ፡ ተመልከት ።

ች፡ ነው ። ቢሆንም ፣ በአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ እንኳ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ እንደ ፡ መሠረት ፡ ሊኖር ፡ ያስፈልጋል ። ይህም ፡ ውል ፡ የሌሎች ፡ ማኅበሮች ፡ መሠረት ፡ የሆ ነው ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ የሚፈጽማቸውን ፡ ብዙዎችን ፡ ተግባሮች ፡ ይፈጽ ማል ።

"ስለ ፡ ማኅበር ፡ የመመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡" የሚናገሩ ፡ ብዙ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ አሉ ። "የማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍና ፡" "የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡" የሚያመለክቱት ፡ አንድን ፡ ነገር ፡ ነው ። ይኸውም ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ መሠረት ፡ የሆነውን ፡ ዋናውን ፡ ውል ፡ ነው ። ጉልህ ፡ የሆነ ፡ ልዩነት ፡ የለም ። ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ የንግድ ፡ ማኅበርን ፡ በሚመሠርትበት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ የሽርክና ፡ ማኅ በር ፡ ውልና ፡ ሌላ ፡ የማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ አያዘጋጅም ፡ "የማኅበሩ ፡ መ መሥረቻ ፡" የሚባለው ፡ ቃል ፡ በሕጉ ፡ አጠቃቀም ፡ መሠረት ፡ የሚመለከተው ፡ ከተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ በቀር ፡ በማንኛውም ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ሥር ፡ የሚገ ኘውን ፡ ዋና ፡ ውልን ፡ ነው ።[66] "የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡" የሚባለው ፡ ቃል ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ አጠቃቀም ፡ አለው ። በተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ የሚገኘ ውን ፡ ዋና ፡ ውል ፡ በሚመለከትና ፡ የማንኛውም ፡ ንግድ ፡ ማኅበር ፡ መሠረት ፡ የሆነ ውን ፡ ውል ፡ በሚመለከት ፡ ነው ።[67]

አንዳንድ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ "ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ፡" ይናገራሉ ። ሕጉ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበርንና ፡ አላፊነቱ ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበርን ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ የሚወስኑትን ፡ ዝርዝር ፡ ደንቦች ፡ ለማመልከት ፡ ይጠቀ ምበታል ። የማኅበሩ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንቦች ፡ የሚዘጋጁት ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ የማ ኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ በሚዘጋጅበት ፡ ዓይነት ፡ ነው ። እነዚህም ፡ የማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ክፍል ፡ እንደሆኑ ፡ ይቆጠራል ።[68]

<u>የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ አቋሞች ፡-</u>

በአንቀጽ ፡ ፪፻፲፩ ፡ መሠረት ፡-

የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ማለት ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ መዋጮ፡ አዋጥተው ፡ በአንድነትና ፡ በሕብረት ፡ የኢኮኖሚ ፡ ተግባር ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ለመሥራትና ፡ ከሚገኘው ፡ ትርፍም ፡ ሆነ ፡ ከሚመጣው ፡ ዕዳ ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ የሚስማሙበት ፡ ውል ፡ ነው ።

የዚህም ፡ ትርጓሜ ፡ አቋሞች ፡ በሚቀጥሉት ፡ ጽሑፎች ፡ ተገልጿዋል ።

<u>ሁለት ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡</u> ቢያንስ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ተዋዋዮች ፡ መሆን ፡ አለባቸው ። ቢያንስ ፡ አምስት ፡ ሰዎች ፡ እንዲኖሩት ፡

66. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፹፮ ፡ (፩)፤ ፪፻፺፱፤ ፪፻፺፰፤ ፫፻፲፫፤ ፭፻፲፯ ፡ ይህ ፡ በተጨማሪ ፡ የሰብዓዊ ፡ ነር ፡ ማኅበርን ፡ መሠረት ፡ ውል ፡ ይጠቅሳል ። (ይመለከታል) ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯፻፷ ።

67. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፩፤ ፪፻፴፫፤ ቁጥር ፡ ፪፻፳፮ ፡ (፪) ፡ ና ፡ ፪፻፳፱ ፡ ማኅበሩ ፡ የተቋቋመበት ፡ ጽሑፍ ፡ ውል ፡ ስለመሆኑና ፡ ስለዚህም ፡ ለንግድ ፡ መዝገብ ፡ ኃላፊ ፡ ለሆነው ፡ ሠራተኛ ፡ መስጠትም ፡ ያለበት ፡ ስለመሆኑ ፡ ብቻ ፡ ይናገራሉ ፤ ይህም ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ ምናልባት ፡ ሁሉም ፡ የማኅበሩ ፡ መቋቋሚያ ፡ ጽሑፍ ፡ ያላቸው ፡ ዓይነተኛ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ድርጅቶች ፡ ብቻ ፡ በመዝገብ ፡ የመግባት ፡ ግዴታ ፡ እንዲኖራቸው ፡ በቅድሚያ ፡ ታስቦ ፡ ይሆናል ። ማስታወሻ ፡ ፷፫ንና ፡ የተያያዘውን ፡ ጽሑፍ ፡ ተመልከት ።

68. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፬፤ ፭፻፲፰ ።

ከሚገደደው ፡ ከአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ አባባል ፡ በሁሉም ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ይጸናል ።[69]

አነስተኛ ፡ ተፈላጊ ፡ የሆነው ፡ የሰዎች ፡ ቁጥር ፡ ሁለት ፡ መሆኑ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻውን ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ሊያቋቁም ፡ አይችልም ፡ ማለት ፡ ነው ። በማንኛውም ፡ መንገድ ፡ ቢሆን ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ማኅበር ፡ የሚባለው ፡ አስተሳሰብ ፡ ትክክለኛ ፡ ላይመስል ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ማኅበር ፡ ያለው ፡ ጥቅም ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ነጋዴ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ይህም ፡ በተለይ ፡ ለተወሰነ ፡ አላፊነትና ፡ አባሉ ፡ ቢሞትም ፡ በማኅበሩ ፡ ለመኖር ፡ መቻል ፡ ላይ ፡ ይጸናል ።[70] አንድ ፡ ነጋዴ ፡ እነዚህን ፡ ጥቅሞች ፡ ለማግኘት ፡ ከፈለገ ፡ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ ማኅበርተኛ ፡ ሊኖረው ፡ ያስፈልጋል ። ነጋዴው ፤ ማኅበርተኛው ፡ በማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ባይካፈልም ፡ ተፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ አነስተኛ ፡ ቁጥር ፡ ለማሟላት ፡ ብቻ ፡ ሲል ፤ ማኅበርተኛውን ፡ ማግኘት ፡ ይኖርበታል ። ነገር ፡ ግን ፡ የተቋቋመው ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኛ ፡ የሆነው ፡ የመጀመሪያው ፡ ነጋዴ ፡ አላፊነት ፡ የተወሰነ ፡ ከሆነ ፡ ሁለተኛው ፡ ማኅበርተኛ ፡ መጠንቀቅ ፡ ይኖርበታል ። የማኅበሩን ፡ የሥራ ፡ ደንቦች ፡ በደንብ ፡ ባለመመልከት ፡ ማኅበሩን ፡ የግሉ ፡ እንደሆነ ፡ ቆጥሮ ፡ ቢሠራና ፡ ማኅበሩ ፡ ቢከስር ፡ የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ የሚሰጠውን ፡ ጥቅም ፡ ሊያጣ ፡ ይችላል ።[71]

የማኅበሩ ፡ አባሎች ፡ ቁጥር ፡ ከሃምሳ ፡ መብለጥ ፡ ከማይችልበት ፡ አላፊነቱ ፡ ከተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ በቀር ፡ የማኅበሩን ፡ አባሎች ፡ ከፍተኛ ፡ ቁጥር ፡ የሚወስን ፡ ነገር ፡ የለም ።[72] በማኅበርተኞች ፡ መሐከል ፡ ሊኖር ፡ በሚገባው ፡ የቅርብ ፡ ግንኙነት ፡ የተነሳ ፡ በተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ በእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ማኅበርተኞች ፡ ቁጥር ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ አነስተኛ ፡ ይሆናል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኞች ፡ ቁጥር ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ መሆን ፡ ይችላል ።

<u>በአንድነትና ፡ በኅብረት ፡ ለመሆን ፡ ስለመፈለግ</u> ፡ ውሉ ፡ የሚጸና ፡ የኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ውል ፡ እንዲሆን ፡ ከተፈለገ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ "በአንድነትና ፡ በኅብረት ፡ ለመ

---

69. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፺፮ ፡ (፩) ።

70. የንግድ ፡ መደብር ፡ ሊሸጥና ፡ ሊወረስ ፡ የሚቻል ፡ ግዙፍነት ፡ የሌለው ፡ ዓይነት ፡ ንብረት ፡ ስለሆነ ፡ ነጋዴው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ንግዱ ፡ እንዲኖር ፡ ለማድረግ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ማቋቋም ፡ አያስፈልግም ። በዚህ ፡ አቅጣጫ ፤ የንግድ ፡ ማኅበር ፤ የንግድ ፡ መደብር ፡ ብቻውን ፡ የሌለውን ፡ አንዳንድ ፡ ጥቅሞች ፤ አሉት ። ለምሳሌ ፡ ነጋዴው ፡ በሚሞትበት ፡ ጊዜ ፡ የንግድ ፡ መደብሩ ፤ ደንበኛ ፡ ገበያተኛን ፤ ሳይጨምር ፡ በከፊሉ ፡ ይሸጣል ፡ በማለት ፡ ይሰጋ ፡ ይሆናል ። ይህም ፡ በተለይ ፡ አደገኛ ፡ የሚሆነው ፡ በንግድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ልምምድ ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ የውርሱን ፡ ጉዳይ ፡ የያዙት ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። ደንበኛ ፡ ገበያተኛው ፡ ሊበላሽ ፡ ይችላል ። የመበላሸቱም ፡ ውጤት ፡ ወደ ፡ ወራሾቹ ፡ የሚሄደው ፡ ክፍያ ፡ አነስተኛ ፡ መሆንና ፡ የደንበኛ ፡ ገበያተኛ ፡ ዋጋ ፡ በመቀነሱ ፡ የኢኮኖሚ ፡ ኪሣራ ፡ ነው ። ይህ ፡ የንግድ ፡ መደብሩ ፡ በንግድ ፡ ማኅበሩ ፡ የሚካሄድ ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለመሆን ፡ ያለው ፡ ዕድል ፡ አነስተኛ ፡ ነው ። የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ቢያንስ ፡ ሁለት ፡ ማኅበርተኞች ፡ ስለሚኖሩት ፡ በአንድ ፡ ሰው ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ ማኅበሩ ፡ ቢፈርስም ፡ እንኳ ፡ የንግዱ ፡ ዋጋ ፡ መጠበቅን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ሌላው ፡ ማኅበርተኛ ፡ ይኖራል ። በሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ላይ ፡ አንዱ ፡ አባል ፡ ቢሞት ፡ እንኳ ፡ ድርሻው ፡ ለወራሾቹ ፡ ተሰጥቶ ፡ ማኅበሩ ፡ ለመቀጠል ፡ የሚያስችለውን ፡ ስምምነት ፡ ማድረግ ፡ ይቻላል ። (ይህም ፡ በሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውሉ ፡ ላይ ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ድንጋጌ ፡ ባይኖር ፡ እንኳ ፡ በአክሲዮን ፡ ማኅበርና ፡ በአላፊነቱ ፡ በተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፡ ይኖራል) ፡ ጋና ፤ ኮሚሽን ፡ እፍ ፡ ኢንኳየሪ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ፴፫ ፡ የተጠቀሰውን ፤ ገጽ ፡ ፯ ፡ ተመልከት ፤ ሌ. ሲ. ቪ. ጕወር ፤ "ካምፓኒ ፡ ሎው ፡ ሪፎርም" ፤ <u>ማላያ ፡ ሎው ፡ ሪቪው</u> ፤ ፬ኛ ፡ ቮልዩም ፡ (፲፱፻፷፪) ፡ ገጽ ፡ ፵፱ን ፡ ተመልከት ።

71. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፴፩ ፤ ፭፻፴፫ ።

72. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፲ ፡ (፪) ።

ሆን" ፡ መፈለግ ፡ አለባቸው ። ይህም ፡ ማለት ፡ የንግድ ፡ ማኅበሩን ፡ ለማቋቋም ፡ የፈለጉ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ፡ ማለት ፡ ነው ። በይበልጥ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ አነጋገርም ፡ ለጋራ ፡ ጥቅምና ፡ በእኩልነት ፡ ደረጃ ፡ በአንድነት ፡ የመሥራት ፡ ፍላጐት ፡ እንዲኖራቸው ፡ ያስፈልጋል ።[73] ይህም ፡ የሚታየው ፡ እያንዳንዱ ፡ ማኅበርተኛ ፡ በማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የመቆጣጠር ፡ መብት ፡ በመመልከት ፡ ነው ።

አንድነት ፡ የመሆን ፡ የማኅበርተኞች ፡ ፍላጐት ፡ ሁሉም ፡ ለማኅበሩ ፡ ወይም ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ለመሥራት ፡ በታቀደ ፡ ንቁ ፡ ዓላማ ፡ መመሥረት ፡ አይኖርበትም። ይህም ፡ ገንዘባቸውን ፡ ብቻ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ በሚፈልጉ ፡ አላፊነታቸው ፡ ለተወሰነ ፡ የሁለት ፡ ዓይነት ፡ ኃላፊነት ፡ ያለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኞች ፡ በአክሲዮን ፡ ማኅበርና ፡ ኃላፊነቱ ፡ በተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ ላይ ፡ አይሠራም ። ሕጋዊ ፡ (ትክክለኛ) ፡ የሆኑ ፡ የቁጥጥር ፡ ዕቅዶች ፡ ለመኖራቸው ፡ ማስረጃ ፡ (ማረጋገጫ) ፡ ስለማይሆን ፡ በአንዳንድ ፡ ማኅበሮች ፤ በተለይም ፡ እንደ ፡ አክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ዓይነት ፡ የተለያዩ ፡ ቡድኖች ፡ የተለያዩ ፡ መብቶች ፡ ባሉዋቸው ፡ ማኅበሮች ፡ ውስጥ ፡ ስምምነቱ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ እኩል ፡ ሊሆን ፡ አይገባውም ። የሕጉ ፡ ግዛት ፡ ከሚፈቅደው ፡ ቁጥጥር ፡ በቀር ፡ እኩል ፡ መሆን ፡ አለበት ።

ማዳጁ ፡ እንዲኖር ፡ የተደረገው ፡ የሽርክና ፡ ማኅበርን ፡ ሌሎች ፡ አቋሞች ፡ ከሚይዙ ፡ ውሎች ፡ ለመለየት ፡ የሚረዳ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።[74] የተወሰነ ፡ ደሞዝ ፡ ሳይኖር ፡ ሠራተኛው ፡ ትርፍ ፡ ቢኖር ፡ ደመወዙን ፡ ከትርፉ ፡ ላይ ፡ በመካፈል ፡ የሚከፈልበት ፡ የሥራ ፡ ውል ፤ የተወሰነ ፡ ወለድ ፡ ከመስጠት ፡ ፈንታ ፡ አበዳሪው ፡ ትርፍ ፡ ቢኖር ፡ ከትርፉ ፡ እንዲካፈል ፡ የሚያደርግ ፡ የብድር ፡ ውልና ፡ ለንግድ ፡ መደብሩ ፡ ሻጭ ፡ የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ ከመክፈል ፡ ይልቅ ፡ ሻጩ ፡ ከንግድ ፡ መደብሩ ፡ የወደፊት ፡ ትርፍ ፡ እንዲካፈል ፡ የሚያደርግ ፡ የሽያጭ ፡ ውል ፡ ለዚህ ፡ ምሳሌዎች ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ ውሎች ፡ ውስጥ ፡ በአንድነትና ፡ በኅብረት ፡ የመሆን ፡ ፍላጐት ፡ የለም ። የንግድ ፡ መደብሩን ፡ ለሚመለከቱ ፡ ውሳኔዎች ፡ ሠራተኛው ፡ በአሠሪው ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነው ። የንግድ ፡ መደብር ፡ አበዳሪ ፡ ወይም ፡ ሻጭ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በመደብሩ ፡ የሥራ ፡ እንቅስቃሴ ፡ ላይ ፡ አይካፈልም ።

<u>መዋጮዎች</u> ፡ የሚጸና ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ እንዲኖር ፡ ከተፈለገ ፡ እያንዳንዱ ፡ ማኅበርተኛ ፡ ለንግድ ፡ ማኅበሩ ፡ መዋጮ ፡ ማዋጣት ፡ አለበት ። መዋጮዎች ፡ ማኅበሩ ፡ ሥራውን ፡ እንዲያካሂድበት ፡ በማኅበሩ ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ እንዲኖሩ ፡ የሚደረጉ ፡ ነገሮች ፡ (ዕቃዎች) ፡ ናቸው ። ስለአዋጣም ፡ የአዋጣው ፡ ሰው ፡ በማኅበርተኝነት ፡ የሚገኘውን ፡ ጥቅም ፡ ያገኛል ። በአክሲዮን ፡ ማኅበርና ፡ ኃላፊነቱ ፡ በተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በማናቸውም ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ መዋጮዎች ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፤ በዓይነት ፡ ወይም ፡ በሞያ ፡ ሥራ ፡ ሊደረጉ ፡ ይችላሉ ።[75] ለአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ ኃላፊነቱ ፡ ለተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ የሚደረጉ ፡ መዋጮዎች ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ በዓይነት ፡ ብቻ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ።[76]

---

73. በማስረጃ ፡ ፴፫ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ጂ ፡ ሪፐርት ፡ ቁጥር ፡ ፯፯ ፡ ተመልከት ፤ ፯፻፩ ፤ በማስረጃ ፡ ፰ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ጂ ፡ ኤስካራ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፯ ፡ —፭፻፲፪ ፡ ተመልከት ።

74. በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ለፈረንሣይ ፡ ንግድ ፡ ሕግ ፡ በኮሚሽን ፡ እፍ ፡ ሪፎርም ፡ የተሰጠውን ፡ መግለጫ ፡ ተመልከት ፤ <u>ትራቮ ፡ ደ ፡ ላ ፡ ኮሚሽን ፤ ደ ፡ ሪፎር ፡ ዱ ፡ ኮድ ፡ ደ ፡ ኮሜርስ ፡ ኤ ፡ ዱ ፡ ድሮዋ ፤ ዴ ፡ ሶስዬቴ</u> ፡ (ፓሪስ ፤ ሴ፲፱፻፶ ፡ ፲፱፻፵፰—፲፱፻፵፱) ፡ ፪ኛ ፡ ቮልዩም ፤ ገጽ ፡ ፫፻፶፫ ፤ ፫፻፶፬ ፤ የሳብ ፡ ኮሚሽን ፡ መግለጫ ፤ ፪ኛ ፡ ቮልዩም ፤ ገጽ ፡ ፭፻፲፩ን ፡ በተጨማሪ ፡ ተመልከት ።

75. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፱ ፤ ፪፻፴፩ ፤ ፪፻፲፭ ፤ ፫፻፫ ።

76. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳ ፤ ፫፻፲፪ ፤ ፭፻፴፰ ፤ ፫፻፴፱ ፤ ፭፻፲፪ ።

በዓይነት ፡ የሚደረጉ ፡ መዋጮዎች ፡ ግዙፍነት ፡ ባላቸውና ፡ በሌላቸው ፡ ንብረቶች ፡ የሚደረጉ ፡ መዋጮዎች ፡ ናቸው ። እነዚህንም ፡ የሚያዋጣው ፡ ሰው ፡ ያሉትን ፤ የገንዘብ ፡ መብቶችን ፡ (ዕዳዎችን) ፡ ወይም ፡ የንብረት ፡ ጥቅምን ፡ ይጨምራሉ ። የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፤ የሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፤ የድርሰትና ፡ የኪን ፡ ጥበብ ፡ ባለ ሀብትነት ፡ መብቶች ፤ የኢንዱስትሪ ፡ ንብረቶች ፡ (የንግድ ፡ ምልክቶች ፤ እንዱስትሪ ዎች ፤ ስዕሎችና ፡ ሞዴሎች) ፤ የንግድ ፡ መደብር ፤ የሚንቀሳቀስ ፡ ወይም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ኪራይና ፡ ሌሎችም ፡ ምሳሌዎች ፡ ናቸው ። ሕጉ ፤ እነዚህ ፡ ንብረቶች፣ ለማኅበሩ ፡ የሚተላለፉበትን ፡ መንገድ ፡ የሚመለከቱ ፡ ብዙ ፡ ደንቦች ፡ አሉት ። ከቁጥር ፡ ፪፻፳፯ — ፪፻፴፪ ፡ (ለተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፤ ለኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፤ ለሁለት ፡ ዓይነት ፡ ኃላፊነት ፡ ለአለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ የሚደረጉ ፡ መዋጮዎችና) ፡ ከቁጥር ፡ ፪፻፹—፪፻፺ ፡ (የማኅበርተኝነትን ፡ ድርሻ ፡ መዋጮ ፡ አድርጎ ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ መደብርን ፡ ለማኅበር ፡ ስለማስገባት) ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ተመልከት ።

የእያንዳንዱ ፡ በዓይነት ፡ የሚደረግ ፡ መዋጮ ፡ ዋጋ ፡ ማኅበርተኞቹ ፡ በተስማሙበትና ፡ በሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውሉ ፡ በተፃፈው ፡ መሠረት ፡ ነው ። የአባሎቹ ፡ በሙሉ ኣላፊነት ፡ የተወሰነ ፡ በሆነበት ፡ በአክሲዮን ፡ ማኅበርና ፡ ኃላፊነቱ ፡ በተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፡ ባለገንዘቦች ፡ በዓይነት ፡ የተዋጣውን ፡ ነገር ፡ ግምት ፡ ትክክለኛ ፡ መሆኑን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ተጨማሪ ፡ መከላከያ ፡ ይፈልጋሉ ። ይህ ፡ መከላከያ ፡ ሕዝቡ ፡ አክሲዮኑን ፡ እየፈረመ ፡ በመግዛት ፡ ለተቋቋመ ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ባለአክሲዮኖችም ፡ ይፈለጋል ። ምክንያቱም ፡ ንብረቱን ፡ ወይም ፡ አዋጭውን ፡ ሰው ፡ ለማግኘት ፡ የሚችሉበት ፡ ቀላል ፡ መንገድ ፡ ባለመኖሩ ፡ ነው ። ለአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ የሚደረጉ ፡ የዓይነት ፡ መዋጮዎችን ፡ መገመቻ ፡ የተለየ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በሕግ ፡ ተሰጥቷል ።[77] ኃላፊነቱ ፡ በተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበር ፤ በሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ለተፃፈው ፡ በዓይነት ፡ ለተደረገ ፡ መዋጮ ፡ ግምት ፡ ማኅበርተኞች ፡ በሙሉ ፡ ለሦስተኛ፣ ወገኖች ፡ ዋሶች ፡ ናቸው ።[78]

አገልግሎቱን ፡ ወይም ፡ የሞያ ፡ ሥራውን ፤ የተወሰነ ፡ ደመወዝ ፡ ሳይከፈለው ፤ ለማኅበሩ ፡ የሚያዋጣ ፡ ሰው ፡ ከትርፉ ፡ ላይ ፡ ድርሻ ፡ ይኖረዋል ። ሠራተኞች ፡ የሌላቸውን ፡ ማኅበሩን ፡ የመቆጣጠሪያ ፡ መብቶች ፡ ስላሉው ፡ "ከሠራተኛ" ፡ ይበልጣል ።

ማኅበሩ ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ያልተሰጠው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ወይም ፡ የንብረቱ ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ የተዋጣ ፡ ከሆነ ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ በዓይነት ፡ የሚደረጉ ፡ መዋጮዎች ፡ የማኅበሩ ፡ ሀብቶች ፡ ናቸው ። በእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ ደንብ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ እያንዳንዱ ፡ ማኅበርተኛ ፡ ገቢ ፡ ላደረገው ፡ መዋጮ ፡ ባለሀብትነቱን ፡ እንደያዘ ፡ ይቆያል ።[79] ("ተቃራኒ" ፡ ድንጋጌዎች ፡ በአባሎች ፡ ያልተከፋፈለ ፡ ባለቤትነትን ፡ ወይም ፡ የእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ እስኪያጅች ፡ ባለሀብትነትን ፡ ይጨምራሉ) ።

ዓላማ ፡ የኢኮኖሚ ፡ ተግባሮች ፡ የሚጸና ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኞች ፡ "የኢኮኖሚ ፡ ተግባር ፡ ያለውን ፡ ሥራ" ፡ ለመሥራት ፡ መፈለግ ፡ አለባቸው ። ይህም፣ ሐረግ ፡ ሰፊና ፡ ማንኛውንም ፡ ትርፍ ፡ ያለውን ፡ ወይም ፡ ትርፍ ፡ ሊያስገኝ ፡ የሚች

77. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፮ ።
78. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፱ ።
79. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፫ ።

ለውን ፣ ሥራ ፡ ሊጨምር ፡ ይችላል ። የሽርክና ፡ ማኅበሩ ፣ ማኅበርተኞች ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲሠራ ፡ የሚፈልጉት ፡ ሥራ ፣ የማኅበሩ ፡ የንግድ ፡ (የሥራ) ፡ ዓላማ ፡ ይባላል ። በጠቅላላው ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ማንኛውንም ፡ ሊገኝ ፡ (ሊደረግ) ፡ የሚችል ፤ ሕገ ፡ ወጥ ፣ ያልሆነና ፡ ግብረገብነት ፡ ያልጐደለው ፡ ዓላማ ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ።[80]

ዓላማ ፡ ትርፎችና ፡ ኪሣራዎች ፣ የስምምነቱ ፡ ማኅበርተኞች ፡ ትርፍና ፡ ኪሣራ ፡ በሚኖርበት ፡ ጊዜ ፡ ከትርፉም ፤ ከኪሣራውም ፡ ለመካፈል ፡ መፈለግ ፡ አለባቸው ። ማኅበሩ ፡ በሚቋቋምበት ፡ ጊዜ ፡ ማኅበርተኞች ፡ የሚያስቡት ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ትርፍ ፡ እንጂ ፡ ስለኪሣራ ፡ አያስቡም ። ኪሣራው ፡ እንዲከፋፈል ፡ በመፈለግ ፡ ሕጉ ፤ በማኅበሩ ፡ ሊመጡ ፡ የሚችሉ ፣ አደጋዎችን ፡ ለመካፈል ፡ መፈለግን ፡ ግዴታ ፡ ያደርገዋል ።[81]

የማኅበርተኞቹ ፡ የትርፍና ፡ የኪሣራ ፡ ድርሻ ፡ እኩል ፡ መሆን ፡ አይኖርበትም ። እኩልነት ፡ ላይኖር ፡ የሚችለው ፡ በተለያዩ ፡ አባሎች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በአንድ ፡ አባል ፡ የትርፍ ፡ ድርሻና ፡ የኪሣራ ፡ ድርሻ ፡ መሐከል ፡ እኩልነት ፡ ላይኖር ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውሉ ፡ የማኅበሩን ፡ የወደፊት ፡ ትርፍ ፡ በሙሉ ፡ ለአንዱ ፡ ማኅበርተኛ ፡ ብቻ ፡ ሊሰጥ ፡ አይችልም ፤ አንዱን ፡ ወይም ፡ ብዙዎቹን ፡ ማኅበርተኞችንም ፡ በማኅበሩ ፡ ላይ ፡ የሚደርሰው ፡ ኪሣራ ፡ እንዳይነካቸው ፡ ለማድረግ ፡ አይችልም ። በውሉ ፡ ይህን ፡ የሚሰጥ ፡ ማንኛውም ፡ ስምምነት ፡ (ውሳኔ) ፡ ፍርስ ፡ ነው ።[82]

ጠቅላላ ፡ የውል ፡ ግዴታዎች ፣ ውል ፡ እንደመሆኑ ፤ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፤ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፪ ፡ የተሰጡት ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይጸኑበታል ። ይህም ፡ የውሉን ፡ አመሠራረት ፡ በሚመለከት ፣ ጉዳይ ፡ ላይ ፣ ውሉን ፡ ለመዋዋል ፡ ችሎታ ፡ ባላቸው ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ጉድለት ፡ የሌለው ፡ ስምምነት ፡ መኖር ፤ በቂ ፡ የሆነ ፤ እርግጠኛነት ፡ ያለው ፤ የሚቻልና ፡ ሕጋዊ ፡ የሆነ ፡ ጉዳይና ፡ የውሉ ፡ አጻጻፍ ፡ ዐይነት ፡ (ፎርም) ፡ በሕግ ፡ የታዘዘ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ ማለት ፡ ነው ። የሚከተሉት ፡ ክፍሎች ፡ እነዚህን ፡ አቋሞች ፡ ይገልጻሉ ፤ ይኸውም ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ልዩ ፡ ችግሮች ፡ ሊነሱ ፡ የሚችሉ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ተዋዋዮችና ፡ ችሎታ ፣ በጠቅላላው ፡ የሚከተሉት ፡ ሰዎች ፡ ውል ፡ ሊፈጽሙ ፡ አይችሉም ። አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ሰዎች ፤ በግልጽ ፡ የታወቁ ፣ እእምሮ ፡ ጐደሎዎች ፤ ፈቃድ ፡ የመስጠት ፡ ችሎታቸው ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ድውይነት ፡ ያለባቸው ፡ ሰዎች ፤ በፍርድ ፡ የተከለከሉ ፡ ሰዎችና ፡ በሕግ ፡ የተከለከሉ ፡ ሰዎች ። በነዚህ ፡ ሰዎች ፡ የተፈጸመ ፡ (የተደረገ) ፡ ውል ፡ ፍርስ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ፈራሽነቱ ፡ የሚገለጸው ፡ ችሎታ ፡ በሌለው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ በእንደራሴው ፡ ወይም ፡ በወራሾቹ ፡ አመልካችነት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ብቻ ፡ ነው ። (በሕግ ፡ በተከለከለ ፡ ሰው ፡ የሚደረግ ፡ ውል ፡ ሊፈርስ ፡ የሚችለው ፡ በሕግ ፡ በተከለከለው ፡ ሰው ፤ በሌላው ፡ ተዋዋይ ፤ ወይም ፡ በዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ አመልካችነት ፡ ነው ።)[83]

---

80. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፫ ፡ (፩) ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯፻፲፭ ፤ ፲፯፻፳ ፤ ፲፯፻፳፬ ፤ ከታች ፡ በማስረጃ ፡ ፩፻፬—፩፻፲፫ ፡ ያሉትን ፡ የተያያዙ ፡ ጽሑፎችን ፡ ተመልከት ።
81. ከላይ ፡ በማስረጃ ፡ ፸፱ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ትራቮ ፤ ፪ኛ ፡ ቮልዩም ፡ ገጽ ፡ ፳ ፡ ተመልከት ።
82. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፭ ።
83. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፶ ፤ ፫፻፲፫ ፤ ፫፻፲፱ ፤ ፫፻፵፫—፫፻፵፱ ፤ ፫፻፹፫ ፤ ፫፻፺፮ ፤ ፫፻፺፯ ፤ ፲፮፻፸፰ ።

እነዚህ ፡ የችሎታ ፡ ማጣቶች ፡ የተጠቀሱት ፡ ሰዎችን ፡ በገዛ ፡ እራሳቸው ፡ ውልን ፡ የማድረግ ፡ መብት ፡ ይከለክላሉ ፡ እንጂ ፡ በእነርሱ ፡ ስም ፡ በእንደራሴዎቻቸው ፡ ውል ፡ የማድረግ ፡ መብትን ፡ አይከለክሉም ። ስለዚህም ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ሞግዚት ፤ ችሎታ ፡ በሌለው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ውል ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል ። ሞግዚቱ ፡ ሥልጣኑ ፡ በሚፈቅድለት ፡ መጠን ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ እንደሆነ ፡ ውሉ ፡ በስሙ ፡ የተደረገለት ፡ ሰውን ፡ ያለመቻል ፡ የውሉ ፡ መቃወሚያ ፡ ማድረግ ፡ አይቻልም ።[84]

የማንኛውም ፡ ውል ፡ ተዋዋይ ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ፡ የውሉን ፡ ጽኑነት ፡ መቃወሚያ ፡ የሚሆነውን ፡ ያህል ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ጽኑነትንም ፡ በተዋዋዩ ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ፡ መቃወም ፡ ይቻላል ። የንግድ ፡ ሕግ ፡ በተጨማሪ ፡ አንዳንድ ፡ ደንቦችን ፡ ይሰጣል ፡ እነዚህም ፡ ችሎታ ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ ነጋዴዎች ፡ እንዳይሆኑ ፡ ከሚከለክሉ ፡ የሕጉ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የመነጩ ፡ ናቸው ። ችሎታ ፡ በማጣት ፡ ምክንያት ፡ ነጋዴ ፡ መሆን ፡ አለመቻልን ፡ የሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ማኅበርተኛ ፡ በመሆኑ ፡ እንደነጋዴ ፡ ለሚያስቆጥሩ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ማኅበርተኛ ፡ ለመሆን ፡ ባለመቻልም ፡ ላይ ፡ ይጸናሉ ። የንግድ ፡ ሥራን ፡ በሚሠራ ፡ የሕብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ሥራን ፡ በሚሠራ ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ኃላፊነት ፡ በአለበት ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ አላፊነቱ ፡ ያልተወሰነ ፡ ማኅበርተኛ ፡ እንደ ነጋዴ ፡ ይቆጠራል ።[85] የንግድ ፡ ሥራን ፡ የሚሠራ ፡ የእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅም ፡ እንደ ፡ ነጋዴ ፡ ይቆጠራል ።

በሕጉ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የሚያወራ ፡ የመጀመሪያው ፡ ውሳኔ ፡ ቁጥር ፡ ፲፪ ፡ ነው ። እላይ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ደንቦች ፡ እንደገና ፡ ከማተት ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ የሚጨምረው ፡ ነገር ፡ የለም ። ይኸውም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ የንግድ ፡ ሥራን ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም ። ሊሠራ ፡ ቢገኝ ፡ የሚሠራቸው ፡ ሥራዎች ፤ ይኸውም ፡ ከንግድ ፡ ጋር ፡ የተያያዙ ፡ ማናቸውም ፡ ሥራዎች ፤ በዚህ ፡ ክፍል ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ የፍትሐ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ሊፈርሱ ፡ ይችላሉ ።

ቁጥር ፡ ፲፪ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ላላደረሰ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ለተከለከለ ፡ ሰው ፡ ሞግዚት ፡ የሆነ ፡ ሰው ፤ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፺፰ ፡ ለተገለጹት ፡ ጉዳዮች ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሰው ፡ ሰው ፡ ስምና ፡ ስለእሱ ፡ ሆኖ ፡ ወይም ፡ በተከለከለው ፡ ሰው ፡ ስምና ፡ ስለእርሱ ፡ ሆኖ ፡ የንግድ ፡ ሥራን ፡ እንዳይሠራ ፡ ይከለክላል ። ይህም ፡ ሞግዚቱን ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሰው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ በተከለከለው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ወይም ፡ የተከለከለውን ፡ ሰው ፡ ነጋዴ ፡ ከሚያደርገው ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ እንዳይገባ ፡ ይከለክለዋል ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፺፰ ፡ መሠረት ፡ ምግዚቱ ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባዔ ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠው ፡ እንደሆነ ፡ በልጁ ፡ ሀብት ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የንግድ ፤ የኢንዱስትሪ ፤ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ሥራዎች ፡ የተገኙ ፡ እንደሆነ ፡ እነዚህን ፡ ሥራዎች ለማካሄድ ፡ ይችላል ። የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ ሥራው ፡ እንዲካሄድ ፡ ወይም ፡ ሒሳብ ፡ እንዲጣራ ፡ ትዕዛዝ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ሞግዚትነቱ ፡ የሚቆይበትን ፡ ጊዜ ፤ የሞግዚቱን ፡ ችሎታዎችና ፡ ለማድረግ ፡ የሚቻለውን ፤ እንዲሁም ፡ ችሎታ ፡ የሌለውን ፡ ሰው ፡ ጥቅሞች ፡ መመልከት ፡ አለበት ። ከዚህም ፡

---

84. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፲፱ ፤ ፫፻፶፭ ፤ ፫፻፹፩ ።
85. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፹ ፡ (፪) ፤ ፳፻ ።

ውሳኔ ፡ ላይ ፡ የቤት ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባዔ ፡ ሞግዚቱ ፡ ንግድ ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ (ይኸውም ፡ ችሎታ ፡ የሌለውን ፡ ሰው ፡ ነጋዴ ፡ የሚያደርግ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ) ፡ እንዲገባ ፡ ፈቃድ ፡ ሊሰጥ ፡ የማይችል ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ይመስላል ። ሊሰጥ ፡ የሚችለው ፡ ፈቃድ ፤ ችሎታ ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ እንዲቀጥል ፡ ወይም ፡ ሒሳቡ ፡ እንዲጣራ ፡ የማድረጊያ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኝነትን ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ አላፊነቱ ፡ ያልተወሰነ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኛ ፡ ከሞተና ፤ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውሉ ፡ ልጅ ፡ የአባቱን ፡ ቦታ ፡ ይወስዳል ፡ የሚል ፡ ከሆነና ፡ ልጁ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ከሆነ ፡ ንግዱ ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ ክፍል ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ቁጥር ፡ ፩፻፺፰ ፤ የቤት ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ፈቃድ ፡ የሚፈልገው ፡ ሞግዚቱ ፡ "የልጁ ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ሆነ" ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ በግልጽ ፡ ይናገራል ። ሞግዚቱ ፡ የልጁ ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ የሆነ(ች) ፡ እንደሆነ ፡ በአካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሰው ፡ ልጅ ፡ ሀብት ፡ ክፍያ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ሥራዎች ፡ የማቆየት ፡ ወይም ፡ በሒሳብ ፡ እንዲጣሩ ፡ የማድረግ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ፡ (አላት) ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ግልጽ ፡ ባይሆንም ፡ እንኳ ፡ በአዲስ ፡ ሥራዎች ፡ ውስጥ ፡ እንዳይገባ ፡ የሚደረገው ፡ ክልከላ ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ በሆነና ፡ ባልሆነ ፡ ሞግዚትም ፡ ላይ ፡ ይጸናል ። እነዚህን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመተላለፍ ፡ በሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ የሚገባ ፡ ሞግዚት ፡ ከተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ በላይ ፡ አልፎአል ፡ ማለት ፡ ነው ።[86]

ቁጥር ፡ ፲፫ ፡ በሞግዚት ፡ ከመተዳደር ፡ ስለወጣ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅን ፡ በሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ወሰን ፡ ይጨምራል ። በቤት ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባዔ ፡ በጽሑፍ ፡ ሥልጣን ፡ ካልተሰጠው ፡ በቀር ፡ ከሞግዚት ፡ አስተዳደር ፡ ነፃ ፡ የወጣ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ የንግድ ፡ ሥራን ፡ እንዳይሠራ ፡ ይከለክላል ። ይህ ፡ ተጨማሪ ፡ ወሰን ፡ ከሞግዚት ፡ አስተዳደር ፡ ነፃ ፡ የወጣ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ልጅ ፡ በጽሑፍ ፡ ሥልጣን ፡ ካልተሰጠው ፡ በቀር ፡ ነጋዴ ፡ ሊያደርገው የሚችለውን ፡ የንግድ ፡ ማኅበርን ፡ የሚመሠርት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ተዋዋይ ፡ እንዳይሆን ፡ ይከለክላል ። ከሞግዚት ፡ አስተዳደር ፡ ነፃ ፡ የወጣ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ ተፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የጽሑፍ ፡ ፈቃድ ፡ ሳይኖረው ፡ ተዋዋይ ፡ የሚሆንበት ፡ ማንኛውም ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፤ ልጁ ፡ ከሞግዚት ፡ አስተዳደር ፡ ያልወጣ ፡ እንደሆነ ፡ ተቆጥሮ ፡ በችሎታ ፡ ማጣት ፡ ምክንያት ፡ ፈራሽ ፡ እንደሚሆነው ፡ ውል ፤ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

ችሎታ ፡ ያለመኖርን ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ የተሰጡት ፡ ችሎታ ፡ የሌለውን ፡ ሰው ፡ ለመከላከል ፡ ነው ። በጠቅላላው ፡ ውሎቹን ፡ ለማስፈረስ ፡ የሚችለው ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ የሆነው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የንግድ ፡ ሥራዎች ፡ (ስምምነቶች) ፡ ደህንነት ፡ እንዲጠበቅ ፡ ችሎታ ፡ ከሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ የሚደረጉ ፡ ውሎች ፡ ከሚያመጡት ፡ ችግር ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችንም ፡ የሕግ ፡ መከላከል ፡ እንዲደረግላቸው ፡ ያስፈልጋል ። የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፩ና ፡ ፲፰ ፡ ንግድ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ አለበት ፡ የሚለውን ፡ ዘይቤ ፡ በመጠቀም ፡ አንዳንድ ፡ መከላከያዎችን ፡ ይሰጣሉ ። በአንቀጽ ፡ ፲፩ ፡ መሠረት ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ እንዳደረሰ ፡ አድርጎ ፡ እራሱን ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ አስገብቶ ፡ ከተገኘ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ መሆኑ ፡ ሦስተኛ ፡

86. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፳፰ን ፡ ተመልከት ።

ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። ስለዚህም ፡ እካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ በእንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታዎች ፡ ውሎቹን ፡ ሊያስፈርስ ፡ አይችልም ። ቁጥር ፡ ፲፰ ፡ በሕግ ፡ የተከለከሉ ፡ ሰዎችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ተመሳሳይ ፡ ደንቦችን ፡ ይዞአል ። ችሎታ ፡ የሌላቸው ፡ መሆኑን ፡ የሚያስታውቅ ፡ ነገር ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ካልገባ ፡ በቀር ፡ ችሎታ ፡ የሌላቸው ፡ መሆኑ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ አይ ችልም ።[87]

ተዋዋዮች ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ያላገባ ፡ ሰው ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኛ ፡ ሊሆን ፡ እንደሚችል ፡ ሁሉ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ አባል ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይኸ ፡ አጠቃላይ ፡ የሆነ ፡ መመሪያ ፡ በሁለት ፡ ዓይነት ፡ መንገ ዶች ፡ መሻሻል ፡ አለበት ። አንደኛ ፡ ከሁለቱ ፡ አንደኛው ፡ (ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት) ፡ የሌላውን ፡ እንደ ፡ ነጋዴ ፡ የሚያስቆጥረውን ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኛ ፡ መሆንን ፡ "ለትዳራቸው ፡ ወይም ፡ ለቤት ፡ ዘመዳቸው ፡ መልካም ፡ አኗኗር" ፡ አይጠቅምም ፡ በሚል ፡ መቃወሚያ ፡ ሊቃወም ፡ ይችላል ። የዚህ ፡ ተቃውሞ ፡ ውጤትም ፡ የነጋዴው (ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት) ፡ ድርሻ ፡ የሆነው ፡ ማኅበሩ ፡ አላፊ ፡ የሆነበት ፡ ዕዳ ፡ በነጋ ዴው ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ መወሰን ፡ ነው ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነ ቶቹ ፡ ዕዳዎች ፡ እንደ ፡ ጋብቻው ፡ ዕዳዎች ፡ ተቆጥረው ፡ ከባልና ፡ ሚስቱ ፡ የግል ፡ ሀብ ትና ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ይከፈላሉ ። (ተቃውሞው ፡ ነጋዴ ፡ የሆነውን ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ የማኅበሩ ፡ ማኅበርተኛ ፡ ከመሆን ፡ አይከለክልም) ። ተቃውሞው ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ የሚጸናው ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ የገባ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ። የሚነግደው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ መቃወሚያው ፡ የማይደገፍ ፡ ነው ፡ የሚል እንደሆነ ፡ መቃወሚያው ፡ እንዲነሳለት ፡ ጉዳዩን ፡ ለቤተሰብ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ማቅረብ ፡ ይችላል ። መቃወሚያው ፡ እንዲቀር ፡ የተደረገ ፡ እንደሆነ ፡ ይህንኑ ፡ የሚ ያሳይ ፡ ማስታወቂያ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ እንዲገባ ፡ ማድረግ ፡ ይገባል ።[88]

ባልና ፡ ሚስትን ፡ የሚመለከተው ፡ መመሪያ ፡ መሻሻል ፡ የአለበት ፡ ሁለተኛው፡ መንገድ ፡ ባልና ፡ ሚስቱ ፡ በአንድነት ፡ የአንድ ፡ የኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኞች ፡ በሚሆኑበት ፡ ሁኔታ ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ባልና ፡ ሚስ ቶች ፡ ከጋብቻቸው ፡ በፊት ፡ ጋብቻቸው ፡ በግልና ፡ በገንዘባቸው ፡ ላይ ፡ የሚያመጣውን ፡ ውጤት ፡ በውል ፡ ሊወስኑ ፡ እንዲችሉ ፡ ይፈቅዳል ። "የጋብቻ ፡ ውል ፡" የሚባለው፡ ነገር ፡ የሌለ ፡ እንደሆነ ፡ በተጋቢዎቹ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የግልና ፡ የገንዘብ ፡ ግንኙ ነትን ፡ የሚወስኑ ፡ ደንቦች ፡ በሕጉ ፡ ተሰጥተዋል ። ጋብቻውን ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የጸደቀ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የገንዘብ ፡ ግንኙነታቸውን ፡ የሚወስን ፡ ውል ፡ ሊፈጽሙ ፡ አይችሉም ።[89]

ባልና ፡ ሚስቱ ፡ ለአንድ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኞች ፡ የሆኑ ፡ እንደሆነ፡ ውሉ ፡ የጸና ፡ እንዲሆን ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡

87. በቅን ፡ ልቦና ፡ ያልሆነ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ (ይኸውም ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ የተከለ ከለ ፡ መሆኑን ፡ የሚያውቅ ፡ በቁጥር ፡ ፲፬ ፡ ወይም ፡ ፲፭ ፡ ሊጠቀም ፡ ይችላል ፡ ወይ ? በቅን ፡ ልቦና ፡ የሚሠሩ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በመዝገብ ፡ ባልገቡ ፡ ጉዳዮች ፡ አይነኩም ፡ የሚለው ፡ የቁጥር ፡ ፻፳፩ ፡ ተደራጊዎች ፡ መሆናቸውን ፡ እነዚህ ፡ ውሳኔዎች ፡ ግልጽ ፡ ያደርጉታል ። ይህ ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ትር ጓሜ ፡ ውስጥ ፡ ነው ። የቁጥር ፡ ፻፳፩ ፡ ፈረንሣይኛ ፡ ትርጓሜ ፡ "በቅን ፡ ልቦና ፡" የሚለውን ፡ ሐረግ ፡ አይጨምርም ፡ (ይተዋል) ።

88. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯—፳ ፤ ፴፫ ፡ (፪) ፤ ፫፻ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፻፺፯ ፤ ፻፺፱ ።

89. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፻፸፯ ፤ ፻፷፯—፻፷፱ ።

ቤቱ ፡ መጽደቅ ፡ ይኖርበት ፡ ይሆናል ፡፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፲፫ ፡ ስለ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ በጭራሽ ፡ አይናገርም ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ቢናገርም ፡ በባልና ፡ ሚስት ፡ መሐከል ፡ ስላለው ፡ ስምምነት ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ አንዳንድ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮችን ፡ ስለሚያቋቁሙ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውሎች ፡ ብቻ ፡ ይሆናል ፡ የሚል ፡ ክርክር ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ፡፡ በንግድ ፡ ማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የባልና ፡ ሚስት ፡ ግንኙነት ፡ በፍትሐ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ጋብቻ ፡ ግዛት ፡ ከተሰጠው ፡ የባልና ፡ ሚስት ፡ ግንኙነት ፡ ጋር ፡ የጠበቀ ፡ ቅራኔ ፡ (ግጭት) ፡ ከሌለ ፡ በተቀር ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ የመጽደቅ ፡ አስፈላጊነት ፡ በማንኛውም ፡ ውል ፡ ላይ ፡ ግዳጅ ፡ ሊሆን ፡ አይገባውም ፡፡[90] ነገር ፡ ግን ፡ የጥያቄው ፡ መፍትሔ ፡ (መልስ) ፡ ከጥርጣሬ ፡ የራቀ ፡ አይደለም ፡፡[91]

ተዋዋዮች ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ስለተሰጣቸው ፡ ማኅበሮች ፡፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ማኅበር ፡ ለአንድ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ አባል ፡ መሆን ፡ መቻልና ፡ አለመቻል ፡ በመጠኑ ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ በተሰጠው ፡ ማኅበር ፡ ዐይነትና ፡ ማኅበርተኛ ፡ ሊሆን ፡ በፈለገበት ፡ ማኅበር ፡ ዐይነት ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ፡፡

በጠቅላላው ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ለሌላ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኛ ፡ ከመሆን ፡ የሚያግደው ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለም ፡፡[92] የገንዘብ ፡ ትርፍ ፡ ለማግኘት ፡ ያልተቋቋመ ፡ ማኅበር ፡ "የንግድ ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ ስለማይችል ፡" አላፊነቱ ፡ ያልተወሰነ ፤ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ለሚሠራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ኃላፊነት ፡ ለአለበት ፡ ማኅበር ፤ ማኅበርተኛ ፡ መሆን ፡ አይችልም ፡፡[93] ለሌላ ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኛ ፡ ለመሆን ፡ መቻሉና ፡ አለመቻሉ ፡ ማኅበርተኛ ፡ የሚሆነው ፡ ትርፍ ፡ ማግኘትን ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ዓላማው ፡ አድርጐ ፡ በመመልከቱና ፡ ባለመመልከቱ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ፡፡ ዓላማው ፡ ትርፍን ፡ ለማግኘት ፡ ከሆነ ፡ ማኅበርተኛ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ትርፍ ፡ ለማግኘት ፡ ያልተቋቋመ ፡ ማኅበር ፡ የማኅበሩን ፡ ሥራ ፡ ለማንቀሳቀስ ፡ የሚረዳውን ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ትርፍ ፡ ገንዘቡን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ ኃላፊነቱ ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኛ ፡ ከመሆን ፡ የሚከለክለው ፡ ነገር ፡ የለም ፡፡

የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኛ ፡ መሆንና ፡ አለመሆን ፡ የተመሠረተው ፡ ማኅበርተኛ ፡ በመሆኑ ፡ ትርፍ ፡ የማግኘትን ፡ አላማ ፡ በማ

90. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯፻፺፩—፲፯፻፺፮ ፡ ተመልከት ፡፡

91. በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ለአንድ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኛ ፡ ለመሆን ፡ ስለ ፡ መቻላቸው ፡ ወይም ፡ አለመቻላቸው ፡ ብዙ ፡ ክርክር ፡ ተደርጎ ፡ ነበር ፡፡ ኢ ፡ ቾርች ፤ ቢዝነስ ፡ አሶሴሽንስ ፡ አንደር ፡ ፍሬንች ፡ ሎው ፡ (ሎንዶን ፤ ስዊት ፡ ኤንድ ፡ ማክስዌል ፤ ፲፱፻፶፫) ቁጥር ፡ ፳፱ ፤ ትራቮ ፤ በማስረጃ ፡ ፴፱ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ፪ኛ ፡ ቮልዩም ፤ ገጽ ፡ ፪፻፴፭—፪፻፵፯ ፤ ፲፱፻፶፯ ፡ ፪ኛ ፡ ቮልዩም ፤ ገጽ ፡ ፳፯ ፤ ፳፰ ፤ ፲፱፻፷፪ ፡ ትልቁ ፡ ጥያቄ ፡ ጋብቻው ፡ በሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውሉ ፡ መሻሻሉና ፡ አለመሻሻሉ ፡ ነበር ፡፡ በኢትዮጵያው ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፲፫ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ትርጓሜ ፡ ከፈረንሳይኛው ፡ ትርጓሜ ፡ ለየት ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፡ አስታውሱ ፡፡ ከፈረንሣይኛው ፡ ሲተረጐም ፡ የሚገኘው ፡ ሻል ፡ ያለ ፡ ትርጉም ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡

ሀ) በቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ካልጸደቀ ፡ በቀር ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ተጋብተው ፡ በሚኖሩበት ፡ ጊዜ ፡ የሚደረግ ፡ (የሚፈጸም) ፡ የገንዘብ ፡ ግንኙነታቸውን ፡ የሚመለከት ፡ ውል ፡ በሕጉ ፡ ፊት ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ፡፡

ለ) በሕጉ ፡ በግልጽ ፡ የተሰጡ ፡ ውሎች ፡ በዚህ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙ ፡ ነገሮች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ፡፡

92. ስለ ፡ ንግድ ፡ ማኅበሮችና ፡ ስለ ፡ ማኅበሮች ፡ ችሎታ ፡ ከላይ ፡ በማስረጃ ፡ ፴፩—፴፫ ፡ የተጠቀሰውንና ፡ ተያይዞ ፡ ያለውን ፡ ጽሑፍ ፡ ተመልከት ፡፡

93. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፳፩ ፡፡

ማኘቱና ፡ ባለማግኘቱ ፡ ነው ። በጠቅላላው ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ትርፍ ፡ ለማግኘት ፡ ያልተቋቋመ ፡ ማኅበር ፡ ያለውን ፡ ዓይነት ፡ ችሎታ ፡ አለው ። (የንግድ ፡ ሥራን ፡ እንዳይሠራ ፡ የሚከለክለው ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ሕግ ፡ ባይኖርም ፡ እንኳ ።)[94] በአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ ኃላፊነቱ ፡ በተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ የሚገኙ ፡ አክሲዮኖች ፡ የበጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ የተቋቋመበት ፡ "ንብረት ፡" (ሀብት) ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ። የአደራ ፡ ንብረት ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ አባል ፡ መሆን ፡ መቻልን ፡ ወይም ፡ አለመቻልን ፡ የሚመለከት ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ መወሰኛ ፡ የለም ። እንደ ፡ በጎ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፤ የአደራ ፡ ንብረት ፡ የተቋቋመበት ፡ ንብረት ፡ (ሀብት) ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበርን ፡ ወይም ፡ ኃላፊነቱ ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበርን ፡ አክሲዮኖች ፡ ሊጨምር ፡ ይችላል ።

እንደ ፡ ጠቅላላ ፡ ደንብ ፤ መንግሥት ፤ የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ከተፈጥሮው ፡ ጋር ፡ የሚስማማ ፡ እስከሆነ ፡ ድረስ ፡ በሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ የመግባትና ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኛ ፡ የመሆን ፡ መብት ፡ አለው ።[95] ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ በአንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ የተወሰነ ፡ ነው ። አንደኛ ፡ የመንግሥቱ ፡ ማዛት ፡ ክፍሎች ፤ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ሚኒስቴሮች ፤ የሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍሎችና ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ያሏቸው ፡ መብቶች ፡ "በአስተዳደር ፡ ሕጎች ፡ የተፈቀዱት ፡" ብቻ ፡ ናቸው ። ይህም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ በአድባራትና ገዳማት ፡ ላይ ፡ ይጸናል ።[96] ይህም ፡ ማለት ፡ የነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ በሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ የመግባትና ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኛ ፡ የመሆን ፡ መብት ፡ ከአስተዳደር ፡ ሕግ ፡ ከተሰጠው ፡ መብት ፡ የተገኘ ፡ መሆን ፡ አለበት ። መብቱ ፡ በግልጽ ፡ የተሰጠ ፡ መሆን ፡ አይኖርበትም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ችሎታ ፡ በጠቅላላው ፡ ከተሰጠው ፡ ውስጥ ፡ እንደተገኘ ፡ ሊቆጠር ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ከሚሠራባቸው ፡ መብቶች ፡ በተዘዋዋሪ ፡ እንደተገኘ ፡ ወይም ፡ በግልጽ ፡ ከተሰጠ ፡ ሥልጣኖች ፡ እንደ ተገኘ ፡ ሊቆጠር ፡ ይቻላል ። በሐሳብ ፡ ዓለም ፡ (in theory) ነገሩ ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ። በተግባር ፡ ግን ፡ የሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍሎች ፤ ሚኒስቴሮችና ፡ ሌሎች ፤ ዓላማቸውን ፡ ከግቡ ፡ ለማድረስ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ በተለይም ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበሮች ፡ ማኅበርተኞች ፡ ይሆናሉ ። ሁለተኛው ፡ ውሳኔ ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ ይገኛል ። የአድሚኒስትራሲዮን ፡ ወይም ፡ የሃይማኖት ፡ ድርጅት ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ የሥራ ፡ ድርጅቶች ፡ የንግድ ፡ ሥራን ፡ መሥራት ፡ የሚችሉት ፡ በልዩ ፡ ሕጎች ፡ በተሰጡት ፡ ዓይነት ፡ ብቻ ፡ ነው ።[97] ምንም ፡ እንኳ ፡ የአድሚኒስትራሲዮን ፡ ወይም ፡ የሃይማኖት ፡ ድርጅት ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ማንኛውም ፡ የሕዝብ ፡ ሥራ ፡ ድርጅት ፡ የንግድ ፡ ሥራን ፡ የሚሠራ ፡ ቢሆንም ፡ እንደ ፡ ነጋዴ ፡ አይቆጠርም ።[98]

መንግሥቱ ፡ ጠቅላላ ፡ የማኅበርተኛነት ፡ ጥቅም ፡ ቢኖረውም ፡ እንኳ ፡ መንግሥቱ ፡ ወይም ፡ የመንግሥቱ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ አባል ፡ በመሆኑ ፡ ብቻ ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የተቋቋመ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ በመንግሥት ፡ ሕግ

---

94. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፹፫ ፤ ፬፻፬ ።

95. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፺ ።

96. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፺፩—፫፻፺፰ ።

97. "በልዩ" ፡ ሕጎች ፡ የሚለውን ፡ ሐረግ ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ንግድ ፡ ሕግ ፡ ይተወዋል ። የእንግሊዝኛው ፤ ትርጉሞች ፡ "ይዘረዘራሉ" ፡ ብቻ ፡ ይላል ። "በልዩ ፡ ሕግ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በፈረንሳይኛውና ፡ በአማርኛው ፡ ንግድ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ አሉ ።

98. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲ ።

የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ማኅበር ፡ አይሆንም ። መንግሥቱ ፡ ወይም ፡ የመንግሥቱ ፡ ክፍል ፡ እንደ ፡ ማንኛውም ፡ ሌላ ፡ ማኅበርተኛ ፡ ሆኖ ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ይቆያል ። መንግሥት ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በተቋቋመ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ ሊካፈል ፡ ስለሚችልበት ፡ መንገድ ፡ የሚገልጽ ፡ የተለየ ፡ ሕግ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የለም ።[99]

<u>ተዋዋዮች ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡</u> በጠቅላላው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መብቶች ፡ የመሥራትና ፡ የመጠቀም ፡ ችሎታን ፡ በሚመለከተው ፡ ረገድ ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሆነው ፡ ይቆጠራሉ ። በመንግሥቱ ፡ መካፈልን ፡ ካለመጨመሩ ፡ በቀር ፡ "የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መብቶች" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ሁሉንም ፡ መብቶች ፡ ያጠቃልላል ።[100] ስለዚህም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ተቆጥሮ ፡ በሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ ይችላል ።

የማኅበሮቹ ፡ ዋና ፡ መኖሪያ ፡ ሥፍራ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የሆነ ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ማኅበሮችና ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የተቋቋሙ ፡ ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደቡ ፡ ንብረት ፡ ድርጅቶች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ እንዲሠሩ ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ፈቃድ ፡ ከተሰጣቸው ፡ ልክ ፡ "በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ እንደተቋቋሙ" ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ እንደተሰጣቸው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ማኅበሮችና ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ አገልግሎት ፡ እንደተመደቡ ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ንብረቶች ፡ ተቆጥረው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መብቶች ፡ ሊኖራቸውና ፡ በነዚህም ፡ መብቶች ፡ ሊጠቀሙባቸው ፡ ይችላሉ ።[101] ስለዚህም ፤ ሥራ ፡ እንዲሠሩ ፡ ከተፈቀደላቸው ፤ እነዚህ ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ማኅበሮችና ፡ ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደቡ ንብረቶች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ቢቋቋሙ ፡ ኖሮ ፡ ይኖራቸው ፡ የነበረውን ፡ በሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ የመግባት ፡ መብት ፡ ዓይነት ፡ መብት ፡ አላቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ አገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ማኅበሮች ፡ ወይም ፡ በልዩ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደቡ ፡ ንብረት ፡ ድርጅቶች ፡ ወይም ፡ አንዳንድ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ የሆኑትን ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ማኅበሮችና ፡ ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ የተመደቡ ፡ ንብረቶች ፡ የሚያከኂ

---

99. የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የሚፈጽሟቸውን ፡ ውሎች ፡ የሚመራውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፱ን ፡ አወዳድር ። "ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ብዙ ፡ የዓለአክሲዮኖች ፡ ክፍል ፡ (ግሩፕ) ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታቸው ፡ የተለየ ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ ለአስተዳደር ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ እንደራሴ ፡ እንዲመርጡ ፡" የሚለውን ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፶፪ ፡ በተጨማሪ ፡ አወዳድሩ ፡ ይህም ፡ የመንግሥት ፡ አክሲዮኖች ፡ ያሉት ፡ ድርጅት ፡ ቢሆንም ፡ ባይሆንም ፡ እያንዳንዱን ፡ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ አስተዳዳሪ ፡ የሚወክላቸው ፡ መሆኑን ፡ ያረጋግጣል ። የመንግሥት ፡ በንግድ ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ መካፈል ፡ የሚያመጣውን ፡ ልዩ ፡ ችግሮችና ፡ መፍትሔአቸውን ፡ ለመግለጫ ፡ የመንግሥት ፡ በንግድ ፡ ማኅበር ፡ መካፈል ፡ ብዙ ፡ በነበረበት ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ኤ ፡ ደላውባደሬ ፤ <u>ትሬይት ፡ ኤለመንታሬ ፡ ዴ ፡ ድሮዋ ፡ አድሚኒስትራቲፍ</u> ፤ (ፓሪስ ፡ ኤልጂዲጀ) ፡

100. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፵፬ ።

101. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፵፭—፫፻፵፯ ። በማስረጃ ፡ ፵፰ ፡ የተሰጠውንና ፡ ተያይዞ ፡ ያለውን ፡ ጽሑፍ ፡ በተጨማሪ ፡ ተመልከት ። እነዚህ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ ለተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፡ በማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ መጽደቅ ፡ ያለባቸው ፡ መሆኑንና ፡ ሌሎቹ ፡ ድርጅቶች ፡ ደግሞ ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ መጽደቅ ፡ እንዳለባቸው ፡ ይገልጻሉ ። የማኅበሮች ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ክፍል ፡ ነው ። በቁጥር ፡ ፫፻፵፮ ፡ (፪)ና ፡ ፫፻፵፯ ፡ መሠረት ፡ ለመቋቋም ፡ የተፈለጉ ፡ ሥራዎች ፡ "ሕገ ፡ ወጥ ፡ ወይም ፡ ከመልካም ፡ ባህል ፡ ጋር ፡ የማይስማሙ ፡ ከሆነ" ፡ ፈቃዱ ፡ ሊወሰድ ፡ ይቻላል ። በሌላ ፡ ምክንያቶች ፡ ፈቃድ ፡ ሊወሰድ ፡ መቻሉ ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ።

ዱትንና ፡ የሚያከናውኑትን ፡ ሥራ ፡ ሊከለክል ፡ ወይም ፡ ሊፈቅድ ፡ ይችላል ።[102] በተጨማሪም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሥራን ፡ ለማካሄድ ፡ የተሰጠው ፡ ፈቃድ ፤ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ካለ ፡ ሊሻር ፡ ይችላል ።[103]

ሌሎች ፡ ሥራዎችን ፡ ሳያካሄድ ፡ ወይም ፡ ሳያከናውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኝ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኛ ፡ ለመሆን ፡ ብቻ ፡ የሚፈልግ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ድርጅት ፡ አቋም ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ። በሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ በሚኒስቴሩ ፡ መጽደቅ ፡ የሚገባው ፡ "የሥራ" ፡ መካሄድ ፡ ነው ፡ ወይ? በማኅበሩ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ በደንብ ፡ መካፈልን ፡ የመሰለ ፡ ሌላ ተጨማሪ ፡ ነገር ፡ መኖር አለበት ፡ ወይ ? ይህ ፡ ጉዳይ ፡ በተቋቋመው ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ዓይነት ፡ የሚመሠረት ፡ ነው ፡ ወይ ? በተግባር ፡ እንደሚታየው ፤ ገንዘባቸውን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ያዋሉ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ ገንዘባቸውን ፡ በሚያወጡበት ማኅበር ፡ ሥራ ፡ ቁጥጥር ፡ ላይ ፡ ስለሚካፈሉ ፡ እነዚህ ፡ ጥያቄዎች ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ጠቃሚዎች ፡ ላይሆኑ ፡ ይችላሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ አክሲዮን ፡ ማኅበር ዓመታዊ ፡ በሆነው ፡ የማኅበርተኞች ፡ ስብሰባ ፡ ድምፅ ፡ ከመስጠትና ፡ ትርፎችን ፡ ከመቀበል ፡ በስተቀር ፡ በሌሎች ፡ የማኅበሩ ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ በትንሹ ፡ ሊሚካፈሉ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋዎች ፡ አክሲዮኖችን ፡ የሸጠ ፡ እንደሆነ ፡ ይህን ፡ ዓይነቱ ፡ ሁኔታ ፡ በርግጥ ፡ ይነሳል ።

የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋዎች ፤ ሰዎችም ፡ ሆኑ ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፤ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ልዩ ፡ ሥራዎችን ፡ እንዳይሠሩ ፡ የሚወስኑ ፡ (የሚከለክሉ) ፡ ሕጎች ፡ አሉ ። ማኅበርተኛ ፡ ለሚሆን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ጠቃሚ ፡ ቢሆኑም ፡ እነዚህ ፡ ሕጎች ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ የመግባት ፡ መብትን ፡ አይወስኑም ፡ (አይከለክሉም) ። ለምሳሌ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፡ ካልተፈቀደለት ፡ በቀር ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኛ ፡ ቢሆንም ፡ የማኅበሩ ፡ ሠራተኛ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።[104] በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ.ም ቱ ፡ ገንዘብን ፡ (ካፒታልን) ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ስለማዋል ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ ዓይነት ፡ ልዩ ፡ ሕጎች ፡ መሠረት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የመሬት ፡ ባለሀብት ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።[105] የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ካልሆነ ፡ በቀርና ፡ ቢያንስ ፡ የዋና ፡ ገንዘቡ ፡ ፶፩ ፡ በመቶ ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ሀብት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፤ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የባንክ ፡ ሥራን ፡ እንዲሠራ ፡ ፈቃድ ፡ አይሰጠውም ።[106]

---

102. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፳፻፹፰ ፡ (፩) ፡ የፈረንሣይኛው ፡ ትርጓሜ ፡ ይህን ፡ ሥልጣን ፡ "ለመንግሥቱ ፡ ድንጋጌ" ፡ ይሰጠዋል ፤ ለሚኒስቴሩ ፡ ግን ፡ አልተሰጠውም ።

103. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፳፻፺፱ ። በፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊሻር ፡ ከመቻሉም ፡ በቀር ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ውሳኔ ፡ በግልጽ ፡ ይደረጋል ።

104. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፺፬ ፡ (፫) ፡ ን ፡ ተመልከት ፤ የሠራተኞች ፡ ጉዳይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የተቋቋመበት ፡ ትዕዛዝ ፤ ፲፱፻፶፬ ፡ ቁጥር ፡ ፲፰ ፤ ትዕዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፯ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፩ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲፰ ፡ ተመልከት ። በተጨማሪም ፡ ስለውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ የሥራ ፡ ፈቃድ ፡ አሰጣጥ ፡ የወጣ ፡ ደንብ ፤ (፲፱፻፶፰) ፤ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፤ ቁጥር ፡ ፪፻፲፭ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፯ኛ ፡ ዓመት ፤ ቁጥር ፡ ፪ ።

105. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፺—፫፻፺፫ ፤ ፳፻፶፰ ፤ የውጭና ፡ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ገንዘብ ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ እንዲውል ፡ ለማበረታታት ፡ የወጣ ፡ ድንጋጌ ፤ ፲፱፻፶፯ ፤ ቁጥር ፡ ፲ ፤ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፶፩ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፫ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፤ ገንዘብን ፡ (ካፒታልን) ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ስለማዋል ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፤ ፲፱፻፶፱ ፤ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፷፪ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፯ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፪ ።

106. የገንዘብና ፡ የባንክ ፡ ሥራ ፡ አዋጅ ፤ ፲፱፻፷፫ ፡ ቁጥር ፡ ፴፪ ፤ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፺፮ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፰ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፮ ።

በመጨረሻም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ አባል ፡ ለመሆን ፡ የሚፈልግ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ትርፎችን ፡ የመውሰድ ፡ መብቱን ፤ በመፍረስ ፡ የሚገኙ ፡ ንብረቶችንና ፡ ሌሎችንም ፡ የመውሰድ ፡ መብቱን ፡ የሚወስኑትን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ ልውውጥ ፡ ቁጥጥር ፡ ደንቦችን ፡ ማወቅ ፡ አለበት ።[107]

ፈቃድ ፡ እያንዳንዱ ፡ የውል ፡ ተዋዋይ ፡ ከጉድለት ፡ ነፃ ፡ የሆነ ፡ ፈቃዱን ፡ መስጠት ፡ አለበት ፤ ይኸውም ፡ ስህተት ፤ ተንኰል ፤ ወይም ፡ ግዳጅ ፡ የሌለው ፡ ፈቃዱን ፡ ማለት ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ጉድለቶች ፤ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ በሚቋቋምበት ፡ ጊዜ ፤ ከብዙ ፡ መንገዶች ፡ ሊመጡ ፡ ይችላሉ ። ለምሳሌ ፡ ተዋዋዩ ፡ ስለሚቋቋመው ፡ ማኅበር ፡ ዓይነት ፡ ሊሳሳት ፡ ይችላል ። ወይም ፡ ደግሞ ፡ ማኅበሩ ፡ ስለሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ሊጭበረበር ፡ ይችላል ። የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውሉ ፡ ለአንደኛው ፡ ተዋዋይ ፡ ወገን ፡ ያነሰ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጥ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነና ፡ የዚህ ፡ ተዋዋይ ፡ ፈቃድ ፡ የተገኘው ፡ ችግሩን ፤ የመንፈስ ፡ ቀላልነቱን ፤ መጃጀቱን ፤ በዕድሜ ፡ መግፋቱን ፡ ወይም ፡ በንግድ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ የልማድ ፡ ዕውቀት ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ በመደገፍ ፡ እንደሆነና ፡ በሕሊናም ፡ ግፍ ፡ መስሎ ፡ ሲታይ ፡ በዚሁ ፡ ተዋዋይ ፡ ጥያቄ ፡ ብቻ ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ይቻላል ።[108]

ጉዳይ ፡ እንደማንኛውም ፡ ውል ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ በቂ ፡ የሆነ ፤ እርግጠኛነት ፡ ያለው ፤ የሚቻልና ፡ ሕጋዊ ፡ የሆነ ፡ ጉዳይ ፡ እንዲኖረው ፡ ያስፈልጋል ። "ጉዳይን ፡" በሚገልጽበት ፡ ጊዜ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በይበልጥ ፡ በተዋዋዮቹ ፡ ስለአለው ፡ የተከፋፈለ ፡ ኃላፊነት ፡ ያወራል ።[109] እነዚህም ፤ በሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ላይ ፡ ማኅበርተኞቹ ፡ መዋጮ ፡ ለማድረግ ፡ የሚስማሙበትንና ፡ ውሉ ፡ የሚፈጸምበትን ፡ የሚመለከቱ ፡ ሌሎች ፡ ኃላፊነቶችን ፡ ይይዛሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ጉዳይ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሩን ፡ ዓላማ ፡ ይጨምራል ፡ ተብሎ ፡ ሊተረጐም ፡ ይችላል ። ስለዚህም ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ዓላማዎች ፡ በቂ ፡ የሆኑ ፤ እርግጠኛነት ፡ ያላቸው ፤ የሚቻሉና ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑ ፡ እንዲሆኑ ፡ ያስፈልጋል ።[110]

የውል ፡ ጉዳይ ፡ ውሉን ፡ ከሚፈጽሙት ፡ ተዋዋዮች ፡ ምክንያት ፡ የተለየ ፡ ነው ። "ምክንያት ፡" ማለት ፡ ተዋዋዮቹ ፡ በውሉ ፡ የሚገቡበት ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡

---

107. የውጭ ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ ምንዛሬ ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፶፯ ፤ አዋጅ ፤ ቁጥር ፡ ፪፻፲፩ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፫ኛ ፡ ዓመት ፤ ቁጥር ፡ ፮ ፤ የውጭና ፡ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ገንዘብ ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ እንዲውል ፡ ለማበረታታት ፡ የወጣ ፡ ድንጋጌ ፤ ፲፱፻፶፭ ፡ ቁጥር ፡ ፰ ፤ ድንጋጌ ፡ ቁጥር ፡ ፵፩ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፪ኛ ፡ ዓመት ፤ ቁጥር ፡ ፩ ፤ ገንዘብን ፡ (ካፒታልን) ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ስለማዋል ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፤ ፲፱፻፶፱ ፤ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፵፪ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፮ኛ ፡ ዓመት ፤ ቁጥር ፡ ፪ ።

108. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯፻፲፭ ፡ (፩) ። በጠቅላላው ፡ ፈቃድን ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯፻፺፯—፲፯፻፲፩ ፤ ፲፯፻፺፱—፲፯፻፲፫ ። ሕዝቡ ፡ ፈርሞ ፡ በመግዛት ፡ በሚያቋቁመው ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ የፈራሚው ፡ ፈቃድ ፡ ጉድለት ፡ የሚገናኘው ፡ ከማኅበሩ ፡ መቋቋሚያ ፡ ጽሑፍ ፡ ይበልጥ ፡ በቀጥታ ፡ ከፈርማው ፡ ውል ፡ ጋር ፡ ነው ።

109. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯፻፲፩—፲፯፻፲፯ ፡

110. በማስረጃ ፡ ቁጥር ፡ ፴፫ ፡ የተጠቀሰውን ፤ ጂ. ሪፐርት ፤ ቁጥር ፡ ፯፻፲፩ ። (የፈረንሣይ ፡ ሕግ) ። ችግሩ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ትንሽ ፡ ለየት ፡ ይላል ፡ ምክንያቱም ፡ በፈረንሣይ ፡ አገር ፡ እንደሚደረገው ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ ይልቅ ፡ ከውል ፡ የሚገኝ ፡ ስብሳቤ ፡ (ግሩፕ) ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ስለሚተረጐምና ፡ የውል ፡ ጉዳይን ፡ የሚመለከቱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ድንጋጌዎች ፡ በተዋዋዮቹ ፡ መሐከል ፡ ስለአለው ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ አላፊነት ፡ አጥብቀው ፡ ስለሚናገሩ ፡ ነው ። የጉዳዩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በተለይም ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮችን ፡ በሚመለከትበት ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ እንደዚህ ፡ የተወሰኑ ፡ መሆን ፡ ያለባቸው ፡ አይመስልም ።

ዓላማ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህ ፤ በሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ላይ ፡ የማኅበሩን ፡ የሥራ ፡ ዓላማ ፡ ይጨምራል ፡ በማለት ፡ ሊተረጐም ፡ ይቻላል ፡ ብሎ ፡ መከራከር ፡ ይቻላል ። የውሉ ፡ ጉዳይ ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ መሆኑን ፡ ለመወሰን ፡ በሚያደርገው ፡ ሙከራ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፤ የተዋዋዮችን ፡ ምክንያት ፡ መመርመር ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ይናገራል ። ነገር ፡ ግን ፡ የአንዱ ፡ ወይም ፡ የሁሉም ፡ ተዋዋዮች ፡ ምክንያት ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ወይም ፡ መልካም ፡ ጠባዩን ፡ የሚቃረን ፡ የሆነ ፡ እንደሆነና ፡ ውሉ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ጽሑፍ ፡ ይህንኑ ፡ የሚያሳይ ፡ ከሆነ ፡ ውሉ ፡ በማንኛውም ፡ ተዋዋይ ፡ ጠያቂነት ፡ ወይም ፡ በማንኛውም ፡ ጥቅም ፡ ባለው ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ጠያቂነት ፡ ሊፈርስ ፡ ይችላል ።[111] በጉዳይና ፡ በምክንያት ፡ መሐከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ የተደረገው ፡ ምናልባት ፡ የውሎች ፡ መሠረት ፡ እርግጠኛ ፡ ባልሆነ ፡ በተዋዋዮች ፡ ጭንቅላት ፡ ላይ ፡ በተደረገ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ምርመራ ፡ የሚወሰን ፡ እንዳይሆን ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ችግሮች ፡ ሊወገዱ ፡ የሚችሉት ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የንግድ ፡ ዓላማዎችን ፡ በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ እንደሚደረገው ፤ ምክንያቶቹ ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ የታዩ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

አንዳንድ ፡ የሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ሊካሄዱ ፡ ወይም ፡ ላይካሄዱ ፡ ስለሚችሉ ፡ ሥራዎች ፡ በግልጽ ፡ ይናገራሉ ። አንድን ፡ ንግድ ፡ ለማካሄድ ፡ ተፈላጊ ፡ ልዩ ፡ ግዳጅ ፡ ካለና ፡ የንግድ ፡ ማኅበሩ ፡ ያን ፡ ግዳጅ ፡ ካሟላቱ ፡ ከተገኘና ፡ ያንን ፡ ንግድ ፡ ለማካሄድ ፡ ካልተከለከለ ፡ በቀር ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ማናቸውንም ፡ የንግድ ፡ ሥራዎች ፡ ለማካሄድ ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፳፪ና ፡ ፳፮ ፡ ይናገራሉ ።[112] የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፲፫ ፡ ኃላፊነታቸው ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበሮችን ፡ "የባንክ ፤ የኢንሹራንስ ፡ እንደዚሁም ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡" ድርጅቶችን ፡ ለማቋም ፡ (ለማቋቋም ፡) ይከለክላቸዋል ። ተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ ማናቸውንም ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭ ፡ የተጠቀሱት ፡ ሥራዎች ፡ እንደ ፡ ጉዳይ ፡ ሊኖራቸው ፡ አይችልም ። ይህን ፡ ክልከላ ፡ መጣስ ፡ የሚያስከትለው ፡ ቅጣት ፡ የማኅበሩ ፡ መፍረስን ፡ ሳይሆን ፡ ተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሩ ፡ እንደ ፡ ኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሆኖ ፡ መቆጠር ፡ ነው ።[113] (የማኅበሩ ፡ መፍረስ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፹፩ ፡ የሚፈለጉትን ፡ ነገሮች ፡ ባለማሟላት ፡ ወይም ፡ ተፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ ምዝገባና ፡ በማስታወቂያ ፡ መውጣትን ፡ ባለማድረግ ፡ ሊመጣ ፡ ይችላል) ። ሌሎች ፡ ክልከላዎች ፡ በልዩ ፡ ሕጎች ፡ ሊሰጡ ፡ ይችላሉ ።

---

111. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯፻፲፮ ፤ ፲፯፻፲፯ ፤ ፲፰፻፰ ፡ (፪) ፡ የቁጥር ፡ ፲፰፻፰ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ትርጓሜ ፡ የሚናገረው ፡ ውሉ ፡ የተቋቋመበት ፡ ጉዳይ ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ለሕሊና ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ሰውሉ ፡ አጻጻፍ ፡ የተደነገገው ፡ ፎርም ፡ አልተጠበቀም ፡ በማለት ፡ ሊፈርስ ፡ ስለመቻሉ ፡ ብቻ ፡ ይናገራል ። ምክንያትን ፡ አይገልጽም ፡ (አይጨምርም) ። የፈረንሳይኛና ፡ የአማርኛው ፡ ትርጓሜ ፡ ግን ፡ ሁለቱንም ፡ ይጨምራል ። የነዚህም ፡ ውጤት ፡ ከሕግ ፡ ውጪ ፡ በሆነ ፡ ወይም ፡ ለሕሊና ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ ጉዳይ ፡ መፍረስ ፡ እንደሚቻል ፡ ሁሉ ፡ ከሕግ ፡ ውጪ ፡ ወይም ፡ ለሕሊና ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ መፍረስ ፡ የሚያስችል ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

112. የቁጥር ፡ ፳፮ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ትርጓሜ ፡ ቁጥር ፡ ፳፪ ፡ ከሚለው ፡ ትንሽ ፡ ይለያል ። የፈረንሣይኛው ፡ ትርጓሜ ፡ የተከለከለውን ፡ ንግድ ፡ የሚያካሄዱ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ግዳጅ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ሳያሟላ ፡ የተገኘ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡ ይላል ። ስለዚህም ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ና ፡ ፳፬ ፡ ለሰዎች ፤ ቁጥር ፡ ፳፭ ፡ ለማኅበሮች ፡ የሚሰጡትን ፡ ዓይነት ፡ መቀጫ ፡ ይኸኛውም ፡ ይሰጣል ። የአማርኛው ፡ ትርጓሜ ፡ ለእንግሊዝኛው ፡ ይቀርባል ። ነገሩ ፡ አከራካሪ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ መቀጫ ፡ አይሰጥም ።

113. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲ ፤ ፭፻፲፫ ። በመዝገብ ፡ የገቡ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ "ካልተፈቀደ ፡ ሥራ" ፡ እንዳይሠማሩ ፡ የሚከለከለውን ፡ የ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. የንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሥራዎችን ፡ ስለማስመዝገብ ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፤ ቁጥር ፡ ፩፻፹፬ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ፳፭ኛ ፡ ዓመት ፤ ቁጥር ፡ ፫ ፤ ቁጥር ፡ V (፮)ን ፡ አወዳድር ።

አጻጻፍ ፡ (ፎርም) ፡ በጠቅላላው ፡ በግልጽ ፡ የሚደረግ ፡ የሕግ ፡ ግዳጅ ፡ ወይም ፡ ተዋዋዮች ፡ የሚወስኑት ፡ የተለየ ፡ መንገድ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ጽኑ ፡ የሆነ ፡ ውልን ፡ ለመፈረም ፤ የተለየ ፡ አጻጻፍ ፡ (ፎርም) ፡ አያስፈልግም ። የተለየ ፡ ጽሑፍ ፡ (ፎርም) ፡ እንዲኖር ፡ ከታዘዘና ፡ ያን ፡ ጽሑፍ ፡ (ፎርም) ፡ ካልተከተለ ፡ ጽኑ ፡ የሆነ ፡ ውል ፡ የለም ፡ ማለት ፡ ነው ።[114]

በመሠረቱ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውልን ፡ ለማቋቋም ፡ ምንም ፡ የተለየ ፡ ጽሑፍ ፡ አያስፈልግም ። ነገር ፡ ግን ፡ የንግድ ፡ ሕጉ ፡ ከእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ በቀር ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ በጽሑፍ ፤ በማስታወቂያ ፡ በመውጣትና ፡ በመመዝገብ ፡ እንዲቋቋም ፡ ያስገድዳል ። በነዚህ ፡ ተፈላጊ ፡ መንገዶች ፡ ያለመቋቋም ፡ ማኅበሩን ፡ እንደሌለ ፡ ያስ ቆጥረዋል ፤ መኖሩም ፡ አይታወቅለትም ።[115]

የንግድ ፡ ማኅበር ፡ በሚቋቋምበት ፡ ጊዜ ፡ ግዳጅ ፡ የሆነ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በማ ስታወቂያ ፡ የመውጣት ፡ ግዳጅ ፡ አለመኖር ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ ግዳጅ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ጽሑፍ ፡ (ፎርም) ፡ ያለመኖር ፡ ከሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ሊቋቋም ፡ የታሰበው ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ ውል ፡ መሰረዝ ፡ ነው ። የንግድ ፡ ማኅበር ፡ የተሰረዘ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በተወሰነበት ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ እንደ ሚሆን ፡ የሚወስኑ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሉም ። ነገር ፡ ግን ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ መሰረዝ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ የረጅም ፡ ጊዜ ፡ ውል ፡ መሰረዝ ፡ ከሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ ጋር ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ይመሳሰላል ። ስለዚህም ፡ ቢያንስ ፡ በማኅበሩ ፡ መሰረዝና ፡ በሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውሉ ፡ መሰረዝ ፡ መሐከል ፡ ትርጉም ፡ ያለው ፡ ልዩ ነት ፡ በሌለ ፡ ጊዜና ፡ ተፈላጊውን ፡ ጽሑፍ ፡ (ፎርም) ፡ በማጣት ፡ ምክንያት ፡ የን ግድ ፡ ማኅበሮችን ፡ መሰረዝ ፡ በምንፈልግበት ፡ ጊዜ ፡ የውሎችን ፡ መሰረዝ ፡ የሚመለ ከቱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንዲጸኑባቸው ፡ ማድረግ ፡ ተገቢ ፡ ይመስላል ።

## መደምደሚያ ፤

ከላይ ፡ የተገለጹት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ነዋሪና ፡ እውነተኛ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ከመሆናቸው ፡ በፊት ፡ ከጊዜ ፡ ብዛት ፡ በሚገኙ ፡ በንግድና ፡ በአስተዳደር ፡ ልምምድ ፤ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔና ፡ በዐዋቂዎች ፡ ትርጓሜ ፡ እየዳበሩ ፡ የሚሄዱ ፡ የሕግ ፡ ክፍ ሎች ፡ (legal skeleton) ናቸው ። ይህም ፡ ጽሑፍ ፡ የተፃፈው ፤ ለአንዳንድ ፡ አጠቃ ላይ ፡ መመሪያዎች ፡ የሚደረገው ፡ የመጀመሪያ ፡ ገለፃ ፤ ይህንኑ ፡ የሥራ ፡ መሥ መር ፡ ሊያፋጥነው ፡ (ሊያካሂደው) ፡ ይችላል ፡ በሚል ፡ ተስፋ ፡ ነው ።

114. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯፻፲፱ ፤ ፲፯፻፳ ፡ (፩) ፤ ፲፯፻፳፪ ።
115. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፩ ፤ ፪፻፲፪ ፤ ፪፻፵፫ ።